ለሁለት ሺ ብር ሞባይል ሲባል
የጠፋ የሰው ሕይወት
ገጽ 10

ተፈሳጊ ሰው የመሆን ምስጢር
ገጽ 12

የ"ቢም" ቴክኖሎጂ - የግንባታ
ኢንዱስትሪው አዲስ መንገድ
ገጽ 14


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

83ኛ ዓመት ቁጥር 117 ታኅሣሥ 27 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

# የዓባይ ግድብ
# ወደ ማጠናቀቂያው ምዕራፍ ተሸጋገሯል

- ከኅብረተሰቡ ከ18 ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ተደርጓል

**አማን ረሺድ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የዓባይ ግድብ በኢትዮጵያውያን የተባበረ ጥረትና ጽናት ወደ ማጠናቀቂያው ምዕራፍ መሸጋገሩን የዓባይ ግድብ ማስተባበሪያ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አስታወቀ።

የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ ኅዳር 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከ18 ቢሊዮን 734 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የዓባይ ግድብ ማስተባበሪያ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ባካሄደው ስብሰባ የግድቡን የግንባታ ሂደትና የአምስት ወራት አፈጻጸምን ገምግሟል።

በግምገማው መሠረት የዓባይ ግድብ በኢትዮጵያውያን

የዓባይ ግድብ ... ወደ ገጽ 9 ዞሯል








# በዓልና የጥበብ ደጁ ሽሮ ሜዳ

**ሔርሞን ፍቃዱ**

ወትሮ በዓል መድረሱን የሚያስታውሱንና ቅድሚያ እንደ ምልክት የሚታዩ ናቸው-ባሕላዊ አልባሳቶቻችን፡፡ አሁንም ለክርስቶስ ልደት በዓል በብዛትና በዓይነት ሽሮ ሜዳ ከሚገኘው ታላቅ ገበያ ለዓይን አዋጅ እስኪሆን ድረስ አምረውና አጊጠው እየተሸጡ ተመለከትን፡፡

ነጋዴዎች ደምበኞቻቸውን ለማስተናገድ

በዓልና የጥበብ... ወደ ገጽ 9 ዞሯል




ፎቶ - ገበበ ገብረ

# "የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ የሀገራችንን ታሪክና ባሕል እንድናውቅ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል"

. በውጭ የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን

ገጽ 9

# ተቋማቱ ለገና እና ለጥምቀት በዓላት የተሳካ አገልግሎት ለመስጠት ተዘጋጅተዋል

**መስከረም ሰይፉ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በአዲስ አበባ ለገና እና ለጥምቀት በዓላት የተሳካ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ለመስጠት በቂ ዝግጅት መደረጉን የአዲስ አበባ ከተማ ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት እና ተጠሪ ተቋማት አስታወቁ፡፡

ተቋማቱ ለገና... ወደ ገጽ 9 ዞሯል








ዜና



ወይዘሮ ሙሉእመቤት ታደሰ

# ኅብረተሰቡ በበዓላት ወቅት ከሚቀርቡ ጥራት የሌላቸው የምግብና የመጠጥ አቅርቦቶች እንዲጠነቀቅ ባለሥልጣኑ አሳሰበ

**ማሕሌት ብዙነህ እና መክሊት ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡ መጪውን የገናና የጥምቀት በዓላት መሠረት አድርገው ለገበያ ከሚቀርቡ ጥራት የሌላቸው የምግብና የመጠጥ አቅርቦቶች ኅብረተሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርግ የአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን አሳሰበ።

የአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሙሉእመቤት ታደሰ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደገለጹት፤ ኅብረተሰቡ መጪውን የገናና የጥምቀት በዓላት ተከትሎ ለገበያ ከሚቀርቡ ጥራት የሌላቸው ምግብና መጠጦች እራሱን ሊጠብቅ ይገባል።

ወይዘሮ ሙሉእመቤት በዓላትን አስመልክቶ ጥራቱ የተጠበቀ ምርት የሚያቀርቡ በርካታ የንግድ አካላት መኖራቸውን አመልክተው፤ በተቃራኒም ጥቂት ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን የማይወጡና ለጤና ጎጂ ምርቶችን የሚያቀርቡ ነጋዴዎች እና ግለሰቦች መኖራቸውን ተናግረዋል።

በመሆኑም ኅብረተሰቡ የሚሸምተውን ምግብና መጠጥ ጤናማነቱን በማረጋገጥ እንዲሁም ሕጋዊ ከሆነ አካል መመረቱን ሊያረጋግጥ ይገባልም ብለዋል።

ባለሥልጣኑ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ የምግብና የጤና ተቋማትን እንዲሁም የጤና ባለሙያዎችን ብቃት በማረጋገጥና ቁጥጥር በማድረግ የኅብረተሰቡን ጤና ማስጠበቅ ነው ያሉት ወይዘሮ ሙሉመቤት፤ በሚያደርገው ቁጥጥር በምግብ ግብዓቶች ውስጥ ባዕድ ነገር መቀላቀልን ጨምሮ ሕገወጥና ለጤናና ጎጂ የሆኑ ምርቶችን የሚያቀርቡ አካላት ላይ እርምጃዎችን እንደሚወስድ ገልጸዋል ።

በአዲስ አበባ በዓላትን መሠረት በማድረግ በርካታ ሕገወጥ ተግባራት በስፋት መሠራታቸው ቀደም ሲል ከተደረገ የቁጥጥር ልምድ የሚታወቅ መሆኑን ገልጸው፤ በዋናነት ከበዓል ጋር ተያይዞ ሕገ ወጥ እርድን፣ በዋጋ ቅናሽ ቤት ለቤት ከሚሸጡ ነገሮችና የአገልግሎት ጊዜያቸው ካበቃ ምርቶችና ምግቦች መጠንቀቅ ይገባል ብለዋል።

ይህም ተግባር በዜጎች እና በሀገር ደረጃ የጤና፣ የሥነ-ልቦና፣ የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ እና የፖለቲካዊ ቀውስ የሚያመጣ ሕገ-ወጥ ድርጊት መሆኑን መገንዘብ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ማኅበረሰቡም እነዚህ ሕገወጥ ተግባራት ሲያጋጥሙት ለባለሥልጣኑ በ8864 ነፃ የስልክ መስመር በማሳወቅ የበኩሉን መወጣት እንዳለበት አሳስበዋል።

ወይዘሮ ሙሉእመቤት እንደገለጹት ለነዚህ ሕገ-ወጥ ድርጊቶች መበራከት የአቅርቦትና የፍላጎት አለመጣጣም፣ የቁጥጥር ሥርዓቱ መላላት፣ የሕግ አስፈጻሚ አካላት ተቀናጅቶ አለመሥራት ዋና ምክንያቶች ናቸው።

በተጨማሪም በኅብረተሰብ ደረጃ ለጥራት፣ ለደህንነትና ለቁጥጥር ሥራው ተገቢውን ትኩረት አለመስጠት እና የተቆጣጣሪና የሕግ አካላት በጥቅም መደለል ወይም ፍርሃት እና የኅብረተሰቡ ንቃተ ሕሊና ዝቅተኛ መሆን ምክንያቶች በመሠረታዊነት ተጠቃሽ ናቸው።

በመሆኑም ሕገወጥ አሠራርን በቁጥጥር ብቻ መፍታት ስለማይቻል ኅብረተሰቡ ራሱ የቁጥጥር አካል መሆንና ሕገወጥ አሠራርን መታገል መቻል አለበት ብለዋል።

ማኅበረሰቡ ማንኛውንም ምርቶች ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ፈቃድ ከሰጣቸውና የአገልግሎት ጥራታቸውን በየጊዜው እየተቆጣጠረ ከሚያድስላቸው ሕጋዊ ተቋማት በመግዛት የራስን ብሎም የአካባቢን ጤና መጠበቅ አለበት ያሉት ወይዘሮ ሙሉመቤት፤ ኅብረተሰቡ ሕጋዊ ያልሆኑ አሠራሮች ሲከሰቱ በነፃ የስልክ መስመር ደውሎ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ አሳስበዋል።

# የገና በዓል ገበያ ቅኝት

**መስከረም ሰይፋ**





በዘንድሮ የገና በዓል የምግብና የመገልገያ ሸቀጦች ዋጋ ሊጨምር ይችላል የሚል ሥጋት እንደነበራቸው የሚናገሩት ሸማቾች ሆኖም ከሽንኩርትና ከዶሮ መጠነኛ ለውጥ በስተቀር የዋጋ ለውጥ እንዳልገጠማቸው ይናገራሉ።

የበዓል ገበያ ደርቶ ከሚስተዋልባቸው አካባቢዎች መካከል ሾላና አዲሱ ገበያዎች ይገኙበታል። የዘንድሮው የገና በዓልን ገበያ ለመቃኘት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋዜጠኞች በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙት ሾላና በአዲሱ ገበያዎች ተገኝተው የዶሮ፣ የእንቁላል፣ የሽንኩርት፣ የነጭ ሽንኩርት፣ የቡና፣ የቅቤ፣ የአይብና የቅመማ ቅመም ዋጋንና የገበያውን ሁኔታ ተመልክተዋል።

በሾላ ገበያ የቅቤና የወተት ተዋፅዖ ነጋዴ የሆኑት አቶ ኃይሉ ወልዴ እንደገለጹት፤ በዓምናው የገና በዓል ወቅት በገበያው ውስጥ ተከስቶ በነበረ የእሳት አደጋ ሱቃቸው ተቃጥሎ ኀዘን ውስጥ የነበሩ ቢሆንም በዘንድሮው በዓል ተመልሰው ሱቃቸውን አቋቁመው በሥራቸው ላይ መገኘታቸው ደስታ ፈጥሮላቸዋል።

አቶ ኃይሉ በወተት ተዋፅዖ ምርቶች ላይ በቂ የሆነ አቅርቦት መኖሩንና በዓልን አስመልክቶ ብዙ የሚባል የዋጋ ልዩነት አለመኖሩን ነው የተናገሩት። በአሁኑ ጊዜ ቅቤ በኪሎ ከ750 ብር እስከ 900 ብር፣ አይብ በኪሎ 250 ብር እንዲሁም ቡላ በኪሎ 220 ብር እየሸጡ መሆኑን ገልጸዋል።

በሾላ ገበያ የዶሮ ነጋዴ አቶ መስፍን ጥላሁን በበኩላቸው፤ በዘንድሮው የገና በዓል ጥሩ የሚባል የዶሮ አቅርቦት መኖሩን ገልጸዋል። የዶሮ ዋጋ በዓሉን አስመልክቶ የተለየ የዋጋ ጭማሪ ባያሳይም አብዛኛው ሸማች ይወደዳል የሚል ግምት በመያዙም በዓሉ ከመድረሱ አስቀድሞ መግዛት መጀመሩን ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜ የዶሮ ዋጋ እንደ ዶሮው አይነት የሚለያይ ሲሆን የፈረንጅ የሴት ዶሮ በ 450 ብር፣ የሀበሻ ዶሮ ከ 800 እስከ 900 ብር፣ ክልስ ዶሮዎችን በአንድ ሺ ብር እንዲሁም የፈረንጅ እንቁላል በ 10 ብርና የሀበሻ እንቁላል በ 14 ብር እየተሸጠ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

በአዲሱ ገበያ የሽንኩርትና የቅመማ ቅመም ነጋዴ የሆኑት ወይዘሮ መስታወት አበበ ወቅቱ ሞቅ ያለ ሸመታ የሚጠበቅበት ቢሆንም ካለፉት የበዓል ገበያ ጋር ሲነጻጸር የቀዘቀዘ መሆኑን ገልጸዋል ።

ወይዘሮ መስታወት በአሁኑ ጊዜ የነጭ ሽንኩርት በኪሎ 220 ብር፣ ሽንኩርት በኪሎ 120 ብር፣ ኮረሪማ በኪሎ 360 ብር፣ ኮሰረት በኪሎ 200 ብር፣ ጥቁር አዝሙድ በኪሎ 240 ብር፣ ነጭ አዝሙድ በኪሎ 200 ብር እንዲሁም ቡና ከ350 እስከ 500 ብር እየሸጡ እንደሚገኙ ነግረውናል።

በሾላ ገበያ ሲሸምቱ ያገኘናቸው ወይዘሮ ወርቂቱ ቱፋ በገበያው ውስጥ የሚፈልጉት ነገር ሁሉ ማግኘት መቻላቸውን ገልጸው፤ ነጭ ሽንኩርት አንድ ኪሎ 240 ብር ቀይ ሽንኩርት በኪሎ 120 ብር፣ ኮረሪማ በኪሎ 240 ብር፣ ቅቤ 750 ብር ገዝተዋል።

ከዓምናው በዓል ጋር ሲነጻጸር ሽንኩርት ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ቢያሳይም፤ ሌሎች ምርቶች ላይ ብዙ የሚባል የዋጋ ልዩነት አለማስተዋላቸውን ሸማቿ ተናግረዋል።

በአዲሱ ገበያ ለበዓል የሚያስፈልጉ ነገሮች የገዙት ወይዘሮ አበበች ኃይሌ በበኩላቸው፤ ገበያው የሞቀና ጥሩ የሚባል የምርት አቅርቦት መመልከታቸውን ገልጸዋል። ከዓምናው በዓል ጋር ሲነጻጸርም ከሽንኩርት ውጭ ያሉ ምርቶች ላይ የዋጋ ልዩነት አለማስተዋላቸውን ተናግረዋል።

# ማኅበሩ ለበዓል የሚመጡ ጎብኚዎችን በጥቅል አገልግሎት እንደሚያስተናግድ አስታወቀ

**አመለወርቅ ከበደ**



አዲስ አበባ፡- የገና እና ጥምቀት በዓላት አስመልክቶ የሚመጡ የውጭና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያስችል የጥቅል አገልግሎት አሠራር ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ቱር ኦፕሬተር አሶሴሽን ገለጸ።

በኢትዮጵያ ቱር ኦፕሬተር አሶሴሽን የአባላት ጉዳይ ኃላፊ ወይዘሮ ቤዛ ጥላሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዘንድሮውን የገና እና ጥምቀት በዓላትን አስመልክቶ ለሚመጡ ጎብኚዎች የጥቅል አገልግሎት ተዘጋጅቶ እየተስተናገዱ ይገኛል።

ማኅበሩ ከ270 በላይ አባላት እንዳሉ የገለጹት ኃላፊዋ፤ መጪዎቹን በዓላት ምክንያት በማድረግ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት የሚመጡ የውጭና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ሁሉንም አገልግሎት ከአንድ ቦታ እንዲያገኙ ለማስቻል የጥቅል አገልግሎት እየቀረበ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

በማዕከል በሚመራ አሠራር የራሳቸውን መንገድ ተከትለው ለሚመጡ ጎብኚዎች የመኪና አገልግሎት፣ የሆቴል፣ የምግብና የጉብኝት እንዲሁም ተያያዥ አገልግሎቶችን በተቀናጀ መልኩ በጥቅል አገልግሎት እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

ከባለሙያዎች ልምድ ማነስ ጋር ተያይዞ ከጎብኚዎች ለሚነሳ ቅሬታ ችግሩን ለመቅረፍ እንዲቻል ማኅበሩ በየጊዜው ሥልጠና እየሠጠ መሆኑን ወይዘሮ ቤዛ አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ቱር ኦፕሬተር አሶሴሽን አባላት ከጎብኚዎች የሚያቀርቡት አገልግሎት ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን መስፈርቶችና ደረጃዎች በጠበቀ መልኩ እንዲሠሩ ይደረጋል ያሉት ወይዘሮ ቤዛ፤ መስፈርቱን ያላሟላ አባል ከአባልነት እንዲወጣ ይደረጋል ሲሉ ገልጸዋል።

ማኅበሩ በዓለም ደረጃ ኢትዮጵያን ገጽታ በመገንባት ላይ ያለ ተቋም ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ በዚህም ዓለም አቀፍ ዝግጅቶችን በመሳተፍ የቱሪዝም መዳረሻዎችን እያስተዋወቀ መሆኑንና በሀገር ውስጥም በስፋት የማስተዋወቅ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የቱሪስት ፍሰቱን ለመጨመር በማኅበራዊ በሌሎች የሚዲያ አማራጮች የማስተዋወቅ ሥራ በስፋት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የጎብኚዎች ቁጥር እንዳይቀንስ የአባላትን ቁጥር ለመጨመርና አባላቱ የማይስ ቱሪዝምን ወይም የተለያዩ ስብሰባዎችን፤ ኤግዚቢሽኖችንና በዓላት ላይ ሰፊ ትኩረት አድርገው እንዲሠሩ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ ያሏትን ሃይማኖታዊና ባሕላዊ እሴቶች ለማየት የሚመጡ ጎብኚዎች በተጓዳኝነት ተፈጥሯዊ ቅርሶችንም እንዲጎበኙ ይደረጋል ያሉት ኃላፊዋ፤ የጎብኚዎችን የቆይታ ጊዜ በማራዘም የውጭ ምንዛሪ ገቢን ለማሳደግ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

# ኢትዮጵያ የባሕር በር ማግኘት የሚያስችላትን ስምምነት መፈራረሟ ትልቅ ሀገራዊ ስኬት ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የባሕር በር ማግኘት የሚያስችላትን ስምምነት ከሶማሌ ላንድ ጋር መፈራረሟ ትልቅ ሀገራዊ ስኬት እንደሆነ ኢፕድ ያነጋገራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ።

የአዲስ አበባ ነዋሪ አቶ ተሻለ ጉራራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሆና ለብዙ ዓመታት ስትቸገር ቆይታለች። ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ የባሕር በር የምታገኝበትን ስምምነት መፈጸሟ ለወደፊት እድገት ወሳኝ ነው። ይህም ዋና የሚባለውን ችግር የሚፈታ በመሆኑ ስምምነቱ አግባብነት ያለውና ትክክለኛ ነው።

የባሕር በር በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳለው ያነሱት አቶ ተሻለ፤ መድኃኒት፣ መሣሪያ፣ ማዳበሪያ፣ ነዳጅ እና ሌሎችም ጠቃሚ ግብዓቶች ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ያስችላል። ይህም ኢኮኖሚያዊ እድገትን ያፋጥናል ብለዋል።

እንደ አቶ ተሻለ ገለፃ፤ የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ የሀገሪቱን ታሪካዊ ሥልጣኔ ለመመለስ ያስችላል። ይህ ደግሞ ሀገሪቱ ከኃያላን ሀገራት ተርታ የምትሰለፍበትን ሁኔታ ያመቻቻል። የኢትዮጵያና የሶማሌላንድ ስምምነቱ ተግባራዊ እንዳይደረግ ሀገራት የሚረባረቡት ኢትዮጵያን ለመጉዳትና እንዳታድግ ለማድረግ እንደሆነ ገልጸዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉዳዩን በሰከነ መልኩ እየተመለከተ ለሀገር ጥቅም መሥራት እንዳለበትም ጠቁመዋል።

ወጣት ሔለን ግዛቸው በበኩሏ፤ የኢትዮጵያና የሶማሌላንድ መንግሥታት ኢትዮጵያ የባሕር በር ማግኘት በምትችልበት ጉዳይ የመግባቢያ ሰነድ መፈራረማቸው




**አቶ ተሻለ ጉራራ**



**ወጣት ደሴ አድምጠው**

ለሁለቱም ሀገራት ትልቅ ስኬት ነው ብላለች።

የባሕር በር ባለቤት መሆን ለኢኮኖሚ እድገት



**ወጣት ሔለን ግዛቸው**



**ወጣት ሳሮን መስፍን**

እንዲሁም የፖለቲካ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ላይ ልዩነት እንዳለው የገለጸችው ወጣት ሔለን፤ ኢትዮጵያ ለዘመናት ስር ሰድዶ የቆየውን ድህነት ለማሸነፍ እና ለቀጣናው ሠላም የራሷን አሻራ ለማሳረፍ የባሕር በር ያስፈልጋታል ብላለች።

የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ የሰጥቶ መቀበልን እና የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ መሆኑን የገለጸው ወጣት ደሴ አድምጠው በበኩሉ የተፈፀመው ስምምነት የዓለም አቀፍ ሕጎችን መሠረት በማድረግ ነው ብሏል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በፍጥነት እያደገ ከመሆኑ እና የሕዝብ ቁጥርም እያሻቀበ በመሆኑ የባሕር በር ማግኘት ለሀገሪቱ ግድ እየሆነ መጥቷል ያለው ወጣት ደሴ፤ የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ እየቀረበ ያለው የጎረቤት ሀገራት አብሮ የማደግ መርሕን በጠበቀ እና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ነው ብሏል።

ወጣት ሳሮን መስፍን በበኩሏ፤ የኢትዮጵያ ወደብ ማግኘት ከራሷ ጥቅም አልፎ ለቀጣናው ጭምር ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ተናግራለች።

ጎረቤት ሀገራት ጭምር አጀንዳውን እንደራሳቸው አጀንዳ በመውሰድ ለነገው የጋራ እድገት ከጎናችን ሊቆሙ እንደሚገባም ጠቅሳለች።

የኢትዮጵያ የባሕር በር መጋራት የምሥራቅ አፍሪካን ቀጣናዊ ትስስር ያጠናክራል፣ የተሻለ የንግድ ትስስር እና የኢኮኖሚ እድገት ፍጥነትን ይጨምራል ብላለች።

የቀጠናው ሀገራት የኢትዮጵያን የባሕር በር ጥያቄ በአዎንታዊ መልኩ መገንዘብና ለተፈፃሚነቱ በጋራ መሥራት አለባቸው ያለችው ወጣት ሳሮን፤ አፍሪካውያን የራሳቸውን ምርት እንዲለዋወጡ እና በቀላሉ እንዲገናኙ ያግዛል ስትል ገልፃለች።

ከፍተኛ የሆነውን የውጭ ምንዛሪ ወጪን ለመቀነስ ያለው ፋይዳም ቀላል የሚባል አይደለም ብላለች።

# ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ቀንድ ሠላም ትልቅ ሚና ተጫውታለች

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ሠላም እንዲሰፍን የሠራችና አሁንም እየሠራች ያለች ሀገር መሆኗን ዲፕሎማት ገለጹ።

አንጋፋው ዲፕሎማት አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ብሎም በአፍሪካ ትልቅ ስፍራ የሚሰጣት ሀገር ናት። በቀጣናው መጫወት ያለባት ሚናም አለ። የምትከተለው ዲፕሎማሲም በኢኮኖሚና ፖለቲካ ጉዳዮች ተቀራርቦ መሥራትና ችግሮች ሲኖሩ ተቀራርቦ መፍታት ላይ ያተኮረ ነው።

ኢትዮጵያ የራሷን ችግር ብቻ ሳይሆን የጎረቤት ሀገራትን ችግር ጭምር በመፍታት የምትታወቅ ሀገር ናት ያሉት አምባሳደር ጥሩነህ፤ በቀጣናው ሠላምና ፀጥታ እንዲሁም በኢኮኖሚ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመፍታት አካባቢውንና ራሷን በማረጋጋት ለዓለም ፀጥታና መረጋጋት የበኩሏን ሚና እየተጫወተች ትገኛለች ብለዋል። አሁንም በምሥራቅ አፍሪካ ሠላም እንዲሰፍን በተለያዩ አግባቦች እየሠራች መሆኗን ገልጸዋል።

የዓለም አቀፍ ሕግ ሀገራት በሠላም እንዲኖሩ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ዓላማ አለው። ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገራት ጋር በትብብር የዓለም አቀፍ ሕጋጋትን እያከበረች ትገኛለች። ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ሠላም እንዲሰፍን ጉልህ ሚና መጫወቷንም ዓለም እንደሚመሰክር ተናግረዋል።

በዋናነት የጸጥታ ችግር በሚከሰትበት ጊዜ ሠራዊቷን በመላክ ሠላምን የሚያደፈርሱ አካላትን በመቆጣጠር የምታደርገው ሚና የሚታወቅ ነው ያሉት አምባሳደር ጥሩነህ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንኳን የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ ኃይል ሶማሌ ሀገር ሆና እንድትኖር፣ በደቡብ ሱዳንና በሰሜን ሱዳን መካከል የነበረው ግጭት ሠላም እንዲሆን እና በርካታ ሥራዎችን ሠርቷል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሚና የሌለበት የሠላም ሁኔታ በምሥራቅ አፍሪካ አለ ብዬ አልገምትም ያሉት አምባሳደር ጥሩነህ፤ ይህም የዓለም አቀፍ ሕግና መርሕን ማስፈጸም ማለት መሆኑን ገልጸዋል፤ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲ ያላትን ሚና ለማስጠበቅ የሀገር ውስጥ ሠላምና ፀጥታን በቶሎ ማረጋጋት እንደሚያስፈልግም አፅንዖት ሰጥተዋል። ይህም ኢትዮጵያ በከፍታዋ ልክ እንድትጓዝ ያደርጋታል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

የቀድሞ ዲፕሎማትና የፖለቲካ ተንታኝ ፕሮፌሰር ብሩክ ኃይሉ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ በእኩልነት፣ በሀገራት ውስጣዊ ጉዳዮች ያለመግባትና በሀገራት መካከል ችግሮች ሲከሰቱ በሠላም መፍታት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ጠቁመው፤ ኢትዮጵያ በታሪኳ በራሷ ግፊት ከየትኛውም ሀገር ጋር ወደግጭት የገባችበት ጊዜ እንደሌለም ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በጐረቤት ሀገር ሱዳን የተቀሰቀሰውን አለመረጋጋት እልባት ከመስጠት አኳያም የአንበሳውን ድርሻ በመውሰድ ጥረት ስታደርግ መቆየቷን የጠቀሱት ፕሮፌሰር ብሩክ፤ በሱዳንና በደቡብ ሱዳን መካከል



**አምባሳደር ጥሩነህ ዜና**

የተቀሰቀሰው ግጭት ወደሠላም እንዲመጣ ያበረከተችው አስተዋፅዖም ከፍተኛ እንደነበር ተናግረዋል።

ፕሮፌሰር ብሩክ እንደገለጹት፤ የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት ባለሥልጣን (ኢጋድ) እና ኢትዮጵያ በቀጣናው ሠላም የሚሰፍንበት ሁኔታን ለመፍጠር ተንቀሳቅሰው ውጤት አምጥተዋል። እናም እ.ኤ.አ. በ1992 ኢጋድ ለቀውሱ እልባት ለመስጠት በናይሮቢ ባካሄደው የሠላም ስምምነት ላይ ኢትዮጵያ ውጤታማ ድል ማስመዝገብ ችላለች ብለዋል።

ለዘመናት በእርስ በርስ ግጭት የዘለቁት የሱዳን መንግሥትና የደቡብ ሱዳን አማፂያን የሠላም ስምምነት



**ፕሮፌሰር ብሩክ ኃይሉ**

ላይ መድረስ ችለዋል። ለዚህ ውጤት ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ሚና የጐላ ነበር። ምክንያቱም ሁለቱ ወገኖች የሁሉም ነገር መሠረት የሆነው የሠላም ስምምነት ላይ መድረሳቸው ቀጣዩን ሁኔታ ብሩህ እንዳደረገው ተናግረዋል።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ሀገሪቱ አንዱን ቀውስ ለመፍታት ያደረገችው ጥረት የተሳካ ቢሆንም፤ ሌላ ቀውስ መከተሉ አልቀረም። በዚህም ላይ ኢትዮጵያ ጉልህ ሚና እየተጫወተች ትገኛለች ያሉት ፕሮፌሰር ብሩክ፤ አሁን ላይ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲና በኢኮኖሚ እያስመዘገበች ያለችው ውጤት ተሰሚነቷን ጨምሮታል ብለዋል።

# ለሸማቹ እፎይታ የሰጡ የእሁድ ገበያዎችና ባዛሮች

**ማሕሌት ብዙነህ**

በበዓላት መቃረቢያ ወቅት ለበዓሉ የሚሆኑ ምግቦችንና አልባሳትን መሸመትና መግዛት የተለመደ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኑሮ መወደድ ቢስተዋልም ሁሉም ማኅበረሰብ እንደአቅሙ የሚያስፈልገውን ለመሸመት ወደ ተለያዩ የገበያ ማዕከላት ያቀናል።

በአዲስ አበባ ከተማ በርካታ የገበያ ማዕከላት እና ምርት መሸጫ ሱቆች የሚገኙ ሲሆን የከተማው ንግድ ቢሮ የምርት ዋጋን ለማረጋጋት እየተገበረ ያለው እሁድ ገበያ እና ባዛሮችም በዓላትን ምክንያት በማድረግ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ለሸማች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

ወይዘሮ እጅጋየሁ ገብረኢየሱስ በአራዳ ክፍለ ከተማ የእሁድ ገበያ ሲገበያዩ ነው ያገኘናቸው። በፊት ቅዳሜ እና እሁድ ብቻ ሲካሄድ የነበረው ገበያ በዓላትን ምክንያት በማድረግ ከሰኞ እስከ እሁድ ድረስ መደረጉ የሚያስፈልጋቸውን ምርቶች በስፋት እና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ እንደረዳቸው ተናግረዋል።

በየካ ክፍለ ከተማ በተዘጋጀው የእሁድ ገበያ ላይ ሲሸምቱ ያገኘናቸው ወይዘሮ ኃያል ገዳሙ እንደሚናገሩት የሚፈልጓቸው ምርቶችን ከሌሎች ገበያ ቦታዎች ይልቅ በባዛሮችና በሰንበት ገበያዎች ቅናሽ እንዳላቸው ይናገራሉ። በተለይም ሽንኩርት በሌላ አካባቢ ይገዙት ከነበረው የ 30 ብር ቅናሽ አለው ብለዋል።

የአትክልት ምርት በመሸጥ ላይ ያገኘናቸው ወይዘሪት ሰሚራ ከድር፤ በሰንበትና በባዛር ገበያዎች እንደ ሽንኩርት እና ቲማቲም የመሳሰሉ ምርቶችን በቀጥታ ለሸማቹ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ላይ እንደሆኑ ተናግረው፤ በተለይም በዓልን ምክንያት በማድረግ ምርቶችን በስፋት እያቀረቡ እንደሆነ አስታውቀዋል።

በባዛሮች ላይ የተለያዩ የአትክልት፣ የአልባሳት፣ የቅባት እህሎች፣ የማር እና ወተት ውጤቶች ለገበያ የቀረቡ ሲሆን በተለይም በእሁድ ገበያዎች ላይ ለበዓል አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች እየተሸጡ ነው።

በገበያዎቹ ሽንኩርት አንድ ኪሎ 105 ብር፣ የሀበሻ እንቁላል 10 ብር የፈረንጅ 9 ብር ከ50፣ ሚጥሚጣ ግማሽ ኪሎ 200 ብር፣ ድንች ኪሎ 30 ብር፣ ቲማቲም ኪሎ 45 ብር እየተሸጠ እንደሆነ በቅኝታችን አስተውለናል።

የየካ ክፍለ ከተማ ንግድ ጽሕፈት ቤት የግብይት ማስፋፊያ ቡድን መሪ አቶ ሃይማኖት ተስፋዬ እንደገለጹት፤ በክፍለ ከተማው 22 የእሁድ ገበያ እና አንድ ባዛር አለ። በበዓሉም በርካታ ግብዓቶች በጥራት እንዲገቡ በማድረግ ከውጭ የተሻለ ዋጋ እየቀረበ ነው።

እሁድ ገበያ ላይ ከሚቀርቡት ሽንኩርትና ድንች በተጨማሪ 100 ሺህ በላይ የእንቁላል፣ ዶሮ፣ አይብ የመሳሰሉ ለበዓል አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በብዛት እንዲገቡ ተደርጓል። አላስፈላጊ የዋጋ ጭማሪ እንዳይኖርም የግብዓቶቹን ዋጋ ከመለጠፍ ጀምሮ በባለሙያዎች ቁጥጥር ይደረጋል ብለዋል።

አቶ ሃይማኖት ሸማቹ ጋር የምርት አለመኖር እና ዋጋ ጭማሪ በሚል እሳቤ ስጋት እንደሚስተዋል ጠቅሰው፣ ምርቶች በበቂ ሁኔታ እንዳለ እና እስከ ዛሬ ከሰዓት ድረስ ለሸማቾች መድረስ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ ቢኒያም ምክሩ በበኩላቸው መጪውን የገና በዓል መነሻ በማድረግ ግብረሃይል በማቋቋም አስፈላጊ የሆኑ ምርቶች በስፋት ወደ ከተማው እንዲገቡ እየተሠራ ነው ብለዋል።

መደበኛ የገበያ ሥርዓቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዓሉን ምክንያት በማድረግ በከተማው በሚገኙ 172 የእሁድ ገበያዎች ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ድረስ ግብይት እንዲፈፅሙ ከማድረግ በተጨማሪ አምስት ባዛሮች እንደተዘጋጁ አስታውቀዋል።

የተዘጋጁት የመገበያያ ቦታዎችም በቂ የምርት አቅርቦትና የገበያ ተደራሽነትን በማስፋት ምርቶቹን ከመደበኛ ባነሰ በቅናሽ ዋጋ በመሸጥ ዋጋ የማረጋጋት ሥራ እየተሠራ ነው። የአቅርቦት ችግር እንዳይኖር እና መዲናዋ በቂ ምርት እንዲገባ ከክልሎች ጋር በቅንጅት ተሠርቷል ብለዋል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹የበዓሉ ዋና ዓላማ ልምድ መፈጸም ሳይሆን እግዚአብሔር ያደረገልንን መልካምነት በተግባር ማሳየት ነው››

*መምህር ዳንኤል ሰይፈሚካኤል*
*በመምሪያ ኃላፊ ደረጃ የሊቃውንት ጉባኤ*

**ስምስም መንግሥቱ**

የዛሬው የዘመን እንግዳችን መምህር ዳንኤል ሰይፈሚካኤል ይባላሉ፡፡ የተወለዱት በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ ነው፤ ይሁን እንጂ እድገታቸው አዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡ እርሳቸው፣ ዘመናዊውንም ሃይማኖታዊውንም ትምህርት ተምረዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የሚሰሩት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መንበረ ፓትሪያሪክ የሊቃውንት ጉባኤ ውስጥ ነው፡፡ በቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲም በመምህርነት ያገለግላሉ፡፡ ሆኖም ትምህርታቸውም ሥራቸውም ሃይማኖቱ ላይ ያተኩራል፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በቲዮሎጂ፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ ያጠናቀቁት በቋንቋ ሥነ ልሳን በሙዚየም ጥናት ነው። አሁን ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ፊኒሎጂ የሚባለውን የትምህርት ዘርፍ በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡

መምህር ዳንኤል ከመደበኛ ሥራቸው በተጨማሪ በጥናትና በተለያዩ ሥራዎች ላይም ተሳትፎ አላቸው። በምሥራቅ አፍሪካ የማኅበረሰብ ጥናት ቡድን ውስጥ አባል በመሆን ሰርተዋል፡፡ የኢትዮጵያንና ከኢትዮጵያ ጋር ትስስር ያላቸውን የመካከለኛና የሩቅ ምሥራቅ እንዲሁም የሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ ታሪክ ጋር በተያያዘ፤ በባህልና በሥነ ጥበብ ዙሪያ መጣጥፎችንም በማዘጋጀት ለሕትመት አብቅተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዋና ሙዚየም ቤተመዛግብትን አደራጅተዋል፡፡ በመገናኛ ብዙሃን ዘርፍም ሃይማኖታዊ መልእክት የሚያስተላልፍ የቴሌቪዥን ጣቢያ በማቋቋምና በመምራት ለአምስት ዓመታት አገልግለዋል። የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ውስጥም እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ መምህሩ፣ በሃይማኖቱ ውስጥ ሰፊ አበርክቶ ያላቸው ናቸው፡፡ እኛም ከዛሬው በመምሪያ ኃላፊ ደረጃ የሊቃውንት ጉባኤ ከሆኑት እንግዳችን ከመምህር ዳንኤል ጋር የገና እና የጥምቀት በዓላትን መሠረት አድርገን ቆይታ ያደረግነው ሲሆን፣ ስለ ሰላምና ተያያዥ ጉዳዮችም አንስተን የሚከተለውን አጠናቅረን አቅርበናል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- መምህር በቅድሚያ ገና ምንድነው? ስለ ጥምቀትም አያይዘው ያብራሩልን?**

**መምህር ዳንኤል፡-** የገና እና የጥምቀት በዓላት መሠረታቸው ሃይማኖታዊ ነው፡፡ በዓላቱ በቤተክርስቲያን አበይት ወይንም ዋና በዓላት ከሚባሉት በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ ዋና በዓላት የሚያሰኛቸው በሃይማኖት ውስጥ ከሚሰጡት መንፈሳዊ ትርጉምና ዋጋ እንዲሁም በዓላቱን በማክበር ብቻ የማይተካ ዋጋ ስላላቸው፣ የሃይማኖታዊ ትምህርት መሠረትም ስለያዙ ነው፡፡

የጌታችን መድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የገና በዓል፤ የአምላክ ሰው መሆን ነው፡፡ አምላክ ሰው ሆኖ የሰው ልጅን ያዳነበት ነው፡፡ ጥምቀት ደግሞ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች የምንሆንበትን ሥርዓትና ዘላለማዊ የሆነ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምንወርስበት ነው። በዓሉን የምናከብረው የድህነት መንገድ የመሠረተልን ስለሆነ ነው፡፡ የበዓላቱ የመከበሪያ መሠረት መጽሐፍ ቅዱስና የሃይማኖት መዛግብት መሆናቸውም መዘንጋት የለበትም፡፡ በአጠቃላይ ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊና ማኅበራዊ እሴት ያላቸው ናቸው፡፡

ገና ማለት የግሪክ ቋንቋ ነው፡፡ ትርጉሙም ልደት ማለት ነው፡፡ አዲስ ኪዳን መጽሐፍ ወደ ግዕዝ ቋንቋ የተተረጎመው ከግሪክ ነው፡፡ ከግሪክ ወደ ግዕዝ የተረጎሙት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አንዳንድ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ ያሉ ቃላትን እንዳለ አስቀምጠዋል፡፡ ከነዚህ ቃላት ውስጥ ገና አንዱ ነው፡፡ ገና ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅን ለማዳንና ዘላለማዊ ሕይወት ለመስጠት ሲል ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ የተወለደበት ቀን ነው፡፡ በምድረ እስራኤል በቤተልሄም በከብቶች በረት ውስጥ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ፡፡ መላእክት ልደቱን ያመሰገኑበት፣ እረኞችም በተወለደበት የከብት በረት ውስጥ ተገኝተው የጎበኙት፣ ሰባሰገል ጠበብት ነገሥታት እጅ መንሻ ያቀረቡበት፣ ፍጡራን ሁሉ የተደሰቱበት በመሆኑ ቤተክርስቲያን ትልቅ ክብርና ቦታ የምትሰጠው በዓል ነው፡፡

ባዕለ ጥምቀትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፈለገ ዮርዳኖስ በመጥምቁ በእደ ዮሐንስ እጅ የተጠመቀበት ነው፡፡ መጠመቁ እግዚአብሔርን አምነው የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስና ዘላለማዊ ሕይወት እንዲኖራቸው የሚፈልጉ የእግዚአብሔር ልጆች ለመባል የሚያችል ነው፡፡ ከገና በዓል ጀምሮ የሚከበረው ዘመን ደግሞ ዘመነ አስተርዮ ይባላል፡፡ በዓሉ እስከ ጥር መጨረሻ ድረስ ይዘልቃል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዓላቱ ሃይማኖታዊ ይዘት ቢኖራቸውም፤ በተለይ የጥምቀት በዓል ማኅበራዊ ይዘታቸው ያመዝናል ይባላልና ስለዚህ ሁኔታም ቢገልጹልን?**

**መምህር ዳንኤል፡-** በዓላቱ ሃይማኖታዊ ናቸው። መሠረታቸውም መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ይሄን እውቅና መስጠት አለብን፡፡ የሚከበረውም በኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና በአማኞችዋ ዘንድ ነው፡፡ ሆኖም ግን አማኙ የራሱ የሆነ ማኅበራዊ አገልግሎት አለው። የኀይማኖቱ ማንነት በማኅበራዊ ሕይወቱ ውስጥ ይገለጻል፡፡ ሃይማኖታችንን ስናከበር ብቻችንን ሳይሆን፤ በጉባኤ፣ በማህበር በአንድ ተሰባስበን ነው። በማኅበራዊ ጎዳናችን ውስጥ ያሉ ግን ደግሞ የሌላ እምነት ተከታይ የሆኑትንም ወገኖቻችንን በማሳተፍ አብረውን እንዲያከብሩ እናደርጋለን፡፡

በተለይም የጥምቀት በዓል በአደባባይ ስለሚከበር ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎችና የዓለም ሀገራት የሚመጡ ሁሉ የሚካፈሉበት ለማሰባሰብ እድል የሚሰጥ በዓል ነው፡፡ ቤተክርስቲያን የምታስተምረው ሃይማኖታዊ ትምህርትና መልእክትም ብዙዎችን በአንድ ጊዜ ለመድረስና የመሰማት እድል አለው፡፡

በዓሉን የምናከብረው እንዲያው ልምድ ለመፈጸም ብቻ አይደለም፡፡ የሰላምን ዋጋ፣ የአንድነትን አስፈላጊነት፣ ከማስመሰል የወጣን መሆናችንን፣ የምንከባበር፣ የምንሰማማ መሆናችንና እነዚህ ሁሉ መልካም የሆኑ እሴቶች እንዳሉን ቤተክርስቲያን በአደባባይ ታስተምራለች፡፡ ተከታዮቹም ይህን የመልካም እሴት የሆነውን ማንነት ተላብሰው የሰሙትን ወይንም የተማሩትን በተግባር እንዲተገብሩት ምክርም ይሰጣቸዋል፡፡ ይተገብሩታልም ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የተጣላ ታርቆ፣ የቀማ መልሶ፣ ያስቀየመ ወይንም የበደለ ክሶ፣ እርስበርስም በመዋደድ በዓሉን ማክበር ግዴታ እንደሆነም ቤተክርስቲያን አጥብቃ መልእክት ታስተላልፋለች፡፡ ትገስጻለችም፡፡

ጥምቀት ከሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ጎን ለጎን ማኅበራዊ ኩነቱ የሚያመዝንበት የተለያዩ ምክንያቶች አሉት። አንዱ ከወቅት ጋር የሚያያይዘው ነው። ገበሬው ሰብሉን ከማሳው ሰብስቦ እህሉን ጎተራ የሚያስገባበት ወቅት በመሆኑ ከእርሻ ሥራ ፋታ ያገኛል፡፡ ወደ ማኅበራዊ ሕይወቱ በመመለስ ለሠርግ፣ ለማህበር ድግስና ለተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ጊዜ ይሰጣል፡፡ በዓላቱም በምግብና በመጠጥ ስለሚታጀቡ ደግሶ በዚህ አጋጣሚ ዘመድ ወዳጅ ጎረቤት ጠርቶ በጋራ ደስታውን ያሳልፋል፡፡

የጥምቀት በዓል በአጠቃላይ ሰው ከሰው የሚገናኝበት ነው፡፡ በሥራና በተለያየ መንገድ ተራርቆ የቆየ ዘመድ ከወዳጁ ይገናኛል፡፡ ወጣቶችም አዲስ ኑሮ ለመመስረት እርስበርስ ለመተዋወቅ እድል ያገኛሉ፡፡ የተለያየ አካባቢ የባህል አለባበስ፣ የባህላዊ አጨፋፈር ስልት፣ ታሪክና ወግ የሚታየው በዚህ በጥምቀት የአደባባይ በዓል ላይ ነው፡፡ ሁሉም በሚያስደስተው ነገር አምሮ፣ ደምቆና ተዘጋጅቶ ስሜቱን የሚገልጽበትና አምልኮቱንም የሚፈጽምበት ነው፡፡

በዚህ አጋጣሚም አንዱ የሌላውን ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ ለማወቅ ያስችለዋል፡፡ አድናቆቱን በመግለጽ አብሮነቱን ያሳያል፡፡ እንዲህ ባለው ሁኔታ ሁሉም



ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን አብሮ ይፈጽማል፡፡ ተጫውቶና ተደስቶም ይውላል፡፡ በዓሉን ሲጨርስም እንዲሁ አይለያይም ለከርሞ በሰላም አድርሷቸው በድጋሚ ተሰባስበው በዓሉን ለማክበር እንዲያበቃቸው አንዱ ለሌላው ቸር ተመኝቶ ነው የሚለያዩት፡፡

የተጣሉ ሰዎችም እርቅ የሚፈጽሙት በዚህ የበዓል አጋጣሚ ነው፡፡ በማስታረቅ ሽምግልና ውስጥ የሚገቡም ሰዎች ዛሬ ካልታረቃችሁ መቼ ልትታረቁ ነው በማለት ነው እንዲታረቁ ተጽእኖ የሚያሳድሩት። የሰው ንብረትም ወስዶ ያልመለሰ ካለ አሁን ሞልቶልሀል በል መልስ በማለት ገስፀውና መክረው እንዲመልስ ያደርጋሉ፡፡ በዓሉን በፍጹም የልቦና ንጽህና እንዲያከብሩ አበክረው ይሸመግላሉ፡፡

ይህ ወቅት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሆነበትን የምንዘክርበት በመሆኑ፤ ቤተክርስቲያን የምታስተምረው ከፀብና ከጥላቻ ርቀን እርስ በርስ መዋደድ እንዳለብን ነው፡፡ ለዚህም ነው የተለያየ ባህልና ቋንቋ ያላቸው ሰዎች ለአንድ ዓላማ በአንድ ስፍራ ተገናኝተው በጋራ የሚያከብሩት፡፡ ይሄ በሩቅ ለሚያይ ሰው ያስደንቅ እንደሆን እንጂ አያስተችም፡፡ ብዝሀነት የሚታይበት በዓል ነው፡፡

ጥምቀት በማይዳሰስ ቅርስነት በተባበሩት የዓለም መንግሥታት የሳይንስ፣ ባህልና ትምህርት ድርጅት (ዩኔስኮ) ሲመዘገብ በቅድመ መረጃ አሰባሰብ ሂደት፤ በዓሉ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚፈጥረው የእርስበርስ ግንኙነት፣ ሰላማዊና በሰዎች መካከል ልዩነት የማይፈጥር መሆኑ በሌሎች አግራሞትና አድናቆት ያገኘ እንደነበር እንዲመዘገብ በነበረው የቅድመ ዝግጅት ሥራ ውስጥ በነበረኝ ሚና አስታውሳለሁ፡፡

የገና በዓልም ቢሆን ምን ያህል ሰላማዊ የሆነ በዓል እንደሆነ አንዱ ማሳያ፤ በውሃ ቀጠነ ቁጣ የሚቀናቸው አንዳንድ ሰዎች እንኳን የገና እለት ከቁጣቸው በረድ ይላሉ፡፡ “ለገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ” እየተባለ በባህላዊ ጨዋታ የሚገለጸውም በዓሉ ነፃነት ያለው መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ ለማኅበረሰቡ ደግሞ ትልቁ ነገር ሰላም ነው፡፡

የጥምቀት ከተራ ታቦታት ከማደሪያቸው ወጥተው በአንድ ስፍራ በድንኳን ስለሚያድሩ የእምነቱ ተከታዮች ወይም ምእመን አጅበው የወሰዱትን ታቦት ለብቻው ጥለው አይመለሱም፡፡ በታቦታት ማደሪያ ታቦታቱን አጅቦ በድንኳን ውስጥ አብረው ያድራሉ፡፡ ያ በዚያ የተሰባሰበው ምእመን እርስ በርሱ አይተዋወቅም፡፡ ከተለያየ ቦታ የተሰባሰበ ነው፡፡ ነገር ግን አንዱ ለሌላው ፍቅርና አክብሮት ሰጥቶ የያዘውንም ምግብ በጋራ ተቋድሶ የሄደበትን ዓላማ በጋራ ይፈጽማል፡፡ አንዱ ሌላውን የሚያየው እንደስጋት ሳይሆን፤ እንደበረከት ነው፡፡ እንዲህ ሰላምን የሚፈጥር አውድ ወይም መድረክ ትልቅ ቦታ ሊሰጠው ይገባል፡፡

በሃይማኖቱ በኩል ደግሞ፤ እንዲህ ከተለያየ አቅጣጫ ለተሰበሰበው ማኅበረሰብ ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጡ ትምህርቶች ይሰጣሉ፡፡ በአደባባይ ከሚሰጡ ትምህርቶች ከብዙ በጥቂቱ ስናነሳ፤ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በአደባባይ ሲያስተምር ወደ እርሱ ሄደው ትምህርቱን የሚከታተሉ ሰዎች ነበሩ፡፡

የሮም የመንግሥት ወታደሮች ወደ እርሱ ሄደው እኛ ምን እናድርግ ይሉታል፡፡ ግፍ አትስሩ፣ የናንተ ያልሆነውን አትንኩ ይላቸዋል፡፡ ቀራጮች (ግብር ሰብሳቢዎች) እንዲሁ ወደርሱ ሄደው እኛ ምን እናድርግ ይሉታል፡፡ ከተፈቀደው ግብር በላይ አትውሰዱ፣ ሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች እኛ ምን እናድርግ ይሉታል፡፡


ሁለት ያለው አንዱን ለሌላው ያካፍል፣ ቸር ይሁን፣ መተዛዘን ይኑር፣ ጠማማው ቀጥ ይበል፣ ሻካራው ይለስልስ ብሎ ይላቸዋል፡፡ መልእክቱ ሻካራና ጉርብጥብጥ የሆነ አስተሳሰብ ያለው ግለሰብም ሆነ ማኅበረሰብ ይለስልስ ነው፡፡ ፍትህን፣ ለእያንዳንዱ እንደሚገባው መኖርን ማስተማር ነው፡፡ ይሄ መልእክት ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን፤ ማኅበራዊ ይዘት ያለው ነው። በየዘመኑ ላለው ትውልድ እንዲህ በጎነት ያላቸው ትምህርቶች እየተሰጡ መልካም የሆነ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር በማድረግ ቤተክርስቲያን ኃላፊነቷን ትወጣላች፡፡

**አዲስ ዘመን፡-በዓሉ ከደስታና ፈንጠዚያ ባለፈ ሰዎችን በመልካም ነገር የሚያንጹ ትምህርቶችም የሚሰጡበት እንደሆነ ገልጸውልናል፡፡ በትምህርት የሚሰጡትን በጎ ነገሮች ሆኖ መገኘት ላይ ያለው ነገር ምን ይመስላል? አሁን ላይ ሀገራችንን የገጠማት የውስጥ ችግር በሃይማኖት ከታነፀ ማኅበረሰብ ያፈነገጠ ነገር የለውም? እዚህ ላይ**

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ‹‹የበዓሉ ዋና ዓላማ ልምድ መፈጸም...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ



**ምን ይላሉ?**

**መምህር ዳንኤል፡-** በቤተክርስቲያን የሚሰጡት ትምህርቶች የሰው ልጅ የተማረውን በሕይወቱ እንዲተገብረው ነው:: ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት፤ ሰላምን፣ አንድነትን፣ መከባበርን፣ ፍቅርን፣ መዋደድን፣ ርህራሄን፣ ግፍ ጠል መሆንን ትምህርት ሲሰጥ ትምህርቱን የተከታተለውም ይህን እንዲተገብረውና ሆኖ እንዲገኝ ነው የሚፈለገው:: ሰው ይሄን ቢያደርግ በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ ተከብሮ እንደሚኖር፣ ፈጽሞ ባይገኝ ግን ከሰውነት እንደሚጎድል ነው ቤተክርስቲያን አጥብቃ የምታስተምረው::

ሆኖ መገኘት ሌላው ብቻ እንዲያደርገው አይደለም። እኔ አስተማሪ ብሆንም መልእክቱን ሳስተላልፍ ከእኔ ጀምሮ መተግበር ይጠበቅብኛል። የምንማረውንም በሕይወት የማንተገብር ከሆነ ከዓለማዊው ቲአትር ተለይቶ አይታይም:: እውነተኛ የሆነ መንፈሳዊ አከባበር አይደለም ማለት ነው::

ቤተክርስቲያን የምታስተምረው ስዕላዊ በሆነ አገላለጽ ሰዎች ሊተገብሩት በሚያስገድድ ሁኔታ ነው:: አምላክ ወደዚህ ዓለም የመጣው የሰውን ልጅ ከሞት ወደ ሕይወት ለማምጣት፣ ሰላምንም ለማስፈን ነው። እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገልንን ነገር በእኛ ሕይወት ውስጥ ልንተረጉም የምንችለው እኛ ያንን በተግባር ስንተረጉም ነው:: ያንን ካልሆንን ከእግዚአብሔር የምናገኘውን ዋጋም ደስታም እናጣለን:: የደካማነት መገለጫ ተደርጎም ይወሰዳል። እውነተኛውን የሃይማኖት ሥርዓት ፈጸምን ለማለት አይቻልም:: በዓሉን ስናከብርም በምድራዊው ዓለም፣ በዘላለማዊውም ሕይወታችን ለመጠቀም ነው:: የበዓሉ ዋና ዓላማ ልምድ መፈጸም ሳይሆን እግዚአብሔር ያደረገልንን መልካምነት በተግባር ማሳየት ነው::

**አዲስ ዘመን፡- እንዲህ ያሉ ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች አሁን ላይ የሚስተዋሉ በቋንቋ፣ በብሔር፣ በጎሳ፣ መከፋፈልን ለማስቀረት ለምን አቅም አልኖራቸውም? ምክንያቱም ችግሩ እየተፈጠረ ያለው በእምነት ውስጥ ባሉ አካላት ጭምር ነው፡፡ በዚህ ላይ ሃሳብ ቢሰጡ?**

**መምህር ዳንኤል፡-** ነገሩ ያስጨንቃል:: ጥናትም ይፈልጋል:: ቤተክርስቲያን ማስተማር የሚገባትን የሃይማኖት እሴት ታስተምራለች:: የምታስተምረውም የእግዚአብሔርን ቃል ነው:: የእግዚአብሔር ቃል እኛ እንድንጠፋፋ፣ እርስበርሳችንም እንድንጠላላ፣ በጥርጣሬና ባለመተማመን ውስጥ እንድንኖር፣ በማያቋርጥ ግጭት ውስጥና መከፋፈል ውስጥ እንድንኖር አይፈቅድም:: እግዚአብሔር በልዩ እንደፈጠረን ነው የምናምነው:: የእግዚአብሔር ፈቃድ የሰው ልጅ በፍቅር፣ በስምምነትና በደስታ እንዲኖር ነው::

የምናስተምርባቸው መጻሕፍትም የመጥፎ ምሳሌዎች አይደሉም:: የተዛባ ትምህርት አስተምረን የፈጣሪን ስም የምናረክስም አይደለንም:: ነገር ግን እግዚአብሔር ከማይወደው ነገር ውጭ የሆነ ነገር እንዴት መጣ? መጥፎ ነገሮች በማኅበረሰቡ ውስጥ እንዴት ሳለ? በተለይ ደግሞ አማኝ በሆነው ማኅበረሰብ ውስጥ፣ የሚለውን በጥልቀት ማየትና መወያየት ይፈልጋል:: በመደማመጥና በመስማማት ነገሩን በጥልቀት መዳሰስ ያለብን ይመስለኛል::

በርግጥ በጉዳዩ ላይ ቤተክርስቲያን ሳትነጋገርበት አልቀረችም:: እንዲያው 90 በመቶ በሚሆነው አማኝ ማኅበረሰብ ውስጥ መጥፎ ነገሮች እንዴት ተፈጠሩ ብለን በውይይት መድረኮች ላይ እናነሳለን:: አንዳንዶቹ የምንሰማቸው ድርጊቶች አማኝ አይደሉም በሚባሉት እንኳን ይፈጸማል ተብለው የማይጠረጠሩ ጭካኔ የተሞላበት ድርጊትና ግጭቶች በመካከላችን መፈጠሩ ከማሳዘን አልፎ ጥያቄ የፈጠረ ጉዳይ ነው::

ችግሮቹ እጅግ የበረቱ ናቸው:: ሁላችንንም አሳስበዋል:: ግን በሽታውን ወደ ማባባስ ወይንስ ወደ ማዳን ነው መሄድ ያለብን? በእኔ እምነት ይሄ ጉዳይ በሃይማኖት ተቋማት ብቻ የሚፈታ አይደለም። ያገባናል የሚሉ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች። ለፖለቲከኞችም በጋራ ሆነው የጋራ የሆነ መፍትሔ ለመስጠት መሥራት ይኖርባቸዋል:: በመንግሥት የወጡ ሕጎች አሉ:: በሃይማኖትም ጥብቅ የሆነ አስተምሮ አለ:: በእምነቱ ሰው ወገኑን ወይንም ወንድሙን ጠልቶ እግዚአብሔርን እወደዋለሁ ማለት እንደማይችል አስተምህሮ አለ:: ሰውን መጥላት እግዚአብሔርን መበደል ነው:: ስለዚህ ሕጎቹን ወደ ማኅበረሰቡ መተርጎም ይጠበቃል::

**አዲስ ዘመን፡- ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በዓላት የስጋት ምንጭ እየሆኑ የመምጣታቸው ጉዳይ እየተነሳ ነው፡፡ ከስጋት ነፃ ሆኖ ለማክበር ከማን ምን ይጠበቃል?**

**መምህር ዳንኤል፡-** ቤተክርስቲያን በዓላቷን በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን፤ በውጭውም ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ጭምር በልዩ ክብር ታከብራለች። ስጋት ውስጥ ሆኖ ማክበር የራሱ የሆነ አሉታዊ ጎን አለው። ግን አሁንም ደጋግመን የምንለው ችግሮቻችንን በመደማመጥና በመስማማት መፍታት እንጂ በዓላትን የችግር መነሻ ለማድረግ መሞከር ተገቢ አይደለም::

**ችግሮቻችንን በመደማመጥና በመስማማት መፍታት እንጂ በዓላትን የችግር መነሻ ለማድረግ መሞከር ተገቢ አይደለም**

ሰላምን የምንጋራው ሁላችንም ነው:: ሁላችንም በምንጋራው ውስጥ ደግሞ ሁላችንም አለንበት:: ስለዚህ ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን ከሚወጡ የተለያዩ ግለሰቦች፣ ተቋማትና ሕግ ከሚያስከብረው ጋር በጋራ ቤተክርስቲያን በዓሉ በሰላም እንዲከበር የምትሰራው ሥራ እንዳለ ሆኖ እያንዳንዱ ሰው በሰላም ግንባታ ለፀጥታ መስፍን፣ ስጋትን በማስወገድ፣ ኃላፊነት ስላለበት የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል::

**አዲስ ዘመን፡- የገና እና የጥምቀት በዓላትን ለማክበር የተደረጉ ዝግጅቶች በተለይም የጥምቀት በዓል የአደባባይ በዓል በመሆኑ የተሰጠውን ትኩረት ደግሞ ቢገልጹልን?**

**መምህር ዳንኤል፡-** ዝግጅቱን በተመለከተ መደበኛ የቤተክርስቲያናችን ዓመታዊ በዓል ስለሆነ፤ ከዋናው መንበረ ፓትሪያሪክ ጀምሮ በየትኛውም አካባቢ የሚገኙ እስከ አጥቢያ ቤተክርስቲያናት መንፈሳዊውንም፣ ማኅበራዊውንም በተለመደ መንገድ ቀኖናዊ ሥርዓቱን ተከትሎ እንዲከናወን ነው::

ገና በላልይበላ፣ ጥምቀት ደግሞ በጎንደር የተለመደ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዓላቱ ወደዚያ እንደሚያመዝኑ ይታወቃል:: ከዓለም አቀፍ ሳይቀር እንግዶች የሚታደሙበት እንደሆነም ይታወቃል:: ከታሪካዊ የአካባበር ሥርዓትና በአካባቢውም ካለው ተደራራቢ ታሪክ፣ መስህቦች፣ ቅርሶችና የማኅበረሰብ እሴቶች ጋር ተያይዞ አካባቢዎቹ ሰፊ ድምቀትና መስህቦች አላቸው። ይሄ እድል የተለየ ነው:: ይህ እንዳለ ሆኖ በሌሎችም አካባቢዎች በዓሉ በተመሳሳይ በደስታና በፍቅር ይከበራል:: ሰዎችም ይታደማሉ::

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ጎብኚዎች የሥነ ጥበብ ቅርሶች፣ ሥነ ሕንፃና ግብረ ሕንፃዎች፣ ታሪክና ባህል የሚስባቸው ሰዎች አሉ:: ነገር ግን ከነዚህ ጎብኚዎች ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት መንፈሳዊ የሆኑ ወይም የሕዝብ በዓላት ላይ መሳተፍ የሚፈልጉ ናቸው:: በዚህ የገና እና የጥምቀት በዓል ላይ ለመታደም ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ከሚመጡት መካከልም አብዛኞቹ የክርስትና እምነት ተከታይ ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ለጉብኝት ብቻ ሳይሆን፤ ጉዞአቸው መንፈሳዊም ነው:: ይህን እኔም በማስጎበኝበት ውስጥ በአንድ ወቅት በነበረኝ ተሳትፎ እውነታውን አረጋግጫለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- የገና እና የጥምቀት በዓላት የቱሪዝም መስህብም ሆነው በሀገር ምጣኔ ሀብት ላይ ያላቸው ፋይዳ ከፍ ያለ መሆኑ ይታወቃል። ቤተክርስቲያን በዚህ ረገድ ስላላት አበርክትዎ ቢነግሩን?**

**መምህር ዳንኤል፡-** ቱሪዝም በባህሪው ቅስቀሳና ማስታወቂያ ይፈልጋል:: ቤተክርስቲያን በራሷ ባቋቋመቻቸው የመገናኛ ብዙሃን፣ በሕትመት ውጤቶች፣ በማኅበራዊ ድህረ ገጾችና በተለያየ መንገድ በማስተዋወቅ ስትሰራ ቆይታለች:: አሁንም እየሰራች ነው:: በቅርቡም በቅርስ መመሪያዋ ሥር የቱሪዝም መምሪያ ከፍታለች:: ይህን ክፍል ያዋቀረችውም ቱሪዝም እንዲያድግና በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ አበርክቶ እንዲኖረው ካላት ፍላጎት የተነሳ ነው::

በዓላት ሲከበሩም እንዲሁ ለመታደም የሚመጡ እንግዶችን ታሳቢ ያደረገ ሥራ ትሰራለች:: በጋራ የምትሰራቸው ሥራዎች ደግሞ የበለጠ ውጤት እንደሚያስገኙም ስለምትገነዘብ ከመንግሥት ጋርም በትብብር ትሰራለች::

**አዲስ ዘመን፡-በኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ውስጥም እንደሚሰሩ ገልጸውልኛልና ይህ ተቋም አሁን ላይ ምን እየሰራ ነው?**

**መምህር ዳንኤል፡-** ይህ ተቋም ረዘም ላለ ጊዜ ሲሰራ የቆየ በመሆኑ የተለያዩ ተግባራት አከናውኗል። አሁንም እየሠራ ይገኛል:: የዚህ ተቋም ትልቁ እሴት ሃይማኖቶች በመከባበርና እርስ በርስ በመደጋገፍ አብረው እንዲኖሩ ማድረግ ነው:: በተቋሙ የማስተማሪያ መጻሕፍት ተዘጋጅቶ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በመዘዋወር ትምህርት ተሰጥቷል:: ትምህርቱ አሁንም ተጠናክሮ ቀጥሏል::

ትምህርቱ ጥሩ ተሞክሮ አስገኝቷል:: አንዱ ሃይማኖት የራሱን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ያለው በዓል ሲያከብር የሌላው እምነት ተከታይ ሳይነቅፍ፣ በጠላትነትም ሳያይ፣ ይልቁንም በመተጋገዝ፣ በመተባበርና በፍቅር አብሮ ለማድመቅ የሚደረግ ጥረት በማስገኘት መልካም የሆነ ተሞክሮ ማጎልበት ተችሏል:: ይህ በፖለቲካ ተጽእኖ ወይንም በሌላ ጣልቃ ገብነት ሳይሆን ትክክለኛ በሆነው የሰው ልጅ ስሜት ነው እየተፈጸመ ያለው::

**አዲስ ዘመን፡- ከገና እና ከጥምቀት በዓል ጋር ተያይዞ እንዲሁም ስለሰላሙም መልእክት እንዲያስተላልፉ እድሉን ልስጥዎ?**

**መምህር ዳንኤል፡-** በዓላቱ ከፍተኛ የሆነ ማኅበራዊ ትስስርን የሚፈጥሩ፤ የሰው ልጅ በጎነት፣ ደግነት፣ ደጎንነት፣ የእርስበርስ መጣመር የሚያጠነክሩ፣ ለተሻለ የጋራ ጥቅም እንዲሆን የሚያደርጉ ትምህርቶችና እሴቶች ያላቸው እንዲሁም በውስጣቸው ፍቅርን፣ መከባበርን፣ ሰላምን፣ አንድነትን መደማመጥን በጣም አጥብቀው የሚያስተምሩ ናቸው። በመሆኑም እኛ የምንመኘው እነዚህ እሴቶች በልባችን ውስጥ ዘልቀው ገብተው በማኅበረሰብ ውስጥ መጥፎ የጥላቻ አስተሳሰቦችን እንዲያስወግድልን ነው:: ጥላቻ በግለሰብ፣ በሀገር ደረጃ እጅግ ጎጂ ነው:: ማኅበረሰቡ እነዚህን መጥፎ የሆኑ ነገሮች በማስወገድ፤ ለሀገራችን አንድነትና ሰላም በሚሆን መንገድ እራሱን ማዘጋጀት ይኖርበታል::

**አዲስ ዘመን፡- መምህር፣ ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን፡፡ መልካም በዓል እንዲሆንልዎ እንመኛለን፡፡**

**መምህር ዳንኤል፡-** እኔም አመሰግናለሁ:: ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በዓሉ የሰላምና የፍቅር እንዲሆን እመኛለሁ::

# "የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ የሀገራችንን ታሪክና ባሕል እንድናውቅ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል"

**. በውጭ የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን**

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጥሪ የሀገራችንን ታሪክና ባሕል እንድናውቅ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል ሲሉ በውጭ የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ገለጹ።

ከተለያዩ ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ ለመጡ የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

ከኔዘርላንድ ወደኢትዮጵያ የመጣው ዳንኤል ገብረማርያም፤ ጥሪው በውጭ ሀገራት የምንኖር ኢትዮጵያውያን ባሕልና ታሪካችንን እንድናውቅ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል ሲል ሃሳቡን ሰጥቷል።

ወደ ኢትዮጵያ በመምጣቱ ደስታ እንደተሰማው የገለጸው ዳንኤል፤ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ ሀገሪቷ ያላትን ሀብት የበለጠ ለማስተዋወቅ የሚረዳ መሆኑን ተናግሯል።

በርካታ ሀገራት በቱሪዝም የሚያገኙት ገቢ ከፍተኛ መሆኑን ካየን ኢትዮጵያም በቱሪዝም ዘርፍ ተመጣጣኝ ገቢ እንድታገኝና የሀገራችን ገጽታዋን እንዲሻሻል ጥሪው ሰፊ ጠቀሜታ እንዳለው አንስቷል።

ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያንም ለሀገራቸው አምባሳደር በመሆን በያሉበት ሆነው ኢትዮጵያን ማስተዋወቅ ይጠበቅባቸዋል ያለው ወጣት ዳንኤል፤ የኢትዮጵያን ባሕል፣ ታሪክና ቅርስ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለማስተዋወቅ ዝግጁ መሆኑን አስረድቷል።

ከአሜሪካ የመጡት ወጣት ምሕረት በሪሁና ቴዎድሮስ ገብረንጉሥ በበኩላቸው፤ ጥሪው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ መልካም አጋጣሚ በኢትዮጵያ ቆይታቸው የተለያዩ መዝናኛ ስፍራዎች፣ የቅርስ መገኛና ታሪካዊ ቦታዎች፣ ተፈጥሯዊ ፏፏቴዎችና ሐይቆችን ለመጎብኘት እቅድ እንዳላቸው ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ያላትን ባሕል፣ ታሪክና ቅርስ ለማስተዋወቅ ፍላጎት አለን ያሉት ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያኑ፤ በተጨማሪም እናት አባት የሌሏቸው ሕጻናትን በመርዳት በሰብዓዊ አገልግሎት መሳተፍ እንደሚፈልጉ አመላክተዋል።

የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ተገኝተው አቀባበል ባደረጉበት ወቅት እንደተናገሩት፤ ሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ባሕላቸውንና ታሪካቸውን እንዲያውቁ በተደረገው ጥሪ መሠረት የተለያዩ ዝግጅቶች ሲደረጉ ቆይተው አሁን ላይ እንግዶቻችንን መቀበል ጀምረናል ብለዋል።

እንግዶቹን ለመቀበል ከቪዛ፣ ከጉምሩክ እንዲሁም ከተለያዩ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ጋር ተያይዞ በትኩረት ሲሠራ ቆይቷል ያሉት አምባሳደር ናሲሴ፤ ለሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያኑ የአገልግሎት ክፍያ ቅናሽ እንደተደረገ አስታውቀዋል።

ጥሪው በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በኩል እንዲሳለጥ ተደርጓል ሲሉ አምባሳደር ናሲሴ ጠቁመዋል። በሦስት ዙር ለሚመጡ እንግዶች ባሕላቸውን እንዲሁም ቅርስና ታሪካቸውን የሚያውቁበትና ረክተው የሚመለሱበት ትልልቅ ሁነቶች እንደተዘጋጁ ጠቁመዋል።

በውጭ ሀገር ለሚኖሩ የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን የቀረበው ጥሪ በሦስት ዙሮች የሚከናወን ሲሆን፤ "ከብዝኃ ባሕል መሠረትዎ ጋር ይገናኙ" የተሰኘው የመጀመሪያው ዙር ከታኅሣሥ 20 እስከ ጥር 30 እንደሚካሄድም ታውቋል። በጥሪው መሠረት የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን በሀገሪቱ የሚገኙ ብዝኃ ባሕሎችን እየተዘዋወሩ ይመለከታሉ ተብሎም ይጠበቃል።

## ተቋማቱ ለገና እና ለጥምቀት በዓላት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የአዲስ አበባ ከተማ ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት፣ የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ የአዲስ አበባ እሳት አደጋ ኮሚሽን እንዲሁም የአዲስ አበባ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የገና እና የጥምቀት በዓል ላይ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን በተሳካ ሁኔታ ለመስጠት የሚያስችለውን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ማጠናቀቃቸውን በትላንትናው እለት በጋራ በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል።

የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ገበየሁ ሊካሳ እንደገለጹት አገልግሎቱ በገና እና ጥምቀት በዓላት ወቅት የኃይል መቆራረጥ እንዳያጋጥም ዝግጅት የተደረገ ሲሆን ችግሩ ካጋጠመም በአስቸኳይ ለመመለስ እንዲቻል የተቋሙ ሠራተኞች በሥራ ገበታቸው ላይ እንዲገኙ ይደረጋል።

ዶ/ር ገበየሁ በዓሉን ምክንያት በማድረግ የቅድመ ክፍያ ቆጣሪ ተጠቃሚ ደንበኞች ሂሳብ ሳይሞሉ ቢቀሩ አገልግሎቱን እንዳያጡ በ 4ኪሎ ፣አያት ፣ካሳንችስ፣ ልደታ ፣ቃሊቲ ፣ለቡ ፣እንዲሁም አየር ጤና በሚገኙ የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት በበዓላት ቀናት ጭምር ሂሳባቸውን መሙላት እንደሚችሉ ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ምክትል ዳይሬክተር አቶ ሳዲቅ ሽኩር በበኩላቸው በአዲስ አበባ በቀን እስከ ሦስት ሺ ቶን ቆሻሻ የሚመረት ቢሆንም በበዓላት ወቅት ይህ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል ብለዋል። ይህም የከተማዋ ጽዳት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይፈጥር ኤጀንሲው ቆሻሻን ከተለያዩ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ለመሰብሰብ አስፈላጊ ዝግጅቶችን ማጠናቀቁን ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ እሳትና አደጋ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ይክፈለው ወልደመስቀል በበኩላቸው በበዓላት ወቅት ኅብረተሰቡ ለአደጋ የመጋለጥ እድሉ ከፍተኛ እንደመሆኑ ይህንን ለመከላከል የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል።

በዚህም ኮሚሽኑ ተሽከርካሪዎችን የማዘጋጀት፣ በቂ ውሀን የማቅረብና የአደጋ ባለሙያዎችን የማደራጀት ሥራ የሠራ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪነት የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ለነዋሪዎች መሰጠቱን ገልጸዋል።

ምክትል ኮሚሽነሩ አደጋን ለመከላከል ዋነኛው ኃላፊነት ሊወስድ የሚገባው ማኅበረሰቡ በመሆኑም የተለያዩ የኤሌክትሪክ ቁሶችን፣ ከሰልን ብሎም ተሽከርካሪዎችን ሲጠቀም በጥንቃቄ ሊሆን እንደሚገባ መክረዋል።

አስተዳደሩ በሚያደርገው ጥረት ብቻ ውጤት ማምጣት አይቻልም ያሉት ተቋማቱ ማኅበረሰቡ አደጋዎችንና የአካባቢ ብክለትን እንዲከላከል እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ትብብር እንዲያደርግ ጥሪ አስተላልፈዋል።

## የዓባይ ግድብ ወደ ማጠናቀቂያው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የተባበረ ጥረትና ጽናት ወደ ማጠናቀቂያ ምዕራፍ መሸጋገሩን አረጋግጧል።

የኢትዮጵያውያን የአብሮነትና ሀገር ወዳድነት ቋሚ መገለጫ የሆነው ግድቡ አጠቃላይ ግንባታው በአሁኑ ወቅት 94 ነጥብ 6 በመቶ መድረሱን ያስታወቀው ኮሚቴው፤ በዚህ ዓመት ተጨማሪ ተርባይኖችን ወደ ኃይል ማመንጨት ለማስገባት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አመላክቷል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ላለፉት 12 ዓመታት በጽናት ገንዘቡን፣ እውቀቱንና ሙያውን ለግድቡ ግንባታ ማዋሉንና የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ ኅዳር 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከ18 ቢሊዮን 734 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ማድረጉንም ኮሚቴው አመላክቷል።

የግድቡ 13ኛ ዓመት ኢትዮጵያውያን ቃላቸውን በተግባር ያጸኑበትን ዓውድ በሚገልፅ መልኩ እንደሚከበርና በውጭ የሚኖሩ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው ሲመጡ የተለያዩ ዝግጅቶችን በማድረግ ስለግድቡ የማስገንዘብና ተሳትፏቸውን እንዲያጠናክሩ የሚያደርጉ ሥራዎች ይሠራሉ ሲል ኮሚቴው አስታውቋል።

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት የሕዝብ ግንኙነትና ሚዲያ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ አብርሃም በበኩላቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳመለከቱት፤ ጽሕፈት ቤቱ የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ መንገዶችን በማዘጋጀት በ2016 በጀት ዓመት አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዷል።

በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያው በሦስት ወራት ለግድቡ ግንባታ ከሀገር ውስጥ ቦንድ ሽያጭ፣ በስጦታ፣ በአጭር የጽሑፍ መልዕክትና በልዩ ልዩ መንገዶች ከ383 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል ብለዋል።

ኅብረተሰቡ በቦንድ ግዥ፣ በ8100 የአጭር ጽሑፍ መልዕክትና ሌሎች የገቢ አሰባሰብ ሂደቶች ላይ የሚያደርገውን ተሳትፎ እንዲያጠናክር ጠይቀው፤ የግድቡ ግንባታ እስኪጠናቀቅ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ የሚደረገው የሃብት ማሰባሰብ ሥራ በተሻለ መነቃቃት እንደሚቀጥል አመላክተዋል።

የግድቡ ገቢ ማሰባሰቢያ የህዳሴ ግድብ ዋንጫ በሲዳማ ክልል በነበረበት ወቅትና ኅዳር 29 ቀን 2016 ዓ.ም ለሱማሌ ክልል እስከገባበት ጊዜ ድረስ አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር መሰብሰቡን ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

የግድቡ ዋንጫ በሱማሌ ክልል በሚኖረው ቆይታ ትልቅ ሀብት እንደሚሰባሰብ ይጠበቃል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የክልሉ ሕዝብ በሁሉም አማራጮች ድጋፉን ሊያጠናክር እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።

መጋቢት ወር ከመድረሱ አስቀድሞ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ትልቅ የሃብት ማሰባሰብ ንቅናቄ ለማካሄድ መታቀዱን ጠቅሰው፤ ለዚህም የሚረዳ ዝግጅት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ መሆናቸውን አስረድተዋል።

ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለዓባይ ግድብ ግንባታ ገቢ ማሰባሰብብ ከተጀመረበት ወቅት አንስቶ እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ 18 ቢሊዮን 613 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ መደረጉን አስታውሰዋል።

## በዓልና የጥበብ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ጎንበስ ቀና እያሉ በትሕትና ይሸጣሉ። ገዢዎችም ዋጋ እንዲቀንስላቸው እየተከራከሩ ልባቸው የፈቀደውን ይገዛሉ። አልባሳቱ ግን ሁሉም ያምራሉ፤ ሁሉም ድንቅ ጥበብ ናቸው፤ ሁሉም ቀልብን ይስባሉ።

በሽሮ ሜዳ ገበያ ለበዓልና ለሠርግ እንዲሁም ለተለያየ ዝግጅት የሚለበሱ ባሕላዊ እና ዘመናዊ አልባሳት በተለያየ መጠን፤ ለወጣቶች፣ ለሕፃናትና ለአዛውንቶች በልክ ተሰፍተው የተዘጋጁ፤ እንዲሁም በትዕዛዝ የሚሰፉ ብትን ጥበቦች በብዛት ይገኛሉ።

ዋጋቸው በመጠንና በጥራት እንዲሁም ፋሽን (አዲስ ፈጠራዎች) በመባል ይለያያሉ። ፋሽን የሚባሉት ዘመናዊ የሴት ወጣቶች አልባሳት ዋጋቸው ከስድስት ሺህ እስከ አስራ ሰባት ሺህ ይጠራላቸዋል።

በጥጥ ፈትል ብቻ የተሠሩ የባሕል ጥበቦች እንደየአካባቢው ባሕል ተሰትረዋል። ሕብረ ብሔራዊነትን በሚያንፀባርቅ አፈሻሸን የተቀናጡ ናቸው። እያንዳንዱ የባሕል ልብስ በዓሉ ከእኔ ውጪ አይደምቅም የሚል ይመስል ዓይኖችን ይሰርቃል፤ ልብን ያማልላል። ገዢ እንደፍላጎቱ የተለያየ ዲዛይን ያላቸውን እንዲያነሳ ጊዜው የፈቀደ ይመስላል።

የሕፃናት የባሕል አልባሳትም አሉ፤ ዋጋቸው እስከ ሁለት ሺህ ብር ይሸጣሉ። ለወጣቶች እና እናቶች እስከ አምስት ሺህ ብር የሚያወጡም እንደየአቅሙ በገበያው ቀርበዋል።

የባሕል ልብስ ገበያው ሁል ጊዜ በድምቀት ያዘጋጃል። ሽሮ ሜዳ የሚገኙ ነጋዴዎችም መተዳደሪያቸው የባሕል አልባሳት መሸጥና መሸመን ነው። ከእነዚህ ነጋዴዎች መካከል አቶ ሮቤል ካሕሳይ አንዱ ናቸው። ነጋዴው የበዓል መዳረስና የባሕል አልባሳት ገበያ አሁን ላይ ሙሉ ዝግጅት አድርገው ደምበኞቻቸውን እያስተናገዱ ነው።

ባሕላዊ እና ዘመናዊ ጥበብ ከወትሮ በበለጠ በዲዛይንና በጥራት ተዘጋጅተዋል። ዋጋው ላይም ቢሆን ከበፊቱ ጭማሪ አልተደረገም። ሆኖም ግን ገበያው ላይ መጠነኛ መቀዛቀዝ አለ ይላሉ አቶ ሮቤል።

አቶ ሮቤል፤ ሱቃቸው ከላይ እስከ ታች በሚያማልሉ የባሕል አልባሳትና ጥበባት ደምቆ ተውቧል። በትእዛዝ የተሠሩ እና ተሰፍተው የሚሸጡ ጥበቦች በዓይነት ተሰቅለዋል። ደምበኞችም እየገቡ ደስ ያላቸውንና አቅማቸው የፈቀደውን ለመግዛት ይመርጣሉ።

ሌላኛው ነጋዴ አቶ ተስፋይ ኃይሉ ናቸው። ሱቃቸው ውስጥ የወንዶችና የሴቶች አልባሳት በተለያየ ዲዛይን ተደርድረው ይታያሉ። ለግብይት የሚቀርቡ አልባሳት እጅግ ጥሩ ዝግጅት እንደተደረገባቸው በመግለፅ፤ የደምበኞች መጠን ቢቀዛቀዝም እስከ ጥምቀት በዓል ድረስ ደምበኞች የባሕል አልባሳት ሊገዙ ስለሚችሉ ለቀጣይ የመሸጥ ዕድል ይኖራል ብለዋል።

ገበያው ውስጥ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር የበዓል ልብስ ለመግዛት ሲዘዋወሩም ተመልክተናል። ወይዘሮ ለምለም ወዳጆ ከባለቤታቸው እና ከአንዲት ሴት ሕፃን ልጃቸው ጋር በመሆን ከጥጥ የተፈተለ ባሕላዊ ጥበብ ሲገዙ አገኘናቸው። ለሕፃን ልጃቸው ሙሉ ቀሚስ ጥበብ በሁለት ሺህ ብር የገዙ ሲሆን ለራሳቸው አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር የሚያወጣ ጥበብ ገዝተዋል።

ወይዘሮዋ እንደሚሉት፤ የአልባሳቱ ገበያ ከበፊቱ ብዙም የዋጋ ጭማሪ አላሳየም። በዲዛይንና በጥራት ግን መሻሻል ይታይበታል። ሌላኛዋ ገዢ ወይዘሮ ምሕረት ለገሰ ደግሞ የመረጡት በዘመናዊ መልክ የተዘጋጀ ጥበብ መነን ይሰኛል። ሰፊ ጥለት ያለው ሲሆን እጅጌ ሙሉ ነው። ጥለቱ በተለያየ ቀለም ስብጥር የተወሓደ የሚያምር ዲዛይን ወጥቶለታል። ዋጋውን ተከራክረው በዘጠኝ ሺህ ብር ገዝተዋል።

ወይዘሮዋ የባሕል ልብስ በጣም እንደሚወዱ ይናገራሉ። የልብሱ ዋጋ ተመጣጣኝ እንደሆነም ነው የሚያስረዱት። ይሁን እንጂ ሌላ ለበዓል የሚያስፈልግ ወጪ ብዙ በመሆኑ እንደ ልብ ለመግዛት ያዳግታል ብለዋል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

# ለሁለት ሺ ብር ሞባይል ሲባል የጠፋ የሰው ሕይወት

አስመረት ብስራት



የካቲት የወር ስም ሆኖ በጥር ወርና በመጋቢት ወር መሃል የሚገኝ ከአስራ ሶስቱ ኢትዮጵያ የወራት አቆጣጠር ውስጥ ስድስተኛው የወር ስም ነው። የካቲት ከተተ ከሚለው ግስ የተባዛ ነው። ወቅቱ የመኸር ጊዜ በመሆኑ አርሶ አደሩ ሰብሉን አጭዶ ሰብስቦ እና ወቅቶ የምርቱን ፍሬ ወደ ጎተራ የሚከትበት ወር በመሆኑ ወርሃ የካቲት ተባለ።

ገበሬው ምርቱን ሰብስቦ ወደ ጎተራ በሚከትበት በወርሃ የካቲት ያለፋበትን ገንዘብ ነጥቆ ከሀብት ቋቱ ሊከት የወደደው ቀማኛ በምሽት ተነጣቂውን አደፍጦ እየተጠባበቀ ነበር። የካቲት 17 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 3፡00 ሰዓት ሲሆን ተደብቆ ግዳዩን ይጠባበቅ የነበረው ቀማኛ ሰዓቱ ደርሶ ግዳዩ ወደ ወጥመዱ ገባ። በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ልዩ ቦታው አትላስ አካባቢ የሚባለው ቦታ ነበር ሀገር ሰላም ብሎ ቤቱ ሊገባ ጠደፍ ጠደፍ የሚለውን አቶ መኮንን መስፍንን በብረት አንገቱን በመምታት ኪሱን ፈታተሾ ያለውን ይዞ ለማምለጥ ይሮጥ ጀመር።

### ቀማኛው

አምታቴ ማሞ ይባላል። ስምን መልዓክ ያወጣዋል እንዲሉ አምታቴ እንደስሙ እያምታታ በሰው ላብ መክበርን ሥራው ያደረገ ሰው ነው። ዓመት ዓመትን እየወለደ ቢሄድም ከጥፋቱ ተምሮ በህቁ ሰርቶ መክበርን ከማሰብ ይልቅ እንዴት አድርጌ በተለየ መንገድ ዘርፌ መኖር እችላለሁ እያለ ያሰላስላል። ጨለም ያሉ ቦታዎችን ምርጫው የሚያደርገው ቀማኛ ለዘረፋ ተግባሩ ድምፅ የሌላቸውን መሳሪያዎች መጠቀም ምርጫው ያደርጋል።

በትንንሽ ቅሚያዎች የጀመረው ዘረፋ እለት እለትን እየጨመረ ሲሄድ ሱስ ሆነበት፡፡ አንድም ቀን ሳይሰርቅ መዋል ይከብደው ጀመር። ቦታ እየቀያየረ እለት እለት ልክ እንደ መደበኛ ሥራው የሰው ማጅራት እየመታ ያገኘውን ይዞ መሮጥ የእለት ከእለት ተግባሩ ሆነ።

ዛሬም ካገኘ በሰላም ዘርፎ ሊሄድ ካላገኘ ደግሞ በያዘው ፌሮ ብረት ማጅራት በመምታት ሊነጥቅ ተዘጋጅቶ ምቹ የሆነ ጨለማ ሰፍራ ተሸሽጎ ይጠባበቅ ጀመር። ከምሽቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ ጨለማውን ተገን አድርጎ ከለል የሚያደርገው ድንጋይ ስር ያደፈጠው ቀማኛ ብቻውን የሚመጣ መንገደኛ እስከ መጣ እየተጠባበቀ ሰዓታት አለፉ። እሱ ያደፈጠበት ቦታ ጨለም ስለሚል ይሁን ለሌላ ሰው ደፍሮ ብቻውን በቦታው ማለፍ ይፈራል።

ከዛ በኋላ ሰው ቀስ በቀስ ቤቱ ገብቶ ወደ ማለቁ ደረሰ። በግምት ከምሽቱ ሶስት ሰዓት አካባቢ ሲሆን አንድ ዳቦና ፍራፍሬ የተሞላ ፌስታል የያዘ ግለስብ ጠደፈ ጠደፍ እያለ ሲያልፍ ከተደበቀበት ወጥቶ ከኋላው ይከተለው ጀመር።

ልቡ ቤቱ መድረስ ላይ የነበረው መንገደኛ ከኋላው ማን እንደተከተለው ልብ ሳይል መንገዱን ብቻ እየተመለከተ ይሄድ ጀመር። ረጅም ርቀት ፊትና ኋላ ከሄዱ በኋላ ጨለማው ድቅድቅ ያለበት የሰው ዘር ዝር የማይልበት ቦታ ላይ ሲደርሱ በያዘው በረት አንገቱን በማለት ይጥለዋል።

መሬት ላይ እንደወደቀ ጊዜ ሳያጠፋ ኪሱን ፈትሾ ያገኘውን ጥሬ ገንዘብ ሰባት መቶ ብር፣ ሞዴሉ ያልታወቀ ሞባይል የዋጋ ግምቱ 2 ሺ ብር የሆነ፣ በአጠቃላይ 2ሺ ሰባት መቶ ብር የሚያወጣ ንብረት ወሰዶ ተዘራፊው በወደቀበት ጥሎት ከአካባቢው ለማምለጥ ይጣደፍ ጀመር።

### የናፈቀበት ሳይደርስ የቀረው አባት

መኮንን መስፍን ይባላል። ታታሪ ለፍቶ አዳሪ የሚባል ዓይነት ሰው ነው። በእለቱ ማልዶ ነበር ከቤቱ የወጣው። አስቸኳይ ሥራ ስለነበረበት ባለቤቱና ሁለት ልጆቹ እንደተኙ ድምፅ ሳያሰማ ሹልክ ብሎ ወደ ሥራው በረረ። ረፈድፈድ ሲል ባለቤቱ ጋር ደውሎ ሰላም ብሎ ማታ ቢያመሽም እንኳን ልጆቹ ሳይተኙ እንዲጠብቁት ይነግራታል።

«ተጨማሪ ገንዝብ ስላገኘሁ ለልጆቹ ምናምን ይገዬላቸው እመጣለሁ ሳታስተኚ ጠብቂኝ» በማለት ካስጠነቀቀ በኋላ አምሽቶ ከወጣበት ሥራው ቤቱ እስኪደርስ ልጆቹ ዓይኑ ላይ እየተንከራተቱ፤ የሚያስፈሊጋቸውን ፍራፍሬም፤ ዳቦም ሌሎች ሌሎች ነገሮችን ገዝቶ የተረፈውን ሰባት መቶ ብር ኪሱ እንደከተተ የናፈቁት ልጆቹና ባለቤቱ ጋር ለመድረስ ይጣደፍ ጀመር።

የናፈቃቸውን ልጆቹን አቅፎ ቤቱ ለመከተት የናፈቀው አባት በቀን ጎዶሎ የካቲት 17 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 3፡00 ሰዓት ሲሆን ያላሰበው ውርጅብኝ ወረደበት። ዘራፊው ልጆቹ ጋር ለመድረስ የተጣደፈውን አባት ንብረት ለመውሰድ እንዲመቸው ከኋላ ሆኖ በብረት አንገቱን በመምታት ሕይወቱ እንዲያልፍ አድርገው።

ለልጆቹ ይዞ ለመግባት ከገዛው አስቤዛ የተረፈውን ኪስ ውስጥ የነበረ ጥሬ ገንዘብ ሰባት መቶ ብር፣ ሞዴሉ ያልታወቀ ሞባይል የዋጋ ግምቱ 2 ሺ ብር የሆነ፣ በአጠቃላይ 2ሺ ሰባት መቶ ብር የሚያወጣ ንብረት ወስዶ የተነፋፈቁት ቤተሰቦች እስከ ወዲያኛው እንዳይገናኙ አደረገው።

### አጋጣሚ ያመጣቸው የዓይን ምስክሮች

በአጋጣሚ ከሰፈራቸው ራቅ ያለ ቦታ የሚኖር ወዳጃቸውን ለቅሶ ለመድረስ የወጡት ወጣቶች ለቅሶ ቤት አምሽተው ሲመለሱ… « አ….» የሚል ድምፅ ተሰማ። ከዛ ከደቂቃዎች በኋላ አንድ የሚሮጥ ሰው በርከት ብለው ወደሚሄዱት ሰዎች እየሮጠ መጣ። ሁኔታው ያላማራቸው ሰዎች ተረባርበው ይዘው ድምፅ ወደሰሙበት ይዘውት ሲሄዱ የወደቀ ሰው ተመለከቱ።

ምንም ነገር እንደላየ ቢናገርም ፖሊስ ጠርተው አስያዙት። የወደቀውም ሰው ለልጆቹ የገዛው አስቤዛ ሜዳው ላይ እንደፈሰሰ አስክሬኑ ተነስቶ በአንቡላንስ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ በቦታው ሲደርስ በአሳዛኝ ሁኔታ የወደቀው ምስኪን አባት፤ ልቀቁኝ አትልቀቁኝ እያለ የሚታገል ነፍሰ ገዳይ ፤ ለቅሶ አምሽተው የሚመጡ ከአስር የሚበልጡ ወጣቶች አካባቢው ደብልቅልቅ ብሎ ነበር። ፖለስ የዓይን ምስክሮችን ቃል ተቀብሎ ማስረጃውን ከያዘ በኋላ፤ የሆስፒታል ምርመራን ጨምሮ ወደ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ አቀረበ።

ንብረት ለመውሰድ እንዲመቸው ሟችን በመምታት ሕይወቱ እንዲያልፍ አድርገሀል ባለው ተከሳሽ ላይ ክስ ይመሰረትበት ዘንድ ወደ ዓቃቤ ሕገ የተላከው አምታቴ ማሞ የተባለው ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ወንጀል ሕግ አንቀጽ 671/2/ ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ክስ ቀርበበት፡፡

### የዓቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝር

ማስረጃውን የተቀበለው የዓቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው ተከሳሽ የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ የካቲት 17 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 3፡00 ሰዓት ሲሆን በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ልዩ ቦታው አትላስ አካባቢ ንብረት ለመውሰድ እንዲመቸው ሟች መኮንን መስፍንን በብረት አንገቱን በመምታት ሕይወቱ እንዲያልፍ አድርጎ ከሟች ኪስ ውስጥ የነበረ 1ኛ ጥሬ ገንዘብ ሰባት መቶ ብር፣ 2ኛ ሞዴሉ ያልታወቀ ሞባይል የዋጋ ግምቱ 2 ሺ ብር የሆነ፣ በአጠቃላይ 2ሺ ሰባት መቶ ብር የሚያወጣ ንብረት የወሰደ በመሆኑ በፈፀመው የከባድ ውንብድና ወንጀል ዐቃቤ ሕግ ክስ መስርቶበታል፡፡

### የእምነት ክህደት ቃል

የሰውን ላብ ለመብላት ጨለማን ተገን አድርጎ የሰው ነፍስ ያጠፋው ተከሳሹ የተከሰሰበት ክስ በችሎት ተነቦለት የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምኩም ጥፋተኛም አይደለሁም ያለ ሲሆን ዓቃቤ ሕግም ተከሳሹ ክዶ ቃሉን የሰጠ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የሚያስረዱ የሕግ ምስክሮቻችን ስላሉ ይሰሙልኝ በማለት ቀጠሮ ያስይዛል።

በቀጠሮውም ቀን በቦታው የነበሩ 10 የሰው ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችና ማስረጃዎችም በተከሳሹ ላይ በክሱ መሠረት ያስረዱ በመሆኑ ተከሳሽ በቀረበበት ክስ መሠረት እንዲከላከል የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ቀነ ቀጠሮ ተሰጠው።

ተከሳሹ የሰውና የሰነድ ማስረጃ ቀርቦበት ወንጀሉን አልፈፀምኩም የሚል የእምነት ክህደት ቃል በመስጠቱ የምስክርነቱን ቃል የሚሽር ሃሳብ ካለው መከላከያ እንዲያቀርብ በተሰጠው ቀጠሮ መሠረት 3 የመከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ቢያሰማም የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችንና ማስረጃዎችን ማስተባበል ባለመቻሉ ተከሳሹ ይከላከል በተባለበት ድንጋጌ ስር ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛ ነህ ብሎታል።

በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ወንጀል ሕግ አንቀጽ 671/2/ ስር የተደነገገውን ሕግ በመተላለፍ በፈፀመው የከባድ ውንብድና ወንጀል ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ ለውሳኔ ቀነ ቀጠሮ ተቆረጠ።

### ምሰክሮች

10 የሰው ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች በምሽት ያውም በጨለማ ከአንድ የሰቆቃ ደምፅ በኋላ ሲሮጥ ያገኙት መሆኑንና በወቅቱ ያልተገባ ዓይነት ሁኔታ በማሳየት ለማምለጥ ሲጣጣር መመልከታቸውን መስክረዋል።

« አንዴ አልነካሁትም፤ አንዴ ይሞታል ብዬ አላሰብኩም፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ አላውቀውም….. » በማለት ይቀበጣጥር እንደነበረ ተናግረው በወቅቱ በቦታው ላይ ማንም እንዳልነበረ ወንጀሉ ሲፈፀም በቅርብ ርቀት በመኖራቸው ነገሩ በትኩሱ እንዳለ መድረሳቸውን አብራሩ።

ከምስክርነቱም ባሻገር ማስረጃዎችንም በማቅረብ በተከሳሹ ላይ በክሱ መሠረት ያስረዱ በመሆኑ ተከሳሽ በቀረበበት ክስ መሠረት እንዲከላከል የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ቢጠየቅም ያንን ሊያደርግ ባለመቻሉ ለመጨረሻ ውሳኔ ግንቦት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ለማስወሰን ተቀጠረ።

### ውሳኔ

**ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎትም ግንቦት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ባስቻለው ችሎት በተከሳሹ ላይ በእርከን 38 ስር በማሳረፍ ተከሳሽን ያርማል ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያስተምራል ያለውን በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኖበታል**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ሌባ ሳ'መሉ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ከሰሞኑ በአንድ የማኀበራዊ ሚዲያ ገጽ አንድ ጽሑፍ ተለጥፎ አስተዋልኩ። ጽሑፉ ለዓይኖቼ አዲስ አልመስል ቢለኝ ጠጋ ብዬ አፈጠጥኩበት። አልተሳሳትኩም። ይህን ልጥፍ ከቀናት በፊት ከምንጩ በቀጥታ አንብቤዋለሁ። በነገሩ እየተገረምኩ ፊደላቱን አንድ በአንድ አነበብኳቸው። ‹‹እባክዎ! ፈሳሽ ሳሙና ቀንሰው አይውሰዱ›› ይላል።

ባይገርማችሁ ይህን የማሳሰቢያ ጽሑፍ ከሚመለከታቸው አካላት እየተለጠፈ በነበረ ጊዜ በቅርብ የታዘብኩ የዓይን እማኝ ነበርኩ። ስፍራው መፀዳጃ ውስጥ ከእጅ መታጠቢያው አጠገብ ከሚገኝ ግድግዳ ላይ ነው። በወቅቱ ይህን መልዕክት ስትለጥፍ ከነበረች የጽዳት ክፍል ኃላፊ ጋር ጥቂት አውርቻለሁ።

እሷ እንደነገረችኝ ፈሳሽ ሳሙናውን ቀንሰው ሲወስዱ እጅ ከፍንጅ የተያዙ ሠራተኞች አሉ። ይህ መቀጠል የለበትምና ማሳሰቢያውን መለጠፍ ግድ ብሏል። ጉዳዩን ስገረምበት፣ ሳፍርበትም ሰነበትኩ። ይህን መልዕክት ከዛን ዕለት ጀምሮ ለቀናት ሳየው ፊደሉንም በግርምት ስቆጥረው ቆይቻለሁ።

የሚያስገርመው ከጥቂት ጊዜያት በኋላ የሆነው ጉዳይ ነበር። ይህን ጽሑፍ በካሜራቸው ያነሱ አንዳንዶች ያዩትን እውነት አሁን በስም ላልጠቀስኩት አንድ የማኀበራዊ ‹‹ዩቲዩብ›› ገጽ በቀጥታ አስተላልፈውታል። የተላከው መረጃ በትክክል ሲለጠፍ ያየሁት ምስል ስለመሆኑ አልተጠራጠርኩም። በአካባቢው የነበሩ ቁሳቁሶች ሁሉ አንድም ሳይቀሩ አብረው ተልከዋል።

ይህን ተከትሎ መነጋገሪያ ሲሆን የቆየው ጉዳይ ታዲያ ሌላውን ተመሳሳይ ድርጊት ያስታውሰኝ ያዘ። መቼም ቸግሮን ሳይሆን ዓመል ሆኖብን የምንፈጽማቸው አንዳንድ ድርጊቶች ከስማችን በላይ መለያችን የሚሆኑበት አጋጣሚ ይኖራል። በአንዳንድ ቦታዎች ‹‹እከሌ እኮ ይሉኝታ የለውም። እከሊትም ነውርን አታወቅም›› የሚል ስም የሚሰጣቸው ሰዎች አይጠፉም።

እንዲህ አይነቱ ስያሜ የሚሰጣቸው ደግሞ ያለ ምንም ምክንያት አይደለም። አንዳንዶች በአንዳንድ ቦታዎች ክብራቸውን የሚያዋርድ፣ ሰውነታቸውን ዝቅ የሚያደርግ ጉዳይ ላይ ሲተጉ ይታያሉ። ለዚህ ማሳያ አንድ ምሳሌን ልጥቀስ። በሆነ የስብሰባ ቦታ በሚኖር የእረፍት ሰዓት ለቆይታው የሚሆን የሻይ ቡና ግብዣ አይጠፋም።

ታዲያ በዚህ ስፍራ አንዳንዶችን አለማየት ነው። የሚመጥናቸውን ያህል ከማንሳት ይልቅ የእጃቸው ሞልቶ አስኪፈስ፣ የጉንጫቸውም ተወጥሮ እስኪታይ የሚሻሙበት አጋጣሚ ይበረክታል። ጉዳዩ የሚያሳፍር ቢሆንም ለአድራጊዎቹ ግን ሁሌም ትክክል ነው።

ሰዎቹ ይህ ብቻ አይበቃቸውም። ለብዙኃን መስተንግዶ ሲባል የተዘጋጀውን ቆሎና ኩኪስ በየኪሳቸው እያጨቁ፣ ሌላ ካለ ለመጨመር ዓይናቸው ይቃብዛል። እንዲህ አይነቶቹ ታዲያ በሠርግና መሰል ግብዣዎች ላይ በተገኙ ግዜ ክፉ ዓመላቸው አይለቃቸውም። የተጠሩበትን በልተው ጠጥተው እንደጨረሱ በምስጋና መውጣት ልምዳቸው ሆኖ አያውቅም።

ዓመለኞቹ ከጎረሱት ምግብ ለመቋጠር፣ ከተጎነጩት ጠላና ጠጅ፣ ቢራና ድራፍት በላስቲክ ዕቃዎች ሞልተው ለመውሰድ ወደ ኋላ አይሉም። ይህ እንግዲህ ክፉ ዓመል ካልሆነ በቀር ምንም ስያሜ አይሰጠውም። ከመብላት መጠጣት ጥጋብ በኋላ የተረፈውን ላለመተው መሻማት ከትዝብት አልፎ ጥላቻ ላይ ይጥላል። ከዚህ ባሻገር ማንነትን በክፉ አስፈርጆ ስምን በአጉል ቅጽል ያስነሳል።

ከዚሁ የግብዣ ጉዳይ ጋር ተያይዞ በበርካቶች ዘንድ የሚነወር አንድ ልማድም አለ። ይህ አይነቱ ልማድ አንዳንዶች ያለ አንዳች ሀፍረት የሚደጋግሙት ነው። ሳይጠሩ ድንኳን ሰብሮ የመግባት ክፉ አባዜ።

ይህ እውነት የሰዎቹ ድርጊት እስኪታወቅ ድረስ በክብር ሊያራምድ ይችላል። ጉዳዩ ታውቆ ማንነታቸው በተጋለጠ ጊዜ ግን ሁኔታውን ያከፋዋል። ብዙ ግዜ እንዲህ አይነቶቹ ልማደኞች ጥሩ ለብሰውና፣ አምሮባቸው የሚታዩ ናቸው። ሰዓቱን ጠብቀው ከመድረስ ባለፈ የሚቀመጡበትን ስፍራ ሳይቀር ለይተው ያውቁታል።

በአለባበሳቸው አይታሙምና በሚመለከቷቸው ዘንድ ሁሌም ሚዛን ይደፋሉ። ይህ ቁመና ከሌሎች የቀደመ ቦታና አክብሮትም ሊያሰጣቸው ይችላል። እንዳሻቸው በልተውና ጠጥተው ከጠገቡ በኋላ ግን ዓይናቸው መቃበዙን አይተውም።

ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እጃቸውን ልከው የሚያነሱትን ይፈላልጋሉ። ሠርግ ከሆነ ሰዎች ቦርሳቸውን ከወንበር ጠረጴዛ ትተው ለጭፈራ ይነሳሉ። ሞባይላቸውን እንደዋዛ ጣል አድርገው በጨዋታ ይያዛሉ። ይሄኔ እነ አጅሬዎች በለስ ይቀናቸዋል። በተከበረ ሞገሳቸው እያታለሉ የሰውን ንብረት ገፈው ከስፍራው እብስ ይላሉ።

በዚሁ የሠርግ አጋጣሚ የአንዳንዶች ልማድ ደግሞ በሙሉ ዓይን ለማየት የሚከብድ ነው። ከቀረበው የምግብ ብፌ ፊት ፈጥነው ለመሰለፍ ቀዳሚ ይሆናሉ። ተራቸው ደርሶ ምግቡ በእጃቸው ሲገባ ደግሞ ምርጫ ይሉትን ጉዳይ ፈጽሞ አያውቁትም። ከእያንዳንዱ ላይ ሰሀናቸው መሸከም ከሚችለው በላይ እየቆለሉ ሌላ ለመጨመር እጃቸውን ይዘረጋሉ።

እነዚህ ሰዎች ‹‹ያየነው ሁሉ አይቅርብን›› ባዮች ናቸው። የሚሹትን ምግብ በእጃቸው ካስገቡ በኋላ ፊታቸው በፈገግታ ይደምቃል። ተጣድፈውና ተስገበግበውም መብላት ይጀምራሉ። በዚህ ፍጥነት ግን ጥቂት አይቆዩም።

ከእያንዳንዱ ላይ መለኳኮፍ እንደያዙ ሆዳቸው ይሞላል። ወዲያው ያነሱትን ምግብ ከአንዱ ጥግ አስቀምጠው ወደ ቦታቸው ይመለሳሉ። ምግቡ በወጉ ሳይበላ እንደባከነ ይቀራል። እነሱም ከትዝብት ወድቀው አይቀሬው ገላጭ ስም ይለጠፍባቸዋል።

አንዳንዴ ደግሞ እንዲህ ይሆናል። ሰዎች ለመስተንግዶ በገቡበት ከፍ ያለ የሆቴል መፀዳጃ ከሚቀመጥ በርከት ያለ ሶፍት ላይ ዓይናቸው ያርፋል። በክፍሉ ሲቆዩ ታዲያ ተጠቅመው ለመውጣት ብቻ አይደለም። በአግባቡ ተጠቅልሎ የተቀመጠውን የመጸዳጃ ወረቀት በእጥፍ በእጥፉ እየጠቀለሉ ከቦርሳ ከኪሳቸው ያጭቁታል።

እንዲህ አይነቶቹ ይህን ድርጊት የሚፈጽሙት ሁሌም መፀዳጃ ገብተው በወጡ ቁጥር ነው። እናም ለበርካቶች ግልጋሎት የታሰበውን ጠራርገው በመውሰድ ለግል በማዋል የሚያህላቸው የለም። ከዚሁ የመፀዳጃ አገልግሎት ጋር ተያይዞ የሚስተዋል ሌላም አሳፋሪ ጉዳይ አለ።

ዓመለኞቹ በዓይን ቅኝት የሚያገኟቸውንና በቀላሉ ለመፍታት የሚያመቹ ቁሳቁሶችን በኪስ ለማድረግ ፈጣን ናቸው። በግድግዳ የሚታሠሩ የሶፍት ማስቀመጫዎች፣ ጌጣጌጦች፣ በቀላሉ የሚፈታቱ የፎጣና የቀላል ነገር ማንጠልጠያዎች ሳይቀሩ ከዓይኖቻቸው አያመልጡም። ካመቻቸው ደግሞ ከኪስ ሲሆኑ የማያስታውቁ ፎጣዎችን ጭምር እንደ መሐረብ አጣጥፈው ይዘው ይወጣሉ።

ሌሎች ደግሞ በእንግድነት ውለው ካደሩበት ሆቴል አንሶላና የትራስ ልብስ ገፈው የሚወስዱ ናቸው። ነጠላ ጫማዎች፣ የሲጋራ መተርኮሻዎች፣ የቴሌቪዥን ሪሞቶችና መሰል ዕቃዎችም ከእነሱ አደን አያመልጡም። ደግነቱ አንዳንድ ነቄ ባለሆቴሎች ሁለት የተለያየ እግር ነጠላ ጫማ እያስቀመጡ ከመሰረቅ ለመዳን ይሞክራሉ።

ነገሩ ሁሉ ‹‹ሌባ ላመሉ›› ሆኖ እንጂ የሚወስዱ ቁሳቁሶች ሕይወትን የሚለውጡ፣ ታሪክን የሚቀይሩ ሆነው አይደለም። አንዳንዶች ግን በትንሽ ነገር ‹‹ሰው›› ይሉትን ታላቅ ክብር ሊያዋርዱ ይፈጥናሉ። ካልተገባ መንገድ ተገኝተውም ስማቸውን በከንቱ ያጎድፋሉ። ልቦናውን ይስጣቸው።

# ዓለም አቀፍ

## ሰሜን ኮሪያ ከደቡብ ኮሪያ ወደሚያዋስናት ድንበር 200 ሚሳይሎችን አስወነጨፈች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሰሜን ኮሪያ 200 ሚሳይሎችን ማስወንጨፏ ተገለጸ።

ሰሜን ኮሪያ 200 ሚሳይሎችን በማስወንጨፍ በጎረቤቷ ደቡብ ኮሪያ ያሉ ሁለት ደሴት እንዲለቀቁ ማስገደዷን ሮይተርስ ዘግቧል።

የሰሜን ኮሪያ ወታደራዊ ባለሥልጣን እንደገለጹት ሰሜን ኮሪያ ከደቡብ ኮሪያ ጋር ወደሚያዋስናት የማሪታይም ድንበር 200 ሚሳይሎችን አስወንጭፋለች።

በደቡብ ኮሪያ በሚገኙ ሁለት ደሴቶች ያሉ ነዋሪዎች ባልታወቀ "ሁኔታ" ምክንያት ለቀው እንዲወጡ ታዘዋል።

የሀገሪቱ መከላከያ ሚኒስትር ነዋሪዎችን ለቀው እንዲወጡ ያዘዘው፣ በሰሜን ኮሪያ ሚሳይል ተኩስ ምክንያት ወይም መልስ ለመስጠት ለማመቻቸት ስለመሆኑ አልገለጸም።

ነገር ግን ከሁለቱ ደሴቶች በአንዱ ነዋሪ የሆኑት ግለሰብ የደረሳቸው መልእክት የደቡብ ኮሪያ ባሕር ኃይል ተኩስ እንደሚያደርግ ያመለክታል።

ውዝግብ ከተፈጠረበት የማሪታይም ድንበር በቅርብ ርቀት የምትገኘው የዮንፒዮንግ ደሴት ባለሥልጣን የመልቀቅ ትዕዛዙ የተላለፈው በሲኡል ጦር መሆኑን ገልጸዋል።

ጦሩ በሰጠው መግለጫ እንዳስታወቀው የሰሜን ኮሪያ ሚሳይል ጥቃት በጦሩም ይሁን በንጹሐን ላይ ጉዳት አላደረሰም።

የሰሜን ኮሪያን ድርጊት "ጸብ አጫሪ" ነው ያለችው ደቡብ ኮሪያ፣ የኮሪያ ባሕረሰላጤ ሰላምን ሊያናጋ ይችላል ስትል አስጠንቅቃለች።

በፈረንጆቹ 2010 ሰሜን ኮሪያ ወደ ዮንግፒዮንግ ደሴት ከባድ መሣሪያ በመተኮስ ከ1953ቱ የኮሪያ ጦርነት ወዲህ ከባድ በተባለ ጥቃት አራት ሰዎችን መግደሏ ይታወሳል።

በወቅቱ ሰሜን ኮሪያ ጥቃቱን የፈጸመችው፣ ደቡብ ኮሪያ የቀጥታ ተኩስ ልምምድ በማድረግ ትንኮሳ ስላደረገች ነው የሚል መልስ ሰጥታ ነበር።





## የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ብሊንከን ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አቅንተዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ብሊንከን ወደ መካከለኛው ምስራቅ አቅንተዋል።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒዮ ብሊንከን በትናንትናው እለት ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ማምራታቸውን ሮይተርስ ዘግቧል።

ሚኒስትሩ ወደ መካከለኛ ምስራቅ ያመሩት በእስራኤል እና ሀማስ መካከል የተጀመረው ጦርነት ወደ ቀጣናው ይስፋፋል የሚል ስጋት ባየለበት ወቅት ነው።

ይህ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለሳምንት የሚቆየው ጉዞ፣ ሀማስ በእስራኤል ላይ ያልተጠበቀ እና ከባድ ጥቃት ካደረሰበት ከፈረንጆቹ ጥቅምት 2023 ወዲህ ለአራተኛ ጊዜ ነው።

ሚኒስትር እስራኤል እና ዌስትባንክን ጨምሮ ጆርዳንን፣ ኳታርን፣ ሳውዲ ዓረቢያን፣ ዓረብ ኢምሬትስን እና ግብፅን ይጎበኛሉ ተብሏል።

ከጦርነቱ በኋላ ጋዛ እንዴት መተዳደር አለባት በሚለው አስቸጋሪ ጉዳይ መሻሻል መኖሩን የጠቀሱት ብሊንከን ተጨማሪ የሰብዓዊ እርዳታ ወደ ጋዛ እንዲገባ ጥሪ አቅርበዋል።

ብሊንከን ጉዞ ያደረጉት በሀማስ ምክትል የፖለቲካ መሪ ሳለህ አል አሮሪ ላይ የደረሰው ግድያ፣ ግጭቱን ቀጣናዊ ያደርገዋል የሚል ስጋት ከተፈጠረ በኋላ ነው።

ከእስራኤል ጋር የተኩስ ልውውጥ እያደረገ ያለው በኢራን ይደገፋል የሚባለው የሊባኖሱ ታጣቂ ቡድን ሄዝቦላ ዝም ብሎ እንደማይቀመጥ ዝቷል።

የእስራኤል እና ሀማስ ግጭት ወደ ቀይ ባሕር ተስፋፍቶ መፋጠጥ ፈጥሯል።

የሀማስ አጋር የሆኑት እና አብዛኛውን የየመን ክፍል የተቆጣጠሩት የሀውቲ ታጣቂዎች በቀይ ባህር በሚንቀሳቀሱ 20 መርከቦች ላይ ጥቃት ሰንዝረዋል።

በጋዛ መጠነሰፊ ጥቃት እያካሄደች ያለው እስራኤል ጦርነቱ ለወራት ሊቆይ እንደሚችል ገልጻለች።

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# ተፈላጊ ሰው የመሆን ምስጢር

አስናቀ ፀጋዬ

አንዳንዴ በሰዎች ያለመፈለግ ስሜት ሊሰማህ ይችላል። ልትገፋ ትችላለህ። መገፋትህን ግን መጥላት የለብህም። ምክንያቱም አንዳንዴ ከባድ ሁኔታዎች ናቸው አንተን አንጥረው የሚያወጡህ። ከህይወታቸው ያወጡህ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። «አትረባም፣ የትም አትደርስም» ልትባል ትችላለህ። ከስራም ልትባበር ትችላለህ። ከፍቅር ግንኙነትህ ተከደህ ልትለያይ ትችላለህ።

ነገር ግን እነዚህ አንተን የገፉህ ሰዎች ተመልሰው ወደ ህይወትህ ዳግም ሊመጡ ይችላሉ። ሲመጡ ግን ትልቁን ቦታ አይደለም የምትሰጣቸው። መድረኩንም አይደለም የምትሰጣቸው። ይልቁንም አንተ መድረኩ ላይ ቆመህ የምተሰራውን ተአምር ቁጭ ብላችሁ ተመልከቱ ነው የምትላቸው። ስለዚህ በህይወት ወሳኝ ነገሮችና ተፈላጊ ሰው እንድትሆን የሚያደርጉህ እነዚህ ናቸው።

ርግጥ በህይወት ውስጥ ወሳኝ የሚባል ነገር የለም። ሰዎች “በህይወትህ ውስጥ ወሳኝ ነገር ምንድን ነው? ብለው ቢጠይቁህ የመጀመሪያው መልስህ ያንተ መኖርና ጤና ነው። የአእምሮ ዝግጅቱ፣ ስነልቦናው፣ የጊዜና የገንዘብ አጠቃቀሙና ሌሎች ኑሮን ለመምራት የምትጠቀምባቸው ዘዴዎች ቀጥሎ የሚመጡ ናቸው። ያንተ መኖር ግን ከምንም በላይ ወሳኝ ነው። ስለዚህ ያንተ መኖር ከምንም ነገር በፊት ወሳኝ ከሆነ ተፈላጊ ሰው ለመሆን ሚስጥሩ፡-

### 1ኛ. አመለካከት

አመለካከት ነገሮችንና ሁኔታዎችን የምትረዳበት መንገድ ነው። ያንተ እይታ ነው። ለምሳሌ አይንህ ላይ አረንጓዴ መነፅር ብታደርግ ነገሮች ሁሉ አረንጓዴ ሆነው ይታዩሃል። የቆሸሸ መነፅር ብታደርግ የቆሸሸ ነገር ይታይሃል። ችግሩ ግን ከአንተ አይደለም፤ ከመነፅሩ ነው። ሰዎች ብዙ ግዜ ወደው ክፉ አይሆኑም። «እኔ መቀየር አልችልም፤ መለወጥ አልችልም፤ የምፈልገውን ማሳካት አልችልም» አይሉም። ሆን በልው አይደለም ይሄ ነገር የሚመጣባቸው። በህይወታቸው በገጠሟቸውና ባሳለፏቸው ምክንያቶች አመለካከታቸው ተንሸዋሯል። በህይወት አስፍቶ የሚያይ ሰውና ፊት ለፊት ብቻ የሚመጣበትን የሚያይ ሰው ህይወትን እኩል አይኖሯትም።

አስፍቶ የሚያይ ሰው ነው ነገን ያስባል። ህልምና ዓላማ አለው። ምን ቢያደርግ የቱ ጋር እንደሚደርስ ያውቃል። ነገሮችን በቅርብ ብቻ የሚያይ ሰው ግን ህይወቱን ለማቆየት ብቻ ነው የሚኖረው። ኑሮ ባይወደድ ደስ ይለዋል። አይሯሯጥም። የማይመስሉ ነገሮችን ነው የሚያስበው። ለምን? አመለካከቱ በውጫዊ ነገሮች ተከቧል። ሁኔታዎች፣ ነገሮችና ሰዎች የእርሱን ህይወት እንደሚቀይሩለት ያምናል።

ስለዚህ ለፍላጋ ውጪ ከወጣህ አታገኝም። ፊኛ ከፍ ብሎ የሚወጣው ለምንድን ነው? ቀለሙ፣ አልያም ንፋስ አይደለም ወደ ላይ ፊኛውን ከፍ የሚያደርገው። በውስጡ የተሞላው አየር ነው ወደ ሰማይ ከፍ እንዲል ያደረገው። አንተንም ከፍ የሚያደርግህ፣ ከሰው በላይ የሚያደርግህ፣ ትልቅ ቦታ የሚያደርስህ ነገሮችን የምታይበት መንገድና አመለካከትህ ነው። ውስጥህ ከተቀየረ ውጪውን መቀየር በጣም ቀላል ነው። ብዙ ሰዎች ግን ውጪው እስኪቀየር ይጠብቃሉ።

### 2ኛ. ዓላማ

ዓላማ በህይወትህ ውስጥ ፈጣሪ አንተ እዚህ ምድር ላይ ስትመጣ እንድትጨምረው፣ የሆነ ነገር እንድታበረክት የተላከበት ሰነድ ነው። ለምሳሌ የሰው ልጅ ዓላማውን እንዴት ያውቃል ከተባለ በጣም በብዙ ልፋት ነው ሊያውቅ የሚችለው። የሰው ልጅ ማሽን አይደለም። ማሽን ቢሆን ኖሮ ፈጣሪ ድርሰቱን ይፅፈዋል፤ አንተ ትኖር ነበር። አላማ ከባድነቱ ድርሰቱን የምትፅፈው አንተ ነህ። የምትመራውና የምትቀምረው አንተ ነህ። ተዋኙም አንተ ነህ። አላማ ሲኖርህ ደግሞ ጥሩ ዳይሬክተር ነህ። ምን መሆንና በምን በኩል መሄድ እንዳለበህ ታውቀዋለህ። አላማ ሳይኖርህ ሲቀር ሰዎች ይጠቀሙበሃል። በነፈሰው ትነፍሳለህ። አላማ ከሌለህ መጠቀሚያ ትሆናለህ።

ህልም ከሌለህ ህልም የሌለው አገልጋይ ነው የምትሆነው። ህልምን መከተል አዲስ ቋንቋ እንደመልመድ ከባድ ነው። ብዙ ጊዜ ትሳሳታለህ፤ ትኮላተፋለህ፤ ቀስ ብለህ ግን መልመድህ አይቀርም። ስለዚህ አላማህን ማወቅ፤ ህልምህን ማወቅ በጣም ከባድ ነገር ሊሆን ይችላል። እንዴት ነው ታዲያ የምታገኘው? ትሞክራለህ የምትወደው ከሆነ ትቀጥላለህ። ከቻልክ ቁጭ ብለህ የማሰብ ልማድ ይኑርህ።

ስለዚህ ዓላማውን ማወቅና ህልሙን መረዳት የሚፈልግ ሰው በተቻለው አቅም ቁጭ ብሎ የማሰብ፣ ከሰዎች የመስማት ልምድ ማዳበር አለበት። ስታነብ ስለሰዎች እያወክ ነው፤ ስታስብ ደግሞ ራስህን ጠፍጥፈህ ለመስራት እድል እያገኘህ ነው። አላማህን ለማወቅ የምትፈልግ ከሆነ ጊዜ ውሰድ።

> **ዓላማ በህይወትህ ውስጥ ፈጣሪ አንተ እዚህ ምድር ላይ ስትመጣ እንድትጨምረው፣ የሆነ ነገር እንድታበረክት የተላከበት ሰነድ ነው**

### 3ኛ. መክሊት

ስትሰራው ጉልበት እንዳወጣህ የማይሰማህ ነገር አለ። ለምሳሌ ስትበላ «እኔ እኮ ስበላ ይደክመኛል፤ አልበላም» አትልም። መብላት ትወዳለህ። በተለይ ርቦህ ስትበላ በእጅህ ምግቡን ጠቅልለህ ወደ አፍህ እስክታደርሰው ድረስ ያለውን ሂደት የሆነ የጉልበት ስራ አድርገህ አትቆጥረውም። ደስ ብሎህ ነው የምታስገባው። በተመሳሳይ የሆነ ነገር መስራት ረሀብ /ፓሽን/ ይኖርሃል። ፓሽን ያንን ነገር ስትሰራ ምንም ጉልበት እንዳወጣህ አለመሰማት ነው። እንደውም ያንን በማድረግህ ደስታ ነው የሚሰማህ።

ብዙ አይነት መክሊቶች አሉ። አንዳንድ ሰዎች ቁጭ ብለው ሲያወሩ ደስ ይላቸዋል። ሌላው ደግሞ አምብቦና አድምጦ መፃፍ ደስታ የሚሰጠው ሰው አለ። አንዳንድ ሰው ከመድረክ ጀርባ ሆኖ የሚቀርፅ፤ ሰዎችን አሳምሮ ወደ መድረክ የሚያቀርብ “ፓሽን” ያለው ሰው አለ። ስለዚህ ፓሽን አንተ ሳይከብድህ በቀላሉ የምታደርገው ተግባር ነው።

የሰዎች ህይወት ላይ የሚጨምር ነገር ከሆነ ፓሽን ነው። ነገር ግን ደግሞ መተኛት የኔ ፓሽን ነው ብለህ በሰዎች ህይወት ላይ ምንም የሚጨምረው ነገር ከሌለ ፓሽን ሊባል አይችልም። ስለዚህ የሚያስደስትህ ነገር ሁሉ ፓሽን ነው ማለት አይደለም። የሚያስደስትህ ነገር የሆነ ዋጋ የሚጨምር መሆን አለበት ፓሽን። አድጎ ነገ የሆነ ትልቅ ቦታ ላይ ሊያደርስህ የሚችል መሆን አለበት።

### 4ኛ. ሰዎት አናሲሲስ /swot analysis/

አንድ ሰው ቢዝነስ ለመስራት ካሰበና ራሱን በደምብ ጠንቅቆ ማወቅ የሚፈልግ ከሆነ ሰዎት አናሊሲስ መስራት አለበት። ጥንካሬውን፣ ድክመቱን፣ እጁ ላይ ያለውን እድልና የእርሱን ተፎካካሪ ወይም ስጋቱን መለየት አለበት። ድክመትና ጥንካሬ ውስጣዊ ናቸው። እድልና ስጋት ደግሞ ውጫዊ ናቸው። እነዚህን ነገሮች ስታጠና ጠላትህን ይበልጥ ታውቀዋለህ። ጠላትህ ያው ማሸነፍ የምትፈልገው ህይወትህ ነው። ጠላቶች ሰዎች አይደሉም። ስለዚህ ህይወትን ማሸነፍ ነው ዓላማህ። ለዛ ነው እነዚህ ነገሮች ጠንቅቀህ ማወቅ ያለብህ።

5ኛ. ጥልቅ ፍላጎት

አሁን ዓለም የደረሰችበትን ቴክኖሎጂና ፈጠራዎች በሙሉ የወሰነው የሰው ልጅ ጥልቅ ፍላጎት ነው። የሰው ልጅ ፍላጎት ባይኖረው በፈረስ እስከዛሬ ድረስ ይጓዝ ነበር። የሰው ልጅ የምኞች ፍላጎቱ ነው ህይወትን የሚቀይርለት። በነፃነት እንዲህ ቢሆን ብለህ ህፃን ልጅ እንደሚመኘው ስትመኝ ያንን ፍላጎት ደግሞ ለማሳካት ስትሮጥ የራስህን ህይወት ብቻ ሳይሆን ዓለምን ልትቀይር ትችላለህ።

### 6ኛ. ውሉ

«ስላንተ እንድነግርህ ከፈለክ የጓደኛህን ፀባይ ንገረኝ» ይባላል። ጓደኛዬ እዚህ እዚህ ቦታ ይውላል ካልክ በርግጠኝነት አንተም ከዛ የተለየ ነገር አይኖርህም። ስለዚህ አብዛኛው ሰው ውሎ ሲባል በአካል አብሮ የሚያገኛቸውን ሰዎች፣ አብሯቸው የሚውላቸውን ሰዎች ብቻ ናቸው ብሎ ያስባል። አይደለም! ውሎ ማለት የአእምሮ ውሎ ነው። በስልክህ የምትውላቸው ውሎዎች አሉ። በርግጠኝነት አማካዩ ህዝብ በቀን ውስጥ ከአራትና ከአምስት ሰአታት በላይ ስልኩ ላይ ጊዜውን ያጠፋል። ይህ ማለት ወደድክም ጠላህም በስልክህ ላይ ከምታያቸው ሰዎች ጋር ጓደኛ ሆነሃል ማለት ነው።

ለምሳሌ አንድ ጂምሮን የሚባል አነቃቂ ንግግር ተናጋሪን ደጋግመህ የምታየው ከሆነ ብታውቀውም ባታወቀውም ጂምሮን ጓደኛህ ሆኗል ማለት ነው። አንድ በጣም የምትወደውን ቲክቶከር ወይም አስቂኝ ሰው ስለእርሱ ቁጭ ብለህ የምታይ ከሆነ ብትወደውም ባትወደውም ከዛ ሰው ጋር ጓደኛ ሆነሃል። ስለዚህ ከአስቂኝ ሰው ጋር የምትውል ከሆነ ሙያህ ወደ ኮሜዲያንነት እስካልተለወጠ ድረስ ህይወት ትስቅብሃለች። ከቁምነገረኛ ሰው ጋር በስልክህ የምትውል ከሆነ አንተም ቁምነገረኛ ነው የምትሆነው። ውሎህን ትመስላለህ። ሳታውቀው ማንነትህ መቀየር ይጀምራል።

እየደጋገምክ የምታደርጋቸው ነገሮች ህይወትህ ላይ ሳታውቀው መገለጥ ይጀምራሉ። አሁን የደረስከበት ደረጃ ላይ የወሰኑት ከአመታት በፊት ያደረካቸው ነገሮች ናቸው። በጣም ደጋግመህ የምታደርገው ነገር፣ የምታነባቸው መፅሃፍቶች፣ የምታያቸው ፊልሞች በሙሉ ህይወትህን ወስነውታል። ነገ የምትደርስበትን ደግሞ አሁን የምታደርጋቸው ይወስኑታል። መጠንቀቅ ያለብህ ለዛ ነው።

### 7ኛ. እምነት

ዓለም ላይ የማይመስሉና አይሆኑም የተባሉ ነገሮች ሆነዋል። ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ ጆንአፍ ኬኔዲ የተባለው የአሜሪካን ፕሬዝዳንት «በቅርቡ ጨረቃ ላይ ሰው እናስቀምጣለን» አለ። መሳቂያ ነበር የሆነው። መላው የአሜሪካን ህዝብ ተሳለቀበት። ግን ብዙ ጊዜ አልፈጀም። አሜሪካ ጨረቃ ላይ ሰው አስቀመጠች። ራሺያና ሌሎችም ሀገራት ተከተሉ። የማይመስሉ ነገሮች የሚሆኑት በእምነት ነው። ትንሿ ጥረትህ ትልቁን እንደምታከል አምነህ ካልጀመርክ ምን ታደርጋለህ? አንዳንድ ጊዜ ጭፍን እምነትህ ነው ህይወትህን የሚቀይረው። የማይመስሉ ነገሮችን አምነህ መጀመር አለብህ።

ነገር ግን የሚመስለውን ጥረት እያደረክ መሆን አለበት። አሁን በዚህ ሰአት ሚሊየነር፣ ቢሊየነር መሆን እፈልጋለሁ ካልክ መጀመሪያ አሁን እጅህ ላይ ምን ያህል ብር አለ? አሁን ላይ ተቀጥረህ በምትሰራበት ቦታ ምን ያህል እየጣርክ ነው? በትንሹ ከታመንክ ነው በትልቁ የምትሾመው። እምነት ማለት የማይታየውን፤ የማይጨብጠውን ነገር ማመን ነው። የምታየውንማ ማመን ማን ያቅተዋል፤ የሚል ያየውን ማመን ማለት ማረጋገጥ ነው። አለ ነው። ያላየኸውን ገና ይሆናል ብለህ የምታምነውን እርግጠኛ ስትሆን ነው የምታምነው።

ምድርን ያንቀጠቀጡና አለምን የለወጡ ሰዎች የተነሱት በእምነታቸው ነው። በሀይላቸው፤ በጉልበታቸው አይደለም። መጀመሪያ እምነታቸው ነው ጉልበትና ብርታት የሰጣቸው። አንዳንዴ የማይመስሉ ነገሮች በህይወትህ ይፈጠራሉ። እኔ እኮ ብዙ ግዜ ሞክሬያለሁ፣ ያላደረኩት ነገር የለም፤ ይህን ፍቅርና ትዳር ለማዳን፣ ይህን ቢዝነስ ቀጥ አድርጎ ለማቆም፣ ለመለወጥ ብዙ ሞክሬያለሁ ልትል ትችላለህ። ጥያቄው “ግን አምነሃል ወይ?” ነው። አንዳንድ ሰው እንደሚቀየር ሳያምን ዝም ብሎ ይሞክራል። እርግጠኛ አይደለም።

እምነት ከሌለው የምታደርጋቸው ጥረቶች ሁሉ ስጋ ለብሰው የእውነት አለም ላይ አይፈጠሩም። አንተም በአእምሮህ ያላየኸው ነገር እውነት ሆኖ አለም ላይ አታገኘውም፤ አትጨብጠውም። አንተ በአይምሮህ ከጨረስከው ነው በእውነታው ለመግለጥ ጉልበት የሚኖርህ። አይምሮህ አንድን ነገር እውነት ይሁን ውሸት መለየት አይችልም። አንተ ደጋግመህ ውሸትም ብትነግረው እውነት ነው ብሎ ነው የሚቀበለው። ግን ያንን ውሸት ለመግለጥ ደግሞ የማያደርገው ጥረት የለም። ሰላም ነው የሚነሳህ።

ለምን? አንተ ተኝተህ ስራውን የሚሰራ አእምሮ ነው ያለህ። ተኝተህ አየር ወጣ አየር ገባ አትልም። ተኝተህ ደምህ ሲዘዋወርና ምግብ ሲፈጭ አንተ አይታወቅህም፤ ተዘርረሃል። ይህንን የሚቆጣጠርልህ የአእምሮ ክፍል አለ። ለዚህ የአእምሮ ክፍልህ እየደጋገምክ መሆን የምትፈልገውን፣ ማሳካት የምትፈልገውን ብታሰርፅበት ጥረትህ ሁሉ ወደዛ ይመራሃል። አእምሮህ አንተ አውቀኸውም ሳታወቀውም ቢሆን፣ ከጀርባ በማታውቀው መንገድ እዛ ቦታ ላይ ራስህን እንድታገኝ ያደርግሃል። አንተ በአእምሮህ ማሳካት የምትፈልገውን ጨርሰው፣ በተግባር ጀምረው መጨረሻ ላይ ሆኖ ታገኘዋለህ።

# መሠረተ ልማት

# የ"ቢም" ቴክኖሎጂ - የግንባታ ኢንዱስትሪው አዲስ መንገድ

**በኃይሉ አበራ**

ዘመኑ ዘመናዊ የግንባታ አሰራሮች ተግባራዊ እየሆኑ ያለቡት ነው፡፡ የግንባታውም ዘርፍ ዘመኑን በዋጁ ቴክኖሎጂዎች እየተካሄደ ሲሆን፣ የአለማችን ትላልቅ ከተሞች ሰማይ ጠቀስ ግንባታዎች የዚሁ ውጤት መሆናቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ቴክኖሎጂዎች የግንባታውን ስራ እያቀለጠፉ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ ማድረግ እያስቻሉም ናቸው፡፡

ግንባታዎችም ውስብስብ እና ሰማይ ጠቀስ እየሆኑ መምጣቸውን ተከትሎ ይህን ግንባታ በተቀላጠፈ መንገድ ማካሄድ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች ናቸው ስራ ላይ እየዋሉ የሚገኙት፡፡ ቴክኖሎጂዎቹ ፕሮጀክቶችን በተቀመጠላቸው ጊዜ፣ ጥራት እና በጀት በወቅቱ ለማጠናቀቅም የሚያስችሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

በሀገራችንም በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ላይ ይህ ቴክኖሎጂ መተግበር ጀምሯል፡፡ በተለይ ‹‹ቢም›› የሚባለው ቴክኖሎጂ በግንባታ መጓተት ለምትቸገረው ኢትዮጵያ ጥሩ መፍትሄ ሊሆን እንደሚችል እየተጠቆመ ነው፡፡

በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት የኮንስትራክሽን ማኔጀመንት ቴከኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት ኢንጂነር ፈለቀ አሰፋ የቢም ቴክኖሎጂን ምንነት አስመልክተው እንዳብራሩት፤ ቢም የተሰኘው ቴክኖሎጂ /የህንጻ መረጃ ሞዴል ወይም ቡይልዲንግ ኢንፎርሜሽን ሞዴል) በዲዛይን፣ በግንባታና በኦፐሬሽን በተናጠል ጥቅም ላይ ሲውሉ የነበሩትን አሰራሮች በሙሉ ወደ አንድ ዲጂታል ፕላትፎርም አቀናጅቶ በማምጣት መስራት የሚያስችል ነው፡፡

ዲዛይነሩ ወይም አማካሪው የፕሮጀክቱን መረጃ ግልጽ /ሼር/ በማድረግ መጠቀም የሚያስችሉ እድሎች እንዳሉት ጠቅሰው፣ ቴክኖሎጂው ሙሉ በሙሉ ዲጂታል ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡ የምንፈልጋቸውን መረጃዎች ዲጂታል በሆነ መንገድ ለመፍጠር እንዲሁም ኮምፒውተሩ ላይ የምንፈለገውን በሙሉ በራሳችን ገንብተን ለመጨረስ የሚያስችለን ነው ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ በቅድሚያ ኮምፒውተሩ ላይ የተገነቡትን መሬት ላይ የማገናዘብ ስራው ይሰራል፡፡ በመሆኑም ፕሮጀክቱ ሁለት ጊዜ ይገነባል፤ የመጀመሪያው በሀሳብ ደረጃ ዲዛይኑንና የሚያስፈልጉ ነገሮች በሙሉ ተገንብተው ይጠናቀቃሉ፡፡ ይህ ሲጠናቀቅ ደግሞ ስራ ተቋራጩ በቀላሉ ወደ መሬት ያወርደዋል፡፡

በተለመደው አካሄድ ዲዛይኑ ተዘጋጅቶ ወደ ግንባታ ሲገባ ተጨማሪ ተለዋጭ ስራዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ ያሉት ኢንጂነር ፈለቀ፣ በዚህ ጊዜም የዲዛይን አለመጣጣም እንደሚፈጠር ይናገራሉ፡፡ ይህም ፕሮጀክቶች እንዲዘገዩ፣ ተሻሽሎም ሲመጣ ተጨማሪ ወጪና የግንባታ ጊዜ ይዞ እንዲመጣ እንዲሁም የመረጃ ክፍተት እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ያብራራሉ፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የቢም ቴክኖሎጂ ተግባራዊ ሲደረግ ከመነሻው የጠራ ዲዛይን፣ የአንዱ ባለሙያ ከሌላው ባለሙያ፤ የአንዱ እውቀት ከሌላው እውቀት ጋር የተናበበ ዲዛይን ተይዞ የሚወጣበት ነው፡፡ በዚህ የተነሳም ወደ መሬት ሲወርድም በቀላሉ ፕሮጀክቱን መገንባት የሚያስችሉ እድሎች ይኖሩታል፡፡

ቴክኖሎጂው በተበጣጠሰ መልኩ ያሉትን የአንድ ፕሮጀክት ታሪኮች ወደ አንድ ማምጣትና የጋራ ስራ መፍጠር የሚቻልበት ነው፡፡ በጋራ እና በቅንጅት ተመሳሳይ መረጃ በመያዝ ፕሮጀክት በቀላሉ መሰራት የሚችልባቸውን እድሎች ያሰፋል፡፡ የዲዛይን ቲምን፣ የኮንስትራክሽን ቲምን እንዲሁም አጠቃላይ ምርታማነትን ማሳደግ፣ ፕሮጀክቶች በጊዜያቸው ማለቅ እንዲችሉ እና የደንበኞች እርካታንም ለማሳደግ፣ የፕሮጀክቶችን ወጪም ለመቀነስ እንደሚረዳም ተናግረዋል፡፡

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ በጀት እንዳይጠየቅባቸው በማድረግ በተጨማሪ በጀትነት ሊጠየቅ የሚችለውን ሀብት ለሌላ ልማት መጠቀም የሚቻልባቸው እድሎች ይኖሩታል፡፡ የተያዙትን ፕሮጀክቶች በወቅቱ በማጠናቀቅ እና ሌላ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በመጀመር ኢንቨስተመንትን ማሳደግም ያስችላል፡፡

እስከ አሁን ባለው አካሄድ ፕሮጀክቶችን የማጠናቀቅ ችግር ሲፈጠር ይታያል፡፡ ፕሮጀክቶች ይጀመራሉ፣ ይቆማሉ፤ ተጨማሪ ወጪ ይደረግባቸዋል ያሉት ኢንጂነሩ፣ ከዚያ በኋላም ለማጠናቀቅ ሊከብድና ውል ከተገባበት ዋጋ ሁለት እጥፍ ድረስ ወጪ ሊጠየቅ የሚችልበት ሁኔታም ሊያገጥም እንደሚችል ተናግረዋል፡፡

የቢም ቴክኖሎጂ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ እንደሚያስችል ነው ያስታወቁት፡፡ ግንባታዎችን በወቅቱ



ማጠናቀቅ እና ጥራትን ማስጠበቅ እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡ በዚህም ዋጋን መቆጠብ እና የተናበበ ዲዛይን እንዲኖር ማድረግ ከተቻለ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ መጠናቀቅ ይችላሉ ፡፡ መንገድ፣ ውሃ እና መሰል መሰረተ ልማቶችን አስቀድሞ ለማሟላት ያስችላል፡፡ በዚህም የመጨረሻው ተጠቃሚ የሆነው ማህበረሰብ በቀላሉ በተገነባው ፕሮጀክት አገልግሎት ያገኛል፡፡

የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ከዚህ አኳያ የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት በኩል ለተለያዩ ተቋማት ባለሙያዎች በተከታታይ ስልጠናዎችን እየሰጠ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ስልጠናውን የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ ዩኒቨርስቲዎች ራሳቸውን ችለው ስልጠናውን እንዲሰጡ ለማድረግ የቢም ቴክኖሎጂን በስርአተ ትምህርቱ በማስገባት ተመራቂዎች እውቀቱንና ልምዱን እንዲቀስሙ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኢንጂነሩ እንዳብራሩት፤ ዩኒቨርስቲዎች በቀላሉ ቴክኖሎጂውን መተግበርና የስራ እድል ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ እንዲኖር ለማድረግም የወሊጋ ዩኒቨርስቲ፣ ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ፣ ሰመራ፣ ጅግጂጋ እንዲሁም አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኑቨርስቲዎችን ጨምሮ ከሰባት ዩኒቨርስቲዎች ሰባት አሰልጣኞችን በማፍራት እነዚህ ደግሞ ተመራቂዎችን እንዲያሰለጥኑ ለማድረግ እየተሰራ ነው፡፡

እስከ አሁንም 300 ያህል ተመራቂዎችን በሰባት ዩኒቨርስቲዎች ማሰልጠንና ሰርቲፋይ ማድረግ ተችሏል፡፡ በቀጣይም በዩኒቨርስቲዎች ቴክኖሎጂው በትምህርት አይነት ተካቶ በሶስት ዓመት፣ በአራት ዓመት፣ በአምስት ዓመት የቢም ቴክኖሎጂው ተካቶ እንዲማሩ እየተደረገ ነው፡፡ በዚህ አይነት ከተሰራ ቴክኖሎጂው ነገ አስገዳጅ ይደረግ ቢባል የሰለጠነ የሰው ኃይል ይኖረናል ማለት ነው፡፡

በግንባታውም ዘርፍ እንዲሁ የሰለጠነ የሰው ኃይል የማሟላት ስራ እየተሰራ ነው ያሉት ኢንጂነሩ ፣አማካሪ ዲዛይን ቲም እንዲፈጠርለት፣ ስራ ተቋራጭ የኮነስትራክሽን ቲም እንዲፈጠርለት፣ ዲዛይንና ቡይልዲንግ ቲሞች እንዲሟሉ እየተሰራ ነው ሲሉም አብራርተዋል፡፡ በተለይ ፕሮጀክት ያላቸው የመንግስት ተቋማት የዲዛይን ቲም ፣ የግንባታ ቲም እንዲፈጠርላቸው እየተሰራ መሆኑንም ነው ያመለከቱት፡፡

የፕሮጀክቶች መጓተት አንዱ ምክንያት የዲዛይን ክፍተት መሆኑን ጠቅሰው፣ ቴክኖሎጂው ተግባራዊ በሚደረግበትም ወቅት ክፍተቶች እንዳይፈጠሩ ችግሩን ለመፍታት የተናበበ ዲዛይን ማዘጋጀት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

መንግስት እስካሁን ቴክኖሎጂውን አስገዳጅ አላደረገም ያሉት ኢንጂነሩ አንዳንድ ተቋማት በራሳቸው ሙከራ እያደረጉ መሆናቸውን ግን አመልክተዋል፡፡ የተወሰኑ ፕሮጀክቶችም በቴከኖሎጂው እንዲጠቀሙ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ኢንጂነር ፈለቀ እንዳሉት፤ የፌደራል ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት ፅህፈት ቤት ባለሙያዎቹን አሰልጥኖ፣ ሶፍትዌር ገዝቶ፣ ኮምፒውተርም አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ የብሔራዊ ትያትር፣ የሰነዶች ማረጋገጫ ፕሮጀክት ላይ፣ እንዲሁም የወጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ካዛንቺስ አከባቢ በሚያስገነባው ፕሮጀክት ላይ ቢያንስ ዲዛይን ደረጃ ላይ ያሉትን ነገሮች በቢም ቴክኖሎጂ ማኔጅ ለማድረግ እየተሞከረ ነው፡፡ በቀጣይም ግንባታ ላይ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የሚደረግበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

ቲኤች ኢንጂነሪንግ በጫካ ፕሮጀክት የሚሰሩ ወደ 29 ህንጻዎችን በቢም ቴክኖሎጂ ተገባራዊ እያደረገ መሆኑን ኢንጂነሩ ጠቅሰው፣ ኦቪድ ግሩፕን የመሳሰሉት ተቋራጮች ፕሮጀክቶቻቸውን ወደ ቢም ቴክኖሎጂ እያስገቡ ናቸው ብለዋል፡፡

መንግስት ቀድሞ ይሄንን መሸከም የሚችሉ ተቋራጭ ተቋማትን መፍጠር ላይ እየሰራ ነው ያሉት ኢንጂነሩ፣ በተለይ በስራ ተቋራጮች ማህበር፣ በአማካሪ መሀንዲሶች ማህበር የሚመጡትን ተቋማት እያበቃ ወደ ስራ እንዲገቡ አሰፈላጊው ድጋፍ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል፡፡

የግንባታ ፕሮጀክቶችን በተቀመጠላቸው ጊዜ ለማጠናቀቅ እና ግንባታዎችን ለማስተዳደር የቢም ቴክኖሎጂ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን ስለመሆኑ የኢንፎርሜሽን ቴከኖሎጂ ፓርክ ኮርፖሬሽን/ አይሲቲ ፓርክ በመባል የሚታወቀው ተቋም/ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር አፈወርቅ ንጉሴም ይገልጻሉ፡፡ እሳቸውም በዓለም ላይ በአሁኑ ወቅት ውስብስብ ህንጻዎች የሚገነቡት በቢም ቴክኖሎጂ በመታገዝ መሆኑን ጠቅሰው ፣ቴክኖሎጂው በዲዛይንም ዘመናዊ አሰራርን በመከተልም ይታወቃል ብለዋል፡፡

በቴክኖሎጂው በመጠቀም ግንባታን በማከናወን ረገድ የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት በሀገር ደረጃ ግንባር ቀደም መሆን መቻሉን አስታውቀው፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፓሬሽን (ኢኮስኮ)ም እንዲሁ በቅርቡ ቴክኖሎጂውን የሚያስፋፋበትን ማዕከል ማስመረቁንም ተናግረዋል፡፡

ይሄንን ቴክኖሎጂ ተግባራዊ በማድረግ በኩል ከአፍሪካ ደቡብ አፍሪካ በዚህ ላይ ከፍተኛ ልምድ እንዳላትም ተናግረዋል፡፡ ኢኮስኮም ከደቡብ አፍሪካ ጋር እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ እሳቸውም የዚህ ቦርድ አባል መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ እስከ አሁን አብዛኛዎቹ የህንጻ ዲዛይኖች በሁለት ዳይሜንሽን (ኤክስ እና ዋይ) ብቻ በሚያሳይ መልኩ ተሰርተው የሚታዩ ናቸው፤ ቢም ቴከኖሎጂ ተግባራዊ አድርገው የሚሰሩ ህንጻዎች ግን እስከ አምስት ዳይመንሽን (5D) ደርሰዋል፡፡ ይህም የህንጻው ግንባታ ካለቀ በኋላ የሚታዩ የህንጻውን አካላት በሙሉ ገና ግንባታው ሳይጀመር መመልከት የሚያስችል ነው፡፡

የቢም ቴክኖሎጂ ሶፍትዌር የግንባታ ፕሮጀክት ከመጀመሩ በፊት የግንባታው የተለያዩ ክፍሎችን እና አካላትን አስቀድሞ ለማወቅ ያስችላል፤ ህንጻዎች ከተገነቡ በኋላም ደህንነታቸውን ለመጠበቅ፤ ጥራቱን ባለበት ለማስቀጠል፣ የአቅርቦት ቁጥጥር ለማድረግ ያስችላል፡፡

የህንጻው ግንባታ ከመጀመሩና ከመጠናቀቁ ቀደም ብሎ አጠቃላይ ወለሉን፣ ግድግዳውን፣ የውሃ መስመሩን፣ የኤሌክትሪክ መስመሩን፣ የእሳት መቆጣጠሪያ ሲስተሙን፣ አሳንሰሩን፣ በርና መስኮቱን፣ ጣሪያውን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆጣጠሪያውን፣ ሶኬት፣ ወዘተ ሁሉ በቴክኖሎጂው ይመላከታሉ፡፡ የህንጻ ግንባታ ጥራት እንዲሁም የመንገድና የተለያዩ ዘርፎች ኤክስቴንሽኖች አጠቃላይ ሁኔታን በተመለከተም ቴክኖሎጂው መረጃ ይሰጣል፡፡

የቢም ቴክኖሎጂ አይነት እና መሰል ቴክኖሎጂዎች በሀገራችን ተግባራዊ መደረግ መጀመራቸው በግንባታ ዘርፉ ለዘመናት ወደኋላ የቀረንበትን ሁኔታ ለመቀየር ያስችላል ያሉት ኢንጂነር አፈወርቅ፣ ፕሮጀክቶችን ለማፋጠንና ዘርፉን ለማዘመን እንደሚያስችል አስቸውም ገልጸዋል፡፡ ሰማይ ጠቀስ እና ውስብስብ ህንጻዎች እንደ ቢም ባሉ ሶፍትዌሮች ሲገነቡ የህንጻውን ውስብስብ ገጽታ በቀላሉ ለማወቅ እንደሚያስችሉ ተናግረዋል፡፡

አርክቴክቱ፣ ሜካኒካል ኢንጂነሩ፣ ኤሌክትሪሺያኑ ወዘተ፣ በተመሳሳይ ጊዜ እየተናበቡ አብረው መስራት የሚችሉበትንም እድል ይፈጥራል ሲሉ አመልክተው፣ አንዱ አንዱን ሳይጠበቅ እየተናበቡ መስራት የሚችሉበትን ሁኔታ፣ ፕሮጀክት በወቅቱ እንዲጠናቀቅ፣ ዋጋ እንዳይጨምር ማድረግም ያስችላል ፡፡ ፕሮጀክቱ በበጀት፣ በገንዘብ፣ በጥራትና በጊዜ በታቀደው ልክ እንዲጠናቀቅም ያግዛል ሲሉም አብራርተዋል፡፡

ቴክኖሎጂው ሊያጋጥሙ የሚችሉ መሰናክሎችን እና ስጋቶችንም አስቀድሞ ለመረዳት እድል እንደሚፈጠር ኢንጂነር አፈወርቅ ተናግረዋል፡፡ ለግንባታው ግብዓት የሚሆኑትን ነገሮች አስቀድሞ ለማሰብና ለማዘጋጀት እንደሚረዳ ጠቅሰው፣ አስፈላጊ ግብኣቶች አስቀድሞ በማሟላት ከሥር ከሥር በፍጥነት በእቅዱ መሰረት ለመስራት በር እንደሚከፍት ጠቁመዋል፡፡

በኢትዮጵያ በቢም ቴክኖሎጂ ከተገነቡ ህንጻዎች መካከል ግዙፉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲሱ ህንጻ አንዱ መሆኑንም አመልክተው፣ በአዲስ አበባ የተገነቡና እየተገነቡ የሚገኙ ትላልቅ የባንክ ህንጻ ፕሮጀክቶች ቢም ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ የዋለባቸው መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ ዘጠነኛውን የከተሞች ፎረም አስመልክቶ በቅርቡ በተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ቴክኖሎጂው የህንጻ የግንባታ ስራ ተሰርቶ ፊዚካል መሰረተ ልማቱ ከቆመ በኋላ ሳይሆን ገና ከመገንባቱ በፊት ማን ምን ይስራ፣ የቱ ጋ ምን ይሁን፣ ምን እንቀንስ የሚለውን የሚመልስ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ከ30 እና 40 በመቶ በላይ ዋጋ መቀነስ የሚያስችል ቴክኖሎጂ መሆኑንም ያመለከቱት፡፡

የተቋራጩ እና የደንበኛው/ባለቤቱ/ አለመናበብ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዲዛይን በአግባቡ ሳይበለጽግ የሚወጣበት እና በቅንጅት ምክንያት ግንባታዎች ፈርሰው እንደገና የሚገነቡበትን ሁኔታ እንደሚያስቀር ጠቅሰው፣ ይሄንን ችግር አስቀድሞ የሚቀርፈውና የግንባታ ስራዎችን በቴክኖሎጂ ለመደገፍ የሚያስችለው የቢም ቴክኖሎጂ በሀገሪቱ እየተዋወቀ መሆኑን አመላከተዋል፡፡ ቴክኖሎጂው በግሉ ዘርፍ እንዲሁም ፐብሊክ ኢንቨስትመንቱ ላይ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፣ በግንባታው ዘርፍ ላይም ለውጥ እየመጣ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ገና፡- የፍቅር፣ የይቅርታና የትሕትና መገለጫ በዓል!

የገና በዓል በክርስትና እምነት ተከታዮች ከሚከበሩ ሃይማኖታዊ/መንፈሳዊ በዓላት አንዱ እና ዋነኛው ነው። በሃይማኖቱ አስተምሮ መሠረት በዓሉ፣ በብዙ ነብያት አንደበት ሲነገርለት የኖረው፣ ለሰው ልጆች መዳን ተስፋ የተደረገው፣ የክርስቶስ ኢየሱስ ውልደት ከቤተልሔም የተበሰረበት ታላቅ ቀን ነው ።

እለቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በኃጢያት ምክንያት ከፈጣሪው/ከአምላኩ ጋር ተራርቆ በጭለማ ውስጥ ለመኖር ለተገደደው ለሰው ልጅ በደሙ የኃጢያት ስርየት ይሆን ዘንድ በብዙ ፍቅር እና ትሕትና የእግዚአብሔር የመስዋዕት በግ ሆኖ ወደ ምድር የመጣበት፣ ለኃጢያት ስርየት ተስፋ ጀማሪ የሆነበት ቀን ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በሰውና በአምላክ መካከል በኃጢያት/ባለመታዘዝ ምክንያት የተፈጠረውን የጥል ግድግዳ ለማፍረስ፣ ሰላም እርቆት ለነበረው የሰው ልጁ እውነተኛ ሠላም በመሆን ከሠላም እጦት ሊታደገው በከብቶች ግርግም የተወለደበት ፤ እና የሠላም ብስራት ዜማ ሆኖ የተሰማበት ዕለት ነው ።

ለክርስትና እምነት ተከታዮች የመዳናቸው ጅማሬና ብሥራት የሆነው ይህ ቀን፣ ትውልዶች በብዙ መሻት ከሩቅ እያዩ የተሰናበቱት የመዳን ተስፋቸው፤ ከተስፋ ቃልነት አልፎ ሥጋ ለብሶ የተገለጠበት፣ በዚህም ከጥልቅ ፍቅር የሚመነጨውን የአምላካችንን ይቅር ባይነት የተረዱበት የደስታ ቀን ነው ።

እንደ እምነቱ አስተምሮ፤ ይህ የሆነው በብዙ ምሕረት እና ስለ ፍቅር ነው። ይህ የሆነው፤ በብዙ ይቅርታ፤ የተወለደውን ደግሞም ስለ ኃጢያት በመስቀል ላይ የሞተውን የኢየሱስ ክርስቶስ የፍቅሩ፣ የይቅር ባይነቱ፣ የትሑትነቱ፣...ወዘተ የባሕሪ ተካፋይ መሆን እንድንችል ነው ።

የእምነቱ ተከታዮች አሁን ላይ ይህንን ትልቅ ትርጉም ያለውን የገናን በዓል ለማክበር ስንዘጋጅ፣ ከሁሉም በላይ ራሳችንን ፣ ከእምነቱ አስተምህሮ አንጻር የቱ ጋር ነኝ ብለን በድፍረት ልንጠይቅ፣ ለሚያገኘውም ምላሽ ታማኝ በመሆን ራሳችንን በአግባቡ ልንመረምር ይገባል።

ከወንድሞቻችን ጋር ያለንን ኅብረት፤ ኅብረታችን የተገዛበትን ፍቅር፣ ትሕትናና ይቅር ባይነት ልናስተውል ያስፈልጋል ። በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ለሌሎች ያለንን የሕይወት ተምሳሌትነት ቆም ብለን ልናጤን ያስፈልጋል።

እንደ ሀገር ክርስትናን በመቀበል ካለን የቀዳሚነት ትርክት አንጻር፤ ያሳለፍናቸውን ብዙ አስቸጋሪ ትናንቶችን ጨምሮ፤ ዛሬ ላይ እየኖርናቸው ያሉ የፈተና ቀናቶቻችንን በአግባቡ ልንመረምራቸውና ለዚህ የሚሆን ድፍረት ልንፈጥር ይገባል።

በዓሉ መንፈሳዊ በዓል ከመሆኑ አኳያ፤ በመወለዱ፤ በመከራውና በሞቱ ከተካፈልነው የፍቅር፣ የእርቅ እና የሰላም መንፈስ አንጻር፤ እንደ ሀገር በምድራችን እየሆነ ያለውን እውነታ በመወለዱ የተስፋ ቃል ልናየው፤ ለዚህ የሚሆን መንፈሳዊ ዝግጁነት ይጠበቅብናል።

እንደ ሕዝብ አሁን ላይ እየሄድንበት ያለው የፍቅር እጦት፣ የመለያየት እና የጥል መንገድ የተገነባበት ማንነታችን ከምን መንፈስ እንደተቀዳ፤ በሰከነ መንፈስ ልናጤነው ያስፈልጋል። ወንድም በወንድሙ ላይ የጨከነበት፣ በስደት እና በሞቱ በአደባባይ የሚፈነድቅበት አስተምሮን ከየት እንዳገኘነው ልንመረምር ይገባል።

እርቅን እንደ ሸንፈት የሚቆጥረው አዕምሯዊ ስሪታችን ከየትኛው መንፈስ እንደተቀዳ፣ ለጥፋት መፎከር እና ማቅራራታችን፣ በዚህም እየደነደነ ድንጋይ እየሆነ ያለው ልባችን ወዴት እየወሰደን እንደሆነ፣ በዚህም ትውልዱን እያስከፈልነው ስላለው ዋጋ ቆም ብለን ልናስብም ይገባል።

በዓሉን ስናከብር ከመብላትና ከመጠጣት ባለፈ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ ባለፈ፣ እስከ መስቀል ሞት ድረስ የሄደበትም የማዳኑን ሀሳብ፣ በኛ ሕይወት እንዲገለጥ የወደደውን የባሕሪውን ምንነት እያሰብን፤ ለሱ ያለንን ተገዢነት እያደስን መሆን ይኖርበታል።

ይህንን ማድረግ መቻል እንደ ሀገር አሁን ላይ እየተገዳደሩን ያሉ ፈተናዎችን ተሻግረን በሃይማኖቱ አስተምሮ ተስፋ የምናደርገውን፤ እውነተኛ የፍቅር፣ የእርቅና የሠላም ሕይወት ወራሽ እንሆናለን። ከዚህም አልፈን ለመጪ ትውልዶች በሁሉም መልኩ/በመንፈሳዊም ሆነ በቁሳዊ ሕይወት የተመቸች ሀገር መፍጠር እንችላለን!

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ

መልካምሥራ አፈወርቅ

‹‹ገና›› የሚለው ቃል ከግሪክ ቃል የተወረሰ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይህ ቃል ሲተረጎም ‹‹ልደት›› ማለት እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ‹‹ገና›› በትንቢተ ነቢያት የተነገረለት የሰው ልጆችን በጥንተ-ተፈጥሮ የፈጠረ የእግዚአብሔር ልጅ ሰውን ለማዳን ሰው ሆኖ የተወለደበት ቀን ነው ፡፡

በዘመነ ሄሮድስ የንግሥና ዘመን የይሁዳ ክፍል በነበረችው የቤተልሔም ከተማ ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ከበስተምሥራቅ የመጡ ጥበበኞች ሕጻኑን ለማየት አለበት ከተባለ ሰፍራ ገሰገሱ። ሳጥናቸውን ከፍተውም የእጃቸውን ስጦታ አበረከቱለት ፡፡

እነኚህ የሰባሰገል ሰዎች ወርቅ፣ ዕጣንና ከርቤ ይዘው ነበር፡፡ ጥበበኞቹ ከሠረገላ ፈረሳቸው ወርደው ወደ ግርግሙ ባመሩ ግዜ ከእናቱ ዕቅፍ ለነበረው ሕጻን ጎንበስ አሉ፡፡ ተንበርክከውም ሰገደሉት፡፡

**በሀገራችን የገና በዓል አከባበር ጥንታዊ መሠረት አለው። በተለይ በገጠሩ ክፍል ወጣቶች በያዕቆብ በትር ተምሳሌት የሚሆን የተሸለመ ዱላና ሩር በመያዝ የገና ጨዋታን በሜዳ በመስኩ ተጫውተው ያሳልፉታል**

በየዓለማቱ ያሉ ሀገራት የገናን በዓል በተለያየ ባሕልና ልማድ ያከብሩታል፡፡ አብዛኞቹ ገና ከመድረሱ በፊት የሚኖሩትን ጥቂት ቀናት በጾምና ጸሎት የሚያሳልፉ ናቸው፡፡ በዩክሬን በዓሉ ከመድረሱ ጥቂት ቀናት አስቀድሞ በየቤቱ እየዞሩ ገናን በዝማሬ የመቀበል ልማድ አላቸው፡፡

ቤሉሩሲያውያንም ዕለቱን ቂጣና ዓሣ በማዘጋጀት በተለየ ደስታ ያሳልፉታል፡፡ በሞንቴግሮ ሳንቲም ያለበት የድፎ ዳቦን ማዘጋጀት የተለመደ ነው፡፡ ዳቦው ሲቆረስ ሳንቲሙን ያገኘ ሰው ዕድሉ የተቃና ይሆንለታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በሩሲያ የሚገኙ ክርስቲያኖች ደግሞ ከአዲስ ዓመት መባቻ ጀምሮ እስከ ዕለተ ገና ድረስ ያሉትን አስራ ሁለት ቀናት የተለያዩ ምግቦችን በመመገብ የሚያሳልፉ ናቸው፡፡ የአስራ ሁለቱ ቀናት ተምሳሌትም አስራ ሁለቱን ሐዋርያት በማስታወስ ለመዘከር እንደሆነ ይነገራል ፡፡

በሰርቪያ የገና በዓል የሚከበረው ከጫካ እንጨት ቆርጦ በማምጣት እንጨቱን በማንደድና በዙሪያው ተሰባስቦ ጣፋጭ ራትን በመብላት ነው፡፡ ጆርጂያውያንም ከቤት ወደ ጎዳና በመውጣት የክርሰቶስን ልደት በተለየ ደስታና ዝማሬ ይቀበሉታል፡፡

በዓለማችን አውሮፓና አሜሪካን ጨምሮ በርካታ የክርስትና ዕምነት ተከታይ ሀገራት የገናን በዓል በድምቀት ያከብራሉ፡፡፡ እነዚህ ሀገራት የከርስቶስን የልደት ቀን የሚያከብሩት ከዘመን መለወጫቸው አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ በታኅሣሥ ወር አጋማሽ ላይ ነው፡፡

ከአፍሪካ ደግሞ ኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ግብፅ ዕለቱን ታኅሣሥ 29 ላይ አስበው ያከብራሉ፡፡ በነዚህ ሀገራት የገና ዕለት በአንድ የመመሳሰሉ ምክንያት ሁሉም የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን በመከተላቸው ነው ፡፡

ከክርስቶስ ልደት በፊት ዓመቱን በሙሉ አረንጓዴ ለሚሆኑት ዛፎች የተለየ ክብር ይሰጥ ነበር፡፡ በወቅቱ እነዚህ ዛፎች ርኩሳት መናፍስትን፣ አስማተኞችንና በሽታን በሙሉ የማጥፋት ኃይል እንዳላቸው ሲታመንበት ቆይቷል፡፡

አብዛኞቹ አረማውያን ዛፎቹን እየቆረጡ በየበራቸውና አጥሮቻቸው ላይ ይሰቅሉ ነበር፡፡ ከሁሉም ደግሞ አይሼሪያውያን የተባሉት የደኖቹን ዛፎች እስከማምለክ መድረሳቸው ይነገራል፡፡

ሰዎቹ ለዛፎቹ ክብራቸውን ለመግለጽ ወደቤታቸው በማምጣት በተለዩ ጌጣጌጦች ያስውቧቸው ነበር፡፡ ይህ ልማድ ዋል አደር ሲል ስያሜው ተቀየረ፡፡ ከገና በዓል መከበር ጋር ተያይዞም ወደ ቤተክርስቲያን የመግባት አጋጣሚውን አገኘ፡፡

ከገና በዓል መከበር ጋር የተለመደው የስጦታ መለዋወጥ ልማድም የራሱ መነሻ ታሪክ አለው፡፡ በ19ኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ በቱርክ የተወለደውና ከስሙ በፊት ‹‹ቅዱስ›› የሚል መጠሪያን የተቸረው ሊቀጳጳሱ ኒኮላስ ታላቅ ክብር የተሰጠው ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው ከገና አባት ጋር ስሙ ቢነሳም በአብዛኞች ዘንድ የባዕድ አምልኮ መሠረት እንዳለው ይታመንበታል፡፡

ታሪክ እንደሚያረዳው በዘመኑ የነበረች የአሮማውያን አማልዕክት ከስፍራው ተወግዳ ቦታው በኒኮላስ አማልዕክት ከተተካ ወዲህ የእሱ ተከታዮች መብዛታቸው ይነገራል፡፡ ይህ ሰው የአማልክቷን ቦታ ከያዘ በኋላ የስጦታዎች መለዋወጥ ተስፋፋ፡፡ የኒኮላስ ተከታዮችም ወደን የተባለና ነጭ ጢም ያለው በዓመት አንድ ጊዜ በሰማይ ይጋልባል የሚባልለትን አማልዕክት ያመልኩ ነበር፡፡

በሀገራችን ከዚህ የአምልኮ ታሪክ ጋር የተያያዘ አንዳች ግንኙነት የለም፡፡ ይሁን እንጂ የገና በዓልን አስመልክቶ የስጦታ መለዋወጥ ልማድ በበጎነት የተወረሰ ባሕል ሆኖ አሁንም ድረስ ይተገበራል፡፡

በኢትዮጵያ የልደት በዓል በየዓመቱ ታኅሣሥ 29 ቀን በድምቀት ይከበራል፡፡ ይህ ቀን ግን ልክ እንደ ዘንድሮ በአራት ዓመት አንዴ ታኅሣሥ 28 ላይ የሚውልበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ እንዲህ ለመሆኑ ምክንያቱ በዘመነ ዮሐንስ የጳጉሜ ወር ከአምስት ይልቅ ስድስት ቀናትን ስለምታስቆጥር ነው፡፡

በሀገራችን የገና በዓል አከባበር ጥንታዊ መሠረት አለው፡፡ በተለይ በገጠሩ ክፍል ወጣቶች በያዕቆብ በትር ተምሳሌት የሚሆን የተሸለመ ዱላና ሩር በመያዝ የገና ጨዋታን በሜዳ በመስኩ ተጫውተው ያሳልፉታል ፡፡

በዚህ ቀን በገናው ሩር አንዱ ሌላውን ቢመታ፣ ቢፈናከት መቀያየም መኮራረፍ አይኖርም፡፡ ሁሉም እንዳሻው ሊሆን ተፈቅዶለታልና ‹‹በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ›› ይሉት እውነት ተተግብሮ ይታያል። የገና በዓል በሀገራችን በድምቀት ከሚከበሩ ቀናት ዋንኛው ነው፡፡ በዚህ ቀን ቤተሰብ፣ ጓደኛና፣ የሥራ ባልደረቦች ስጦታ የመለዋወጥ ልማድን አዳብረዋል፡፡

ቀደም ሲል ዕለቱን ለማድመቅ በየቤቱ በተፈጥሮ ጽድ የሚዘጋጅ የገና ዛፍ የሚጌጥበትና በተለየ ደስታ ሁሉም የሚያከብርበት ተሞክሮ ነበር፡፡ በፅድ ዛፍ የማክበር ልማድ አሁን እየቀረ ቢሆንም እሱን በሚተካ የሰው ሠራሽ ዛፍ በመብራትና በጌጣጌጦች ተውቦ በየቤቱ፣ በየሆቴሉና በታዋቂ ስፍራዎች ደምቆ የመታየቱ ልማድ ለበዓሉ የልዩ ውበት ማሳያ ነው፡፡

ገና የእየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀን በመሆኑ ሕጻናት በተለየ ጉጉት ይጠብቁታል፡፡ ይህን ዕለት ለማክበርም ደማቅና አሸብራቂ የማስዋቢያ ቁሶችን መጠቀም ምርጫቸው ነው፡፡

የገና በዓል በሀገራችን ታላቅ ተብለው ከሚከበሩት ዓውደ ዓመቶች መሐል አንዱ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ አብዛኛው ሕዝበ ክርስቲያን በጾም በፀሎት የሚቆይበት በመሆኑ ዕለቱን በዕርድና በተለየ ዝግጅት የማሳለፍ ልማድ አለው፡፡

ይህ አጋጣሚ ብዙኃንን በማኅበራዊ ሕይወት ያስተሳስራል፡፡ ጉርብትናን አብሮ መኖርን፣ ተጠራርቶ መብላት መጠጣትን በማጉላት ኢትዮጵያዊነትን በጉልህ ያደምቃል፡፡ በዚህ ግዜ ‹‹በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ›› ይሉት አባባል ትርጉም አለው፡፡ ለመላው የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች በሙሉ መልካም የገና በዓል ይሁን፡፡

# የቀጣናውን ሀገራት ለአዲስ የትብብር መንፈስ የሚያነቃቃ ስምምነት

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

የኢትዮጵያን ቀጣይ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና ማኅበራዊ አቅጣጫ ይወስናሉ ተብለው በግንባር ቀደምትነት ከተቀመጡ ቁልፍ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የባህር በር ነው፡፡ ሀገሪቱ ሰፊ የሕዝብ ቁጥር ባለቤት ነች። በአፍሪካ የተነቃቃ የኢኮኖሚ ባለቤት መሆኗም ተደምሮበት የባህር በር ይህንን እድገት ሳይንገራገጭ ለማስቀጠል ወሳኝ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡ ከወራት በፊት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የባህር በር ኢትዮጵያ እንደሚያስፈልጋት በመግለፅ ጥያቄው ይፋ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ በብዙዎች ዘንድ መነጋገሪያ ሆኖ ሰንብቷል፡፡

ለአንድ ሀገር ሕዝብና ትውልድ የእድገትና የስልጣኔ መንገድ ጠራጊ ተደርገው ከሚወሰዱት ውስጥ አንዱ የባህር በር ነው፡፡ 22 ከመቶ ገደማ ያክሉ የኢኮኖሚ መነቃቃት በዚህ የወደብ የገበያ ልውውጥ በኩል የሚመጣ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ነው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በጠንካራ መሠረት ላይ ለማቆም እንዲያስችል ኢትዮጵያ የባህር በር አጀንዳን ወደፊት ያመጣችው። ላለፉት ጥቂት አስርት ዓመታትም ማኅበረሰባችን ቀደምት ታሪኮችን በመጥቀስ የባህር በር ፍላጎቱን ሲያንፀባርቅ ቆይቷል።

ከሰሞኑ አጀንዳውን ወደፊት አምጥቶ ከመወያየት የዘለለ የተግባር ርምጃም ተወስዷል። ይህንን ተከትሎም በኢትዮጵያና በሱማሌ ላንድ መንግሥት በኩል ታሪካዊ የሁለትዮሽ ስምምነት በወደብ ጉዳይ ተፈርሟል። ይሄንኑ እውነታ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት በተሰማ መግለጫ አረጋግጠናል። ስምምነቱ ኢትዮጵያ የባህር በር የምታገኝበትን መንገድ ከመጥረጉም ባለፈው ጥያቄው ሕጋዊና ትክክል እንደሆነ ማረጋገጫ የሚሰጥም ጭምር ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የሶማሌ ላንድ ፕሬዚዳንት ሙሴ ቢሂ አብዲ ታሪካዊ ነው በተባለው የመግባቢያ ሰነድ ላይ በመዲናችን አዲስ አበባ ፊርሚያቸውን አኑረዋል፡፡ የሰነዱ አስፈላጊነት የትብብርና የአጋርነት መንፈስን ከማስረጽ ጎን ለጎን በተለያዩ ዘርፎች ማለትም፤ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ግንኙነት የሚያጠናክር ነው፡፡

የመግባቢያ ሰነዱ ኢትዮጵያ ካነሳችው የባህር በር ጥያቄ አንጻር ፋይዳው ላቅ ያለ ስለመሆኑም በስፋት እየተነገረም ነው። የሀገሪቱን የባህር በር የማግኘት መሻት ተጨባጭ የሚያደርግ፣ የወደብ አማራጮችን የሚያሰፋ፣ የሁለቱን ሀገራት የዲፕሎማሲ፣ የጸጥታ የሚያጠናክር ነው፡፡ ለምሥራቅ አፍሪካ ሆነ ለአፍሪካ ሀገራት አዲስ የትብብር መነቃቃትን የሚፈጥርም እንደሚሆን በስፋት እየተነገረ ነው፡፡

በፊርማ ሥነ ሥርዓቱ ላይ፣ የሶማሌ ላንድ ፕሬዚዳንት ሙሴ ቢሂ አብዲ ‹ኢትዮጵያ ከስምምነቱ በኋላ ለሶማሌ ላንድ ነፃ የሀገርነት እውቅናን የምትሰጥ የመጀመሪያዋ ሀገር እንደምትሆንና በምላሹ ሱማሌላንድ ደግሞ ኢትዮጵያ የባህር በር እና የባህር ኃይል ቤዝ እንዲኖራት በቀይ ባህር በኩል 20 ኪሎ ሜትር ርቀትን የሚሸፍን መሬት በሊዝ እንደምትሰጥ የተናገሩበት ሁኔታ ነበር፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶር) እንኳን ለኢትዮጵያ ስብራት ጥገና ቀን በጋራ አደረሰን፤ አደረሳችሁ፤ በተደጋጋሚ ለሕዝባችን በገባነው ቃል መሠረት ኢትዮጵያ ካሏት ዋና ዋና ስብራቶች መካከል አንዱ ቀይ ባህርን የመጠቀም በዛውም የማልማት ፍላጎት ከሱማሌላንድ ወንድሞቻችን ጋር በተደረገ የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመናል» ሲሉ እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል፡፡

**22 ከመቶ ገደማ ያክሉ የኢኮኖሚ መነቃቃት በዚህ የወደብ የገበያ ልውውጥ በኩል የሚመጣ ነው**

ስምምነት ተከትሎ የሶማሌላንድ የኢንፎርሜሽን ሚኒስትሩ አሊ ሀሰን ሞሀመድ ‹‹ታሪክ እየተሰራ ነው። ይህ ጨዋታ ቀያሪ ትልቅ ትርጉም ያለው ስምምነት ነው፡፡ ትልቅ እና ወኔ የሚጠይቅ ርምጃ ነው። ወደፊት ለሁለቱ ሀገራት የብሩህ አድማስ በሮችን የሚከፍት ነው›› ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

ይህ በሁለቱ ሀገራት መካከል አዲስ ምዕራፍ ከፋች ስምምነት በኢትዮጵያ በኩል ራሱን እንደቻለ ተስፋ ሰጪ ጅማሮ ሊታይ የሚገባው ነው። በባህር በር የይገባኛል ጥያቄ በኩል ቀጣይ ተጨባጭ አቅጣጫዎችን እንድናማትር እድል ሊሰጥ የሚችል ጭምር ነው፡፡ በሰጥቶ በመቀበል፣ ተካፍሎ በመብላት፣ በመጋራትና በማጋራት መርህ ላይ የተመሠረተው የሀገራችን አስተማማኝና ቀልጣፋ የወደብ አማራጭ የማግኘት ጥያቄ፤ አሁን ላይ ይዞት የመጣው ተስፋ ሰጭ ውጤት፤ በቀጣይም በተመሳሳይ መልኩ ተጨማሪ ወደቦችን ማግኘት የሚያስችል ክስተት ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ለዚህም፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ‹‹ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ እንዳነሳነው እኛ ያሉንን ሀብቶች የመጋራት፣ የመካፈልና በጋራ የመልማት ፍላጎት እንጂ ማንንም በኃይል የማስገደድ ፍላጎት የለንም ስንል የነበረው ሃሳብ ወደተግባር ተቀይሮ ዛሬ በፈረንጆቹ አዲስ ዓመት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ለሶማሌ ሕዝብ የምናበስረው የምስራች ሆኗል›› ሲሉ በሁለትዮሽ ስምምነቱ ወቅት የተናገሩትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ዛሬም ካለን ላይ እየሰጠን፣ የሚገባንን እየጠየቅን በትላንቱ የአባቶቻችን ዳና ላይ መቆየት ይገባናል። እንደ ሕዝብ ነውር እና ይሉኝታ የምናውቅ ሕዝቦች ነን። ዘመናዊነትን ከባህልና ከሥርዓት ጋር አቻችለን መኖር የሚያስችሉን እሴቶች ባለቤት ነን፡፡ ትላንት ዛሬም የምንታወቅበት በዚሁ ነው፡፡ ከሰሞኑ የተደረገው የሰጥቶ መቀበል መርህም ከዚሁ እሴታችን ጋር የተቆራኘ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። እዚህ ጋር የሚከተለውን ምሳሌ ታሪክን አጣቅሰን ማንሳት ይገባናል።

የእስልምና ሃይማኖት መስራቹ ነብዩ መሀመድ በአረብና በሌሎች ሀገራት የሚሳደዱ ተከታዮቻቸውን ‹‹ወደ ኢትዮጵያ ሂዱ። እዛ ሰው የማይበድል ራሱም የማይበደል መንግሥትና ሕዝብ አለ›› ብለው እንደላኳቸው እናስታውሳለን፡፡ በሽሽት ወደ ሀገሪቱ ከገቡ በኋላም የወቅቱ ንጉስ በኢትዮጵያዊ ሥነ ሥርዓት በእንግዳ ተቀባይነት መንፈስ እንደተቀበላቸው የታሪክ ሰነድ አገላብጠን ማግኘት እንችላለን፡፡ ከዚህ ታሪክ ቀደም ባሉት ግዚያት ጭምር በትብብር፣ በጋራና በአብሮነት ስሜት ከሰው ልጆች ጋር መኖር እንደምንችል እንማራለን። ዛሬ እኛ ለኢኮኖሚ እድገታችን፣ ለዓላዊነት ዘብ የሚሆን የባህር በር ትንፋሽ ስንፈልግ ደግሞ በዚሁ የመተባበር መንፈስ በዲፕሎማሲና ውይይት ልናሳካው ችለናል።

ሌላው በትብብርና በሰጥቶ መቀበል መርህ እንደምንሰራ ምሳሌ የሚሆነን ጉዳይና የባህር በር ጥያቄ ጋር የሚመሳሰለው አጀንዳ የዓባይ ግድብ ነው። ይህንን ታላቅ የኃይል አቅርቦት ፕሮጀክት ያለ አንዳች የውጭ ኃይል ድጋፍ በሕዝባችን ሕብረት ስንገነባ እራሳችንን ብቻ አስበን አይደለም። ይልቁኑ ቀጣናውን በኃይል አቅርቦት ለማስተሳሰርና በጋራ ለማደግ ነበር።

ጎረቤት ሀገራት ሰፋፊ የባህር በር ባለቤት ቢሆኑም ጥያቄያችንን በይፋ እስክናቀርብ ድረስ ማናቸውም በገፀ በረከትነት አላቀረቡልንም። እኛ ግን የዓባይን ግድብ ፕሮጀክት ‹‹የጋራችን ነው›› እናም በጋራ አስበን፣ በጋራ መክረን በጋራ እንልማ›› በሚል ሚዛናዊነትን ያስቀደመ አስተሳሰብን አንስተናል። ከነዚህ ሁለት እውነታዎች ተነስተን ለፍትህ፣ ለእውነትና ለሚዛናዊነት ያለንን ቦታ መረዳት ይቻላል። ዛሬም ከሶማሌ ላንድ ጋር ያደረግነው ስምምነት ይህንን መነሻ ያደረገ መርህ ላይ የቆመ ነው።

ጥያቄያችን እንደ መንግሥት ወቅቱን የጠበቀ፣ እንደ ሕዝብ ደግሞ ይገባናልን ያስቀደመ እንቅስቃሴ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ በጣም የሚገርመው ደግሞ ታሪክና ተፈጥሮ ካቋደሱን (ዓባይና ቀይ ባህር) ጸጋዎቻችን ሳንጠቀም በረከቶቻችንን ለሌሎች አሳልፈን የሰጠን መሆናችን ነው። እኛ ‹‹ወቅታዊ የባህር በር ጥያቄያችንን መልሱ ወይም ደግሞ እናንተ እስካሁን ተጠቅማችኋል፤ አሁን የኛ ተራ ነው። ስንበላ ቆማችሁ እዩን›› ሳይሆን የጋራ ‹‹የተፈጥሮ ፀጋዎችን በጋራ እንጠቀም›› የሚል ነው፡፡

በሕዳሴ ግድብ በኩል ታሪክ የሚዘክረውን የጀብደኝነት ተግባር ፈጽመን ዓባይን ገድበናል፡፡ ብዙ ርቀትን ተጉዘን እውነት በማይመስል ታሪክ በኩል ለትንሳኤ መቃረባችን ይታወቃል፡፡ በቀይ ባህር በኩል ደግሞ የይገባኛል ጥያቄ ሰንዝረን ከተጋሪ ሀገራት ጋር ለውይይትና ለተግባቦት በርና ልባችንን ከፍተን እየጠበቅን ነው፡፡ የሰሞኑ የሶማሌ ላንድ የሁለትዮሽ ስምምነትም የዚሁ አካል ነው፡፡

በሂደት በሁለቱም ተፈጥሯዊ ጸጋዎቻችን በኩል ከተጋሪነት ባለፈ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ በተጽዕኖ ፈጣሪነትም ዳብረን ሀገርን ከድህነት፣ ሕዝብን ከተረጂነት አላቀን በሁለት እግራችን ቆመን የጥንቱን ታሪካችንን የምናድስበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም፡፡ ዓባይን ከይገባኛል ጥያቄ ተነስተን እንደገደብነው ይታወቃል። በታሪክም በሕግም ፍትሀዊ የሆነው የባህር በር ጥያቄም ሙሉ ለሙሉ ምላሽ አግኝቶ የከፍታዎቻችን አብሳሪ አቅም እንደሚሆኑ እናምናለን፡፡

አንድም በሕዳሴ ግድብ አንድም በባህር በር የይገባኛል ጥያቄ በኩል የትንሳኤ ጮራ በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ እየፈነጠቀ ነው፡፡ በፖለቲካም ሆነ በቅኝ ገዢዎች ሴራ፣ በአቅም ማጣትም ሆነ በግዛት መጥበብ መነሻነት የከፍታዎቻችንን ማማዎች አጥተናቸው ብዙ ዘመናት በድህነት ማቅ ውስጥ ከርመናል፡፡ አሁን ጊዜው የቀደመ ሥልጣኔያችንን እና ኃያልነታችንን የምናስመልስበት፣ ኢትዮጵያዊነትን ከብዝሀነት ጋር ቀይጠው ገናናነትን ያሰጡንን ተፈጥሯዊ ጸጋዎቻችንን በነፃነት የምንጠቀምበት፣ በውይይትና በድርድር ወደሁነኛ የአብሮ ማደግ መርህ ውስጥ የምንገባበት ነው፡፡

የባህር በር ይገባኛል ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ አግኝቶ ወደሥራ ሲገባ ቀጣዩ የኢኮኖሚ አቀጣጣይ ሆኖ የልማት አርበኝነቱን ይወስዳል፡፡ ይሄ ማለት በየጊዜው ለሚጨምር የሕዝብ ቁጥርና የፍላጎት መናር እንደሁነኛ መፍትሔ የሚወሰድ ይሆናል፡፡ ከመነሻው የይገባኛል ጥያቄውንም የፈጠሩት ከሕዝብ ቁጥርና ከፍላጎት መናር ጋር የማደግ ምኞትን ያነገቡ እኚህ ወቅታዊ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

ከሶማሌ ላንድ ጋር የተደረገው የመግባቢያ ስምምነት መሬት እንዲወርድና ተግባር ላይ እንዲውል ሁላችንም መሥራት ይጠበቅብናል። ይህንን የኢትዮጵያን የማደግ ፍላጎት የሚያረጋግጥ አጀንዳ የሚያሰናክሉ የሴራ ትንታኔዎችን፣ አደናቃፊ ኃይሎችን ችላ ብለን ሙሉ ትኩረታችን ስምምነቱን ሙሉ ለሙሉ ማስፈፀም ላይ ማድረግ ይጠበቅብናል።

በጀመርናቸው በትላልቆቹ ማርሽ ቀያሪ የዓባይ ግድብ የመነቃቃት መንፈስ፤ በጀመርነው የባህር በር የማግኘት ተግባራዊ ርምጃ በኩል ድህነትና ኋላቀርነትን ተሰናብተን ከአዲስ የእድገትና የለውጥ መሻታችን ጋር እንደምንወዳጅ የብዙዎቻችን እምነት ነው፡፡ ለውጥ የብዙኃነት ነጸብራቅ ነውና ለጀመርናቸውም ሆኑ ልንጀምራቸው ላሰብናቸው ሀገራዊ እቅዶች ጠጠር ማዋጣት ከሁላችን የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። ሰላም!!

# ማህደረ ጤና

# ቫይረሱን ለመግታት የማኅበረሰብ መሪነት

**አስናቀ ፀጋዬ**

ኢትዮጵያ የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዎችን በማጠናከር፣ ቅንጅታዊ አሠራርን በማጎልበት፣ መንግሥታዊ እና ዓለም አቀፍ ተቋማትን፣ አጋር ድርጅቶችን፣ ሲቪክ ማኅበራትን እና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ወረርሽኙ በማኅበረሰቡ ጤናና በሰብዓዊ ደህንነት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገቧ በሚመለከታቸው ሁሉ የተመሰከረለት አፈፃፀም ነው።

ለአብነትም የኤችአይቪ ስርጭት ምጣኔን እ.ኤ.አ በ2010 ከነበረበት 1 ነጥብ 26 ከመቶ፣ እ.ኤ.አ በ2022 ወደ 0 ነጥብ 91 ዝቅ ማድረግ ተችሏል። ኤችአይቪ በደማቸው ይገኛል ተብለው ከሚገመቱ ወገኖች መካከል 84 ከመቶ የሚሆኑት ተመርምረው ራሳቸውን እንዲያውቁ፣ ከእነዚህ ውስጥ 98 በመቶ ያህሉ ደግሞ የፀረ ኤችአይቪ መድኃኒት እንዲጠቀሙና መድኃኒት ከሚወስዱት ውስጥ 96 ነጥብ 3 በመቶ ያህሉ የቫይረስ ልኬት መጠን በሚፈለገው ልክ እንዲወርድ ተደርጓል።

በሌላ በኩል በዓመት ውስጥ የሚኖረውን በኤድስ ምክንያት የሚከሰትን የሞት መጠን እ.ኤ.አ ከ100ሺህ 125 ሰው፣ እ.ኤ.አ በ2022 ከ100ሺህ ሰው ወደ 11 በማውረድ ከ52 ከመቶ በላይ እንዲቀንስ ማድረግ ተችሏል። በተመሳሳይ ቫይረሱ በደማቸው ከሚገኝ እናቶች የሚወለዱ ሕፃናት የምርመራና ሕክምና አገልግሎት በወቅቱ እንዲያገኙ ለማድረግ የማፋጠኛ እቅድ በማዘጋጀት በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል።

ኤችአይቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ እነዚህ ሥራዎች ተሠርተው ውጤት የመጣ ቢሆንም፤ አሁንም ተጨማሪ የቤት ሥራዎች እንዳሉና በተለይ የቫይረሱ የስርጭት ምጣኔ ከክልል ክልልና ከከተማ ከተማ የሚለያይ እንደመሆኑ በዋናነት በከተሞች አካባቢ ጠንከር ያለ ሥራ መሥራት እንደሚጠይቅ መረጃዎች ያመላክታሉ። ለምሳሌ በከተማ የቫይረሱ ስርጭት መጠን ከፍተኛው ጋምቤላ በ3 ነጥብ 69 በመቶ፣ አዲስ አበባ 3 ነጥብ 47 በመቶ፣ ሐረሪ 2 ነጥብ 97 በመቶ፣ ድሬዳዋ 2 ነጥብ 9 በመቶ እና ዝቅተኛው ሶማሌ 0 ነጥብ 18 በመቶ መሆኑን ከተለያዩ መረጃዎች ለመመልከት ተችሏል። የኤችአይቪ ስርጭት ጥቅል ምጣኔ በከተማ 2 ነጥብ 9 በመቶ፤ እንዲሁም በገጠር 0 ነጥብ 4 በመቶ እንደሆነም እነዚሁ መረጃዎች ያሳያሉ።

ኤችአይቪን በመከላከል ረገድ የማኅበረሰቡን ሚና ለማጉላትና አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎችም ከተሞች እየጨመረ የመጣውን የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት የዓለም ኤድስ ቀን ‹‹የማኅበረሰብ መሪነት ለላቀ ኤችአይቪ መከላከል›› በሚል መሪ ቃል በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ35ኛ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ ለ36ኛ ጊዜ በቅርቡ መከበሩ ይታወሳል። ከዚሁ ጎን ለጎን የቫይረሱ ስርጭት በአዲስ አበባ ከተማ እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ በርብርብ መሥራት እንደሚጠበቅ ተነግሯል።

የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ እንደሚናገሩት ኤችአይቪ/ኤድስ ዓለም አቀፍ ችግር መሆኑ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ዓለም አቀፍ ምላሽ ለመስጠት የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። በተወሰዱትም የተቀናጁ ምላሾች ለውጥ ማምጣት ተችሏል። የዓለም አቀፉ ዘርፈ ብዙ የተቀናጀ ምላሽ አሰጣጥና ስልትን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ማኅበረሰብ አቀፍ የኤችአይቪ/ኤድስ ስርጭትና በአዲስ የመያዝ ምጣኔ እንዲሁም በኤድስ ምክንያት ከሚከሰት ሞትና ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅኅኖ አንፃር ትርጉም ያለው ውጤት ማስመዝገብ ስለመቻሉ የተለያዩ ጥናቶችና ሪፖርቶች ያሳያሉ።

የኤችአይቪ ስርጭትን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራው በተጠናከረ ሁኔታ ቀጣይነት እንዲኖረውና በጤናው ዘርፍ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት ያስችል ዘንድ ማኅበረሰቡን በግምባር ቀደምትነትና በባለቤትንት የሚመሩ የኤችአይቪ/ኤድስ የንቅናቄ መድረኮችን እያዘጋጁ ሚናቸውን እንዲወጡ ማስቻል ይጠበቃል።

በአውሮፓውያኑ የጊዜ ቀመር መሠረት በየዓመቱ ታኅሣሥ 1 የዓለም የኤችአይቪ/ኤድስ ቀን ሆኖ እንዲከበር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከወሰነበት ግዜ ጀምሮ እለቱ በልዩ ልዩ መሪ ቃሎችና ዝግጅቶች በየዓመቱ እየተከበረ ይገኛል። ከበዓሉ አከባበር ጋር በተያያዘም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኤችአይቪ/ኤድስ የጋራ ፕሮግራም በየዓመቱ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ መሪ ሃሳቦችና አጀንዳዎችን እየቀረፀ በመላው ዓለም በይበልጥ ትከረት ተደርጎ እንዲሠራባቸው ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም ዓመት ‹‹የማኅበረሰብ መሪነት ለላቀ የኤችአይቪ መከላከል›› በሚል መሪ ቃል የሃሳብ ንቅናቄ በመፍጠር የአገልግሎቱን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ሰፊ የማኅበረሰብ ተሳትፎ ያደርጋል።

እንደ ኃላፊው ገለፃ ኤችአይቪ/ኤድስ የማኅበረሰብ ጤና ችግር ከመሆን አልፎ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነ-ልቦናዊና የሥነ ሕዝብ ችግር ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል። ችግሮቹም ውስብስብና ዘርፈ ብዙ በመሆናቸው ስትራቴጂ ተነድፎ ዘርፈ ብዙ ምላሽ ሲሰጥ በመቆየቱ አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ ቢቻልም አሁንም ኤችአይቪ/ኤድስ የከተማዋ (አዲስ አበባ) የጤና፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስጋት ስለሆነ በቀጣይ የቫይረሱን ስርጭት ለመግታትና ተፅዕኖዎቹንም ለመቆጣጠር የሚደረገውን ማኅበረሰብ መር ተሳትፎ አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮም የኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭት በኅብረተሰቡ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባሩን ከሕክምና አገልግሎቱ ጋር በቅንጅት እየመራና ኅብረተሰቡን ማዕከል ያደረገ የመከላከልና የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት በዘላቂነት መሠረት ለመጣል ከባለድርሻ አካላት ጋር ሆኖ እየሠራ ይገኛል።

በዓለም አቀፍና በሀገር አቀፍ ደረጃ እ.ኤ.አ በ2030 ኤድስን ለመግታት የተያዘውን ግብ ለማሳካት በየምዕራፉ የሚከናወኑ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማጠናከር የተቀመጡትን ሦስት ግቦችን ለኤችአይቪ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን 95 ከመቶ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለውን ደረጃ እንዲያውቁ የማድረግ፣ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ እንዳለ ካወቁት ደግሞ 95 ከመቶዎቹ መድኃኒት እንዲጀምሩ የማድረግ፤ እንዲሁም መድኃኒት የጀመሩትና ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ 95 ከመቶ የኅብረተሰብ ክፍሎች በደማቸው ውስጥ ያለው ቫይረስ መጠን እንዲቀንስ የማድረግን ግብ ለማሳካት ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

ግቡን ለማሳካት በስትራቴጂ እቅዱ በተለይ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ ማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችና ፕሮግራሞች ተቀርፀው ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ። በመሆኑም የሀገሪቱ የኤችአይቪ/ኤድስ ስርጭት ከአጠቃላይ ማኅበረሰብ አንፃር ሲታይ 0 ነጥብ 91 በመቶ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ከተማ ደግሞ የስርጭት ምጣኔው 3 ነጥብ 47 ሆኗል። የኢትዮጵያ የኤችአይቪ/ኤድስ ስርጭት ከአጠቃላይ ተጋላጭ የማኅበረሰብ ክፍሎች አኳያ ሲታይ 23 በመቶ ነው።

በሀገሪቱ ኤችአይቪ በደማቸው ያለባቸው ሰዎች 610ሺህ 350 ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከል 61 ከመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። እ.ኤ.አ በ2022 ብቻ 8ሺህ 257 ሰዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ አዲስ ኤችአይቪ ተይዘዋል። በአዲስ አበባ ከተማ ደግሞ 489 ሰዎች አዲስ በቫይረሱ የተያዙ ናቸው። በአዲስ አበባ ከተማ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የሚገኝባቸው ወገኖች 112ሺህ 185 ሲሆኑ፣ ከዚህ ውስጥ 3ሺህ 206ዎቹ ህፃናት ናቸው። ይህም ምጣኔው 2 ነጥብ 8 ከመቶ መሆኑን ያሳያል። 68ሺህ 240፤ ወይም 61 ከመቶ ያህሉ ኤችአይቪ/ኤድስ በደማቸው አለባቸው።

ኃላፊው እንደሚያብራሩት ኤችአይቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ከሌላው የሕክምና አገልግሎት ጋር ተቀናጅቶ በመሠራቱ የኤችአይቪ/ኤድስ ስርጭት ምጣኔን እ.ኤ.አ በ2010 ከነበረበት 1 ነጥብ 26 ከመቶ፤ እ.ኤ.አ በ2022 ወደ 0 ነጥብ 91 መቀነስ ተችሏል። በዚሁ መሠረት በኤችአይቪ/ኤድስ ምክንያት የሚከሰት ሞት ምጣኔ 125 ከ100ሺህ፣ ወደ 11 ከ100ሺህ ማውረድ ተችሏል። ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፈውን ኤችአይቪ ቫይረስ በተሠራ ጠንካራ ሥራ ከ46 በመቶ ወደ 12 በመቶ መቀነስ ተችሏል።

በ2020 ዓ.ም ከኤችአይቪ ነፃ የሆነ ትውልድ ለመፍጠር የተያዘውን ራዕይ እውን ለማድረግ አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡ የሚገኙ ቢሆንም ራዕዩን እውን ለማድረግ ሰፊ ሥራ መሥራት ይጠበቃል። በተለይ የዘንድሮው የዓለም ኤችአይቪ/ኤድስ ቀን ‹‹የማኅበረሰብ መሪነት ለላቀ የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከል›› በሚል መሪ ቃል የተከበረ እንደመሆኑ እለቱ ሲታሰብ ኤችአይቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ለሚገኙ ወገኖች አጋርነትን ማሳየት ያስፈልጋል። ቫይረሱ በሰው ልጅ ጤናና በማኅበረሰቡ ላይ የሚያስከትለውን ዘርፈ ብዙ ችግር በዘላቂነት ለማስወገድ እ.ኤ.አ በ2030 ኤችአይቪ/ኤድስን ለመግታት የተያዘውን ግብ ለማሳካት ሁሉም ቃል መግባትና ቃሉን መፈፀም ይጠበቅበታል።

በቀጣይም የማኅበረሰቡን የመሪነት ሚና ለማጉላት የጤና ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ የተቀናጀ የኤችአይቪ/ኤድስ ስርጭትን ለመከላከልና ለሕክምና ሥራ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ባለድርሻ አካላት እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ተባብረው ሊሠሩ ይገባል።

ኢትዮጵያ በ1980ዎቹ መጨረሻና በ1990ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ የኤችአይቪ/ኤድስ ስርጭት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሮ ከታየባቸው ሀገሮች መካከል አንዷ ነበረች። ሆኖም በግዜው በኤችአይቪ መከላከልና መቆጣጠር ላይ ከታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል አንስቶ እስከ ላይኛው የመንግሥት መዋቅር ድረስ በተሠራ ከፍተኛ የንቅናቄና የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ የቫይረሱን ስርጭት በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ተችሏል።

ሆኖም ቀደም ሲል በተሠሩ ሥራዎች መርካትና ይህንኑ ተከትሎ በመንግሥትም ሆነ በሕዝቡ በኩል መዘናጋት በመፈጠሩ ኢትዮጵያ የኤችአይቪ/ኤድስ ስርጭት አደጋ እንዳለባት በርካታ ጠቋሚ ምልክቶች አሳይተዋል። ከዚህ በመነሳት እንደ ሀገርም ሆነ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በኤችአይቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ሥራ ላይ የማኅበረሰቡ የመሪነት ሚና ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ ከወዲሁ ብዙ ሥራ እንደሚሠራ ይጠበቃል።

**በ2020 ዓ.ም**

**ከኤችአይቪ ነፃ የሆነ ትውልድ ለመፍጠር የተያዘውን ራዕይ እውን ለማድረግ አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡ የሚገኙ ቢሆንም ራዕዩን እውን ለማድረግ ሰፊ ሥራ መሥራት ይጠበቃል**

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ልምድና ዕውቀትን በማጣመር የተጀመረ የንግድ ሥራ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ወላጅ አባቷ ረጅሙን የሕይወት ጉዟቸውን በተለያዩ የንግድ ሥራዎች አሳልፈዋል፡፡ ልጆቻቸው ግን ትኩረታቸውን ትምህርታቸው ላይ ብቻ እንዲያደርጉ በማሰብ በከፍተኛ ክትትልና ቁጥጥር አሳድገዋል፡፡ እሳቸው ከተሰማሩባቸው የንግድ ሥራዎች መካከል አንዱ በአነስተኛ መጭመቂያ ማሽን ዘይት አምርቶ መሸጥ ነበር፡፡ ‹‹በወቅቱ አባቴ የዘይት መጭመቂያ ማሽን በመጠቀም የምግብ ዘይት ከቅባት እህሎች አምርቶ ለገበያ ሲያቀርብ አስታውሳለሁ›› የምትለው የዕለቱ እንግዳችን ወይዘሮ መርየም ሳልህ ትባላለች፡፡

ከነጋዴ ቤተሰብ የተገኘችው ወይዘሮ መርየም ከትምህርትና ከቅጥር ሥራ በኋላ በወጪና ገቢ ንግድ ተሰማርታ መድኃኒቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ታስመጣለች፤ በምትኩ ደግሞ ማሾን ጨምሮ ጥራጥሬና የቅባት እህሎችን ለውጭ ገበያ በማቅረብ መድኃኒት ለማስመጣት የሚያስፈልጋትን የውጭ ምንዛሬ ፍላጎት ታሟላለች፡፡

‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራ በተለይም ኤክስፖርት ንግድ ብዙ ውጣ ውረድ ያለበትና እጅግ ፈታኝ ቢሆንም መሥራት የግድ ነው›› የምትለው ወይዘሮ መርየም፤ የንግድ ሥራን ከወላጅ አባቷ የወረሰች ስለመሆኑ ትናገራለች፡፡

ገና ልጅ እያለች ጀምሮ በንግድ ሥራ እንደምትሰማራ ታውቅ እንደነበርና ጓደኞቿም ወደፊት ነጋዴ እንደምትሆን ያመላክቷት እንደነበር የምታስታውሰው ወይዘሮ መርየም፤ በእሷ የንግድ ሕይወት ውስጥ የወላጅ አባቷ ድርሻ ትልቅ መሆኑንም ትናገራለች፡፡

እሷ እንዳለችው ፤ወላጅ አባቷ ሳይማሩ የተማሩ ጎበዝ ነጋዴ ነበሩ፡፡ ዘይት ጨምቀው ከመሸጥ ጀምሮ በሸቀጥ ሱቅ፣ በመኪና መለዋወጫና በሌሎችም የንግድ ሥራዎች ተሰማርተው ሰርተዋል፡፡ አነስተኛ በሆነች የዘይት መጭመቂያ ዘይት ጨምቀው በሚነግዱበት ወቅት ከመንግሥት በተጣለባቸው ከፍተኛ የግብር ጫና ምክንያት ማሽኑን ነቅለው ከሥራው ወጥተዋል። ቀጥለውም በሸቀጥ ንግድና በሌሎች የንግድ ሥራዎች የተሰማሩት ወላጅ አባቷ፣ ብርቱና ታታሪ ነጋዴ እንደነበሩ ትገልፃለች፡፡

የንግድ ሥራን ከወላጅ አባቷ እየተመለከተች ያደገችው ወይዘሮ መርየም፤ ‹‹ከንግድ ሥራው በተጨማሪ ብዙ የሕይወት ልምዶችንም ጭምር ከወላጅ አባቴ ተምሬያለሁ። ለዚህም ምክንያቱ ከሌሎች ልጆች በተለየ ሁኔታ አባቴን ስለምቀርበው ነው›› ትላለች፡፡ ከወላጅ አባቷ ያገኘችውን ልምድና ዕውቀት ተጠቅማ ከትምህርት በኋላ በሁለት ተቋማት ተቀጥሮ የመሥራት ዕድል የገጠማት ቢሆንም በተለይም ሁለተኛውን ሥራዋን የለቀቀችው ሳትወድ በግድ እንደነበር አጫውታናለች፡፡

ወይዘሮ መርየም በአዲስ አበባ ከሚገኘው የንግድ ስራ ትምህርት ቤት በሴክሬቴሪያት ሳይንስ እና በቢሮ አስተዳደር ዲፕሎማዋን፣ ሥራ ላይ እያለች ደግሞ የመጀመሪያ ዲግሪዋን በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አግኝታለች፡፡ ትምህርቷን በከፍተኛ ውጤት ታጠናቅቅ እንደነበር ያስታወሰችው ወይዘሮ መርየም፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀጥራ የሠራችው አሜዳድ በተባለ ድርጅት ውስጥ ነበር፡፡ በዚሁ ድርጅት ውስጥ የነበራት የሥራ ቆይታም ከአስር ወራት በላይ መሻገር አልቻለም፡፡

ሁለተኛውን የሥራ ዕድል ያገኘችው ደግሞ ከአንጋፋውና የአገር ኩራት ከሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ነው፡፡ በኢትዮጵያ አየር መንገዱ በነበራት የስራ ቆይታ ‹‹ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሯ ትሄዳለች›› እንደሚባለው ዝቅተኛ ከሚባለው የሥራ መደብ ጀምራ እያደገች በበርካታ የሥራ ኃላፊነቶችም ሰርታለች፡፡

ለአስራ አምስት ዓመታት በቆየችበት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ከብዙዎች በመማር ልምድና ዕውቀት በመቅሰም ራሷን አብቅታለች፡፡ ሥራዋን በሙሉ አቅሟና በትጋት ትሰራ እንደነበር ነው ያስታወሰችው፡፡

ይሁንና ባጋጠማት የቤተሰብ ችግር ምክንያት ረዘም ላለ ጊዜ ከሥራ ውጭ ሆና ትቆያለች፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድም ለረጅም ጊዜ ጠብቋት እንደነበር ገልጻ፣ እሷም ሳትፈልግ፣ ተቋሙም ማሰናበት የግድ ሆኖበት ተለያይተዋል፡፡

የአገር ኩራት ከሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከተተሰናበተች ከጥቂት ዓመታት በኋላ ከችግሯ ማገገም ስትችል ተመልሳ ወደ ቅጥር መሄድ እንደሌለባት በማመን የግል ሥራ መጀመር እንዳለባት ትወስናለች፡፡ በንግድ ስሙ ሜርሲ ሜድ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የተባለ ድርጅት መስርታ በአስመጪና የላኪነት ንግድ ሥራ ተሰማራች፡፡

በወቅቱ ወደ ግል ሥራዋ ለመምጣት ዙሪያ ገባዋን ስታማትር ቆይታ ወደ አስመጪነት ያቀናችው ወይዘሮ መርየም፤ ለሥራ ያላትን ፍላጎትና ቅልጥፍና እንዲሁም አስተዳደር ላይ በነበራት ብቃት ብዙዎች ያውቋታል፡፡ በመሆኑም ብዙዎች የግል ሥራዋን ስትጀምር አብረዋት ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጎትና ጉጉት እንደነበራቸው አጫውታናለች፡፡

የሜርሲ ሜድ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መስራችና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ መርየም፤ የንግድ ሥራዋን ለመጀመር መነሻ ካፒታል ያገኘችው ከባንክ በመበደር ነበር፡፡ በወቅቱ የግል ባንኮች የቤት መግዣ ብድር ያበድሩ እንደነበር ታስታውሳለች፡፡

ከአዋሽ ባንክ ባገኘችው ብድር የመድሃኒት አስመጪነት ፈቃድ በማውጣት የንግድ ሥራዋን ‹‹ሀ›› ብላ የጀመረችው የዛሬ አምስት ዓመት ነው፡፡ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎችን በመቅጠር የጀመረችው የመድሃኒት አስመጪነት ሥራ፤ እጅግ በጣም ጥንቃቄ የሚፈልግ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪን በወቅቱ የሚፈልግ በመሆኑ ሥራውን ፈታኝ ያደርገዋል ትላለች።

መድሃኒቶቹን ከአገር ውስጥ አምራቾችና ከውጭ በማስመጣት ለገበያ የምታቀርበው ወይዘሮ መርየም፤ አንድ መድሃኒት ሲጠፋ አልያም በቶሎ ወደ ሀገር ውስጥ ሳይገባ ሲቀር ውስጧ እጅጉን እንደሚያዝንም ትናገራለች፡፡ በመዘግየት ሂደት ውስጥ መድሃኒት አጥተው ሕይወታቸው የሚያለፍ ብዙ ሰዎች እንዳሉም ጠቅሳ፣ መድሃኒት ከፍተኛ ጥንቃቄና ትኩረት እንደሚፈልግ ትገልጻለች፡፡

እሷ እንደምትለው፤ በአገር ውስጥ የሚመረቱ የመድኃኒት አይነቶችን እንዲሁም ከውጭ የሚመጡ የተለያዩ መድሃኒቶችን አዲስ አበባ ከተማ ውስጥና በክልል ከተሞች ለሚገኙ ለጅምላ አከፋፋዮች ታስረክባለች። ከጅምላ አከፋፋዮች ደግሞ ቸርቻሪዎች ተረክበው በየአካባቢው በሚገኙ ፋርማሲዎች አማካኝነት መድሃኒቱ ማህበረሰቡ ጋር እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

ማህበረሰቡ እንዲጠቀምባቸው ወደ ገበያ የሚቀርቡት የመድሃኒት አይነቶች በየጊዜው የሚፈለጉ ናቸው፤ ከምታቀርባቸው መዳህኒቶች መካከል ማህበረሰቡ በየእለቱ የሚገለገልባቸው እንደ ስሪንጅ፣ ግላቭ፣ ማስታገሻ መድሃኒቶች፣ የስኳር እንዲሁም የደም ግፊት መድሃኒቶች ይገኙበታል፡፡

ወይዘሮ መርየም የህክምና ትምህርት ባይኖራትም በልምድ ከባለሙያዎች ጋር ባላት ቀረቤታና ለነገሮች በምትሰጠው ከፍተኛ ትኩረት መድሃኒቶችን ለይታ እንደምታውቅ ትናገራለች፤ ሥራውን ተላምዳ በተነሳሽነትና በጥንቃቄ እየሠራች መሆኗን አጫውታናለች፡፡

> **የህክምና ትምህርት ባይኖራትም በልምድ ከባለሙያዎች ጋር ባላት ቀረቤታና ለነገሮች በምትሰጠው ከፍተኛ ትኩረት መድኃኒቶችን ለይታ ታውቃለች፤ የመድኃኒት አስመጪነት ሥራውን ተላምዳ በተነሳሽነትና በጥንቃቄ እየሠራች ትገኛለች**

መርየም እንዳለችው፤ መድሃኒት የማስመጣት ሥራዋ ተጠናክሮ የቀጠለ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት በርካታ የተለያዩ መድሃኒቶችን ከአገር ውስጥ አምራቾችና ከውጭ በማስመጣት ለክልል ከተሞች ጭምር ተደራሽ ታደርጋለች፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ በተወሰኑ አካባቢዎች በተፈጠረው የሰላምና ጸጥታ ችግር ምክንያት መንገዶች ተዘጋግተው መድሃኒቶች በአግባቡና በፍጥነት እየደረሱ አይደለም የምትለው ወይዘሮ መርየም፤ ይህም በሥራው ላይ ከሚያሳድረው ጫና ባለፈ እጅጉን የሚያሳስባትና የሚያሳዝናት ጉዳይ መሆኑን ተናግራለች፡፡

መድሃኒት ማለት ሰዎች ለሚገጥማቸው የጤና ችግር መፍትሔ የሚሰጥ መሆኑን ገልጻለች፤ በዚህ ላይ በመስራቷም እርካታ ይሰማታል፣ በተመሳሳይ ደግሞ መድሃኒቱ እያለ በሰላምና ጸጥታ ችግር ምክንያት ሰዎች መድሃኒት አጥተው ሕይወታቸው ሲያልፍና ሲሰቃዩ ማየትና መስማቷ ደግሞ በእጅጉ እንዲሰማት አድርጓታል። ያም ቢሆን ተፈላጊ መድሃኒቶችን ለማህበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ የሚቻላትን ሁሉ እየደረገች መሆኗን ወይዘሮ መርየም ጠቅሳ፣ በተለይም መድሃኒቶች ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልጋቸው አስታውቃለች፡፡ ክትትል፣ ትኩረትና ሰላም ይፈልጋሉ ትላለች፡፡

መድሃኒቶችን ወደ አገር ውስጥ ከማስገባት ባለፈም በኤክስፖርት ሥራ ላይ መሰማራት መቻሏን ያጫወተችን ወይዘሮ መርየም፤ የኤክስፖርት ሥራ በኪሳራ የሚሰራ መሆኑን ጠቅሳ፣ ኪሳራው ግን በውጭ ምንዛሬ እንደሚካካስ ገልጻለች፡፡ መድሃኒቶችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስፈልጋትን የውጭ ምንዛሬ ለማግኘትም ማሾን (የእህል ዘር) ጨምሮ ጥራጥሬና የቅባት እህሎችን ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ በመግዛት ወደ ውጭ ገበያ ትልካለች፡፡

እሷ እንዳለችው፤ በኤክስፖርት የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ወደ አገር ውስጥ ለሚመጣው ዕቃ ጠቃሚ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ኤክስፖርት በኪሳራም ቢሆን ይሰራል፡፡ ከዚህ ቀደም በነበረው አሰራር አንድ በወጪ ንግድ የተሰማራ ነጋዴ የተለያዩ ምርቶችን ለውጭ ገበያ ልኮ ከሚያገኘው የውጭ ምንዛሬ 30 በመቶ ያህሉን ብቻ በቀጥታ እንዲጠቀም ነበር በመንግስት በኩል የሚፈቀድለት፡፡ 70 በመቶው በመንግሥት አሰራር ውስጥ አልፈው ነበር የሚጠቀሙት፡፡

ይህ አሰራር የኤክስፖርት ንግዱ አትራፊ እንዳይሆን አድርጎት መቆየቱን ነው መርየም ያስታወሰችው። በአሁኑ ወቅት ግን መንግሥት አሰራሩን አሻሽሎ 50 በመቶውን የውጭ ምንዛሬ ነጋዴው በቀጥራ ራሱ እንዲጠቀም ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ገልጻለች፡፡

ይህ አሰራር መንግሥት ካለባት የዶላር እጥረት የመጣ መሆኑን ጠቅሳ፣ አሰራሩን ነጋዴውም እንደሚቀበለው ገልጻለች፡፡ ነገር ግን መድኃኒት የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው ቢባልም በሚፈለገው ልክ አይደለም ትላለች፡፡

ለመድኃኒት የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሬ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ማግኘት እንደማይቻልም ገልጻለች፡፡ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ መድሃኒቶች በከፍተኛ ወጪ እንደሚገቡ አመላክታ፣ የውጭ ምንዛሬው ተገኝቶ መድሃኒቶቹ ወደ አገር ውስጥ ከገቡ በኋላም መድሃኒቶቹ ታክስ የሚደረጉበት ላይ ችግር እንዳለም ጠቁማለች፡፡ አንድ አስመጪ በሰጠው ዋጋ ሁሉም አስመጪ መቀረጣቸው የዘርፉ ሌላው ችግር መሆኑን አመልክታለች፡፡

እሷ እንዳስገነዘበችው፤ መድኃኒት ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልገውና ጊዜው ካለፈ የሚያደርሰው ጉዳት አደገኛ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ያሻዋል፡፡ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንደመምጣቱ መድሃኒት አስመጪዎች ተናብበው መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ ለአብነትም አንድ መድሃኒት በአገር ውስጥ ጠፋ ከተባለ ሁሉም መድሃኒት አስመጪዎች ተረባርበው ያስመጣሉ፡፡ ያን ጊዜ መድሃኒቱ በአገሪቷ ይጥለቀለቃል፡፡ የተትረፈረፈ ነገር ደግሞ ዋጋው መውረዱ አይቀርምና በዚህ ምክንያት ለመድሃኒቱ ከወጣው ወጪ ባነሰ ዋጋ ለመሸጥ መገደድ ይመጣል፤ ይህም ሌላኛው የዘርፉ ተግዳሮት ነው፡፡

ልጅ እያለች ጀምሮ በንግድ ሥራ መሰማራት እንደምትችል የሚሰማት ወይዘሮ መርየም፣ ‹‹ነጋዴ መሆን ብችልም፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራ መሥራት እጅግ ፈታኝና አስቸጋሪ ነው›› ትላለች፡፡ ለግሉ ዘርፍ በተለይም ለነጋዴው የተሰጠው ስም ጤናማ እንዳልሆነም ጠቅሳ፣ ነጋዴው በሄደበት ሁሉ በአግባቡ አይስተናገድም፤ ሁሉም እንደ አጭበርባሪ ይታያል ስትል ትገልጻለች፡፡ ነጋዴው ብዙ ዋጋ ከፍሎና ብዙ ውጣ ውረዶችን ተቋቁሞ እንደሚሰራም አስታውቃ፣ በተለይም ገቢ ሰብሳቢ ተቋም የግሉን ዘርፍ በአግባቡ ሊያገለግል፣ ሊያደምጥ፣ ሊረዳና ሊንከባከብ እንደሚገባ አመላክታለች፡፡

በአገር ውስጥ መድሀኒት የማምረት ሃሳብ ያላት ወይዘሮ መርየም፤ በአሁኑ ወቅት ለ30 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችላለች፤ በቀጣይም ሥራዋን በማስፋት ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል የመፍጠር ፍላጎት አላት፡፡

አትክልት የመትከልና የመንከባከብ ልምድ እንዳላትም ጠቅሳ፣ በግብርናው ዘርፍ ለመሰማራት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላትም ነው የነገረችን፡፡ ግብርና የሁሉም ነገር መሰረት መሆኑን ጠቅሳ፤ በዘርፉ ለመሰማራት ያላትን ዝግጁነት ገልጻለች፡፡

ነግዶ ለማትረፍም ሆነ ዘርቶ ለመቃም፤ ወልዶ ለመሳምና ወጥቶ ለመግባት ሰላም መተኪያ የለውም ያለችው ወይዘሮ መርየም፣ እያንዳንዳችን ለሀገር ሰላም የበኩላችንን እናዋጣ የሚል መልዕክቷንም አስተላልፋለች።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚተጉትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስለአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## የገና በዓልን ከካንሰር ታማሚ ሕፃናት ጋር ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ክፋት ያልበረዘው፣ ተንኮል ያልወረሰው ማንነት:: በዕንባና ሳቅ የተዋዛ ለንፁህ አንደበት የተገዛ ሰውነት። የሕይወትን ጣፋጭ/መራር ጣዕም የማይለይ፣ እሳት ውሃውን የማይመርጥ ደግ ጊዜ - ልጅነት::

ዛሬ እንግዳ ሆኜ የተገኘሁት ይህን እውነታ ቀርቤ በማይበት ዕንቦቀቅላ ሕፃናት መሀል ነው:: አብዛኞቹ ለማየት የሚያሳሱ ናቸው:: በአግባቡ የተያዙ፣ በቆንጆ ልብሶች የተዋቡ ንጹህ ሕፃናት:: ልብሳቸው ብቻ ሳይሆን ውስጣቸው ጭምር እንደ ነጭ ወረቀት ጎልቶ የሚታይ ንፁሃን መሆናቸውን ነጋሪ አላሻኝም::

በእናቶቻቸው ዕቅፍ ያሉትን ጨምሮ ከወዲያ ወዲህ የሚሯሯጡ ልጆች ቤቱን አድምቀውታል። በቻልኩት አቅም የሁሉንም ገጽታ ለማስተዋል ሞከርኩ:: አብዛኞቹ ጸጉራቸው ትኩስ መላጣ በሚባል መልኩ ሙልጭ ብሎ ተላጭቷል:: በሁሉም ገጽታ ፍጹም በቃል የማይገለጽ የዋህነት ይነበባል::

ውስጤ አንዳች ነገር ያቀበለኝ ይዟል:: እነዚህ ልጆች ስለነገ ብዙ ናቸው:: ሀገር በእነሱ ላይ ብሩህ ተስፋን ትጥላለች:: የራሳቸው፣ የቤተሰቦቻቸው ድካም ወደፊት የማንነታቸው መሠረት ይሆናል። ከእነሱ መሀል ስለነገ መድረሻው አስቀድሞ የሚያልም አለ::

ዶክተር፣ ፓይለት፣ ኢንጂነር፣ መምህር፣ ሀገር ጠባቂ ወታደር መሆን የሚሻ ብዙ ነው:: አሁንም እያንዳንዱን ሕፃን በአትኩሮት ማስተዋል ይዣለሁ። በገጽታቸው ላይ የተለያየ መልክ እያየሁ ነው:: የሳቀ፣ ያኮረፈ፣ የተከዘ፣ ዝም ያለ ፊት ከፊቴ ይመላለሳል::

ዛሬ የገና ዋዜማ ነው:: በዚህ ቀን በርካቶች ስለበዓሉ ስጦታ ይለዋወጣሉ:: ማግስቱን ለሚከበረው ዓመት በዓል ቤታቸውን ያስጌጣሉ፣ የገናውን ዛፍ በድምቀት ያስውባሉ:: እነዚህ ሕፃናትና ወላጆቻቸው ግን ዛሬ በቤታቸው አልተገኙም:: ልጆቹ እንደ እኩዮቻቸው፣ እናቶቻቸውም እንደ ጎረቤቶቻቸው አውደ ዓመትን ለማክበር ጉድ ጉድ የሚሉ አልሆኑም::

እነሱ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጠው፣ በዚህ ስፍራ የተገኙት በምክንያት ነው:: አሁን ወላጆቻቸው ስለ ልጆቻቸው መኖር ግድ ይላቸዋል:: ልጆቹ በጤና ዘልቀው ተስፋቸው ይሰምር ዘንድ ዛሬን ከቤትና ቀያቸው ሊርቁ ተገደዋል:: እነዚህ ሕፃናትና ወላጆቻቸው በትናንትናው የሕይወት መንገድ ብዙ ፈተናዎችን ተጋፍጠዋል:: ስለነገ ግን ከቶውንም ተስፋ አይቆርጡም::

እነሆ በ“ማቴዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ” ቅጥር ግቢ ተገኝቻለሁ:: የገና በዓል ዋዜማን ከካንሰር ሕሙማን ሕፃናት ጋር እያከበርኩ ነው። በዝግጅቱ ሕፃናቱንና ወላጆቻቸውን ጨምሮ የግቢው ማኅበረሰብ፣ የሶሳይቲው ወዳጆችና ሌሎችም እንግዶች በአካል ተገኝተዋል::

ዕለቱን አስመልክቶ ዋዜማውን ከልጆቹ ጋር ለማሳለፍ በስፍራው የተገኙት የማርዮት ሆቴልና አፓርትመንት ሠራተኞች ለልጆቹ የገና ስጦታን ይዘዋል:: በዓሉን የሚመጥኑ ጣፋጮችንም አዘጋጅተዋል:: በዝግጅቱ የታደሙት ወላጆች የዕለቱ ልዩ እንግዶች ናቸው:: እንደ ወጉ ዓውደ ዓመቱን በቤታቸው ባያከብሩም እነሱን አክብሮ ‹‹እንኳን አደረሳችሁ!!!›› የሚል ወገን ማግኘታቸው አስደስቷቸዋል::

ዝግጅቱ በድምቀት ተጀምሯል:: በመሰብሰቢያ አዳራሹ ግድግዳ ላይ የተሰቀሉት ቀይና ነጭ ፊኛዎች፣ መብራቶችና ደማቅ ጌጣጌጦች ለበዓሉ ልዩ ውበትን አላብሰዋል:: ጣፋጮቹ፣ ከረሜላዎቹና ስጦታዎቹ በዓይነት ተደርድረዋል::

ልጆቹ ይህ ሁሉ የሆነው ለእነሱ መሆኑን እያወቁት ነው:: አንዳንዶቹ በተኮላተፈ ጣፋጭ አንደበታቸው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው “ሀፒ በርዝደይ . . .” (መልካም ልደት) እያሉ ይዘምራሉ:: ሁሉም ፍጹም ጨዋነት በተሞላው ሁኔታ ከእንግዶቹ ጋር እያሳለፉ



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

ነው::

የማርዮት ሆቴልና አፓርትመንት ሠራተኞች ላለፉት ስድስት ዓመታት ከሶሳይቲው ጋር በተለያዩ ተሳትፎዎች አሳልፈዋል:: የአንድ ቀን ደመወዛቸውን ከማበርከት ጀምሮ አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ በማድረግም እስካሁን ከካንሰር ከሕሙማኑ ጎን አልተነጠሉም::

የማርዮት ሠራተኞች ሁሌም እንደ ቅርብ ቤተሰብ ናቸው:: ከጓዳ፣ ከማጀቱ የጎደለውን አይተው ይሞላሉ:: የገበታው በረከት ለመሆንም እጃቸው ሰስቶ አያውቅም:: ለተቋሙ አስፈላጊ የሆኑ የሥልጠና ድጋፎችን ማበርከት ልማዳቸው ነው:: እንደ ዛሬው ዓውደ ዓመት በሆነ ጊዜም ‹‹እንኳን አደረሳችሁ!!!›› ለማለት ቀዳሚዎች ናቸው::

የማርዮት ሆቴልና አፓርታማ መርህ ሁሌም ማኅበረሰቡን መሠረት ያደርጋል:: በተለይ ደግሞ በሕመም ለተጎዱና ልዩ ድጋፍ ለሚያሻቸው ወገኖች ያለው እይታ ለየት ይላል:: ሠራተኞቹ ሁሌም በዚህ ስፍራ በተገኙ ጊዜ ፍቅራቸው ከፊታቸው ይነበባል:: ትህትናን በማሳየት ‹‹ከጎናችሁ ነን›› ማለትን ያውቁበታል:: ከጊዜያቸው ጊዜ ቀንሰው፣ ከኪሳቸው ማካፈል የዘወትር መለያቸው ነው::

የማርዮት ሠራተኞች ለበዓል ያመጡትን ስጦታ ለማበርከት በሶሳይቲው አዳራሽ በተገኙ ጊዜ ወይዘሮ ሳምራዊት ስለ እሷና ስለ ሥራ ባልደረቦቿ መልዕክት አስተላለፈች:: ሳምራዊት የማርዮት ሠራተኛ እንደ መሆኗ በንግግሯ ብዙኃኑን ወክላለች::

ሳምራዊት እንዳለችው እሷና ሌሎች ሠራተኞች ወደ ማቲዎስ ሶሳይቲ በመጡ ጊዜ በተሰሩት ተግባራት በእጅጉ ተደስተው ነበር:: በወቅቱ ይህን የመረዳዳት ዕድል በማግኘታቸውም ዛሬን አብረው ተጉዘዋል:: ይህ በመሆኑ ደግሞ ለድርጅቱ ያላቸው አክብሮትና ምስጋና በእጅጉ የላቀ ነው::

ሳምራዊት እንደምትለው በመስጠትና መቀበል መካከል ባለው ሂደት መመስገን ያለበት ሰጪው ሳይሆን ተቀባዩ ነው:: “ለምን?” ከተባለ ደግሞ የእርካታና ደስታው ውጤት ሲለካ ሚዛኑ የሚደፋው በሰጪው አእምሮ ላይ ስለሆነ ነው::

ከማቲዎስ ወንዱ ጋር የነበረው የዓመታት ጉዞ መሠረቱም ይኸው ነው:: ሁሉም ሠራተኛ በሚባል መልኩ ለድርጅቱ አቅምና ጉልበት ለመሆን ወደኋላ ብሎ አያውቅም:: የዛሬው የገና በዓል ስጦታና ቆይታ በዚህ ብቻ አይቋጭም:: ወደፊት በሚኖሩ መሰል አውደ ዓመቶችና አስፈላጊ ቀናት ሁሉ የማርዮት አጋርነት አይጓደልም::

በስፍራው ተገኝተው እንግዶቹን የተቀበሉት የማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ መስራችና ባለቤት አቶ ወንዱ በቀለ ስለተደረገው ስጦታ ሁሉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል:: ከንግግራቸው ለማወቅ እንደተቻለው ማርዮት ማለት ሸራተንን ጨምሮ የሚያስተዳድርና በዓለም ላይ ወደ ስምንት ሺህ ሆቴሎች ያሉት ታዋቂ ድርጅት ነው::

በአዲስ አበባው ማርዮትና ሸራተን ሆቴል ለካንሰር ሕሙማን ገቢ ማሰባሰቢያ የሚሆን የርዳታ ሳጥን እንዲቀመጥ ተደርጓል:: ለዚህ ሳጥን መቀመጥ ፈቃድ የተሰጠው ብቸኛ ድርጅት ደግሞ የማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ብቻ ነው::

የማርዮት ሠራተኞች ከደመወዛቸው በማሰባሰብ ለድርጅቱ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይገዛሉ:: በሆቴሉ መጠቀም ባስፈለገ ጊዜም ክፍያውን በግማሽ በመቀነስ ትብብራቸውን ያሳያሉ:: ዛሬ ደግሞ ከግቢው የካንሰር ታማሚ ሕፃናት ጋር የገና በዓል ዋዜማን ለማሳለፍ ተገኝተዋል::

እሳቸው እንዳሉት በዓለማችን ወደ 200 የሚጠጉ የካንሰር አይነቶች አሉ:: ካንሰር አስቀድሞ ከተደረሰበት መፍትሔው ይገኛል:: አሳዛኙ ነገር ግን የሕፃናትን ካንሰር አስቀድሞ መከላከል አለመቻሉ ነው:: በተለይ እኛን በመሰሉ ሀገራት ሕመሙ ባጋጠመ ጊዜ ሕይወት ፈተና ይሆናል:: እንደ አቶ ወንዱ ገለጻ ካንሰር በሕፃናት ላይ መገኘቱ አስቀድሞ ከታወቀ ግን አክሞ ለማዳን ያለው ዕድል ሰፊ ነው:: ለዚህ ምሳሌ ሆኖ የቀረበው ወጣቱ አለኸኝ ነበር::

አለኸኝ ዕለቱን በሶሳይቲው ተገኝቶ በበዓል ዋዜማው ተሳትፏል:: ከዛሬ አስር ዓመት በፊት በዕጢ ካንሰር መያዙ ሲታወቅ ገና የአስር ዓመት ልጅ ነበር:: ኑሮው በገጠር የሆነው ሕፃን በወቅቱ ቤተሰቦቹ ስለሕመሙ ምንነትና ክብደት አንዳች የሚያውቁት መረጃ እንዳልነበረ ያስታውሳል::

ዛሬ የሃያ አንድ ዓመት ወጣት የሆነው አለኸኝ በሕይወት ውጣ ውረድ ብዙ አሳልፏል:: ለሕክምና ከጎጃም አዲስ አበባ ሲመላለስ መንገዶች አልጋ በአልጋ አልነበሩም:: በየጊዜው የሚወስደው ‹‹ኬሞቴራፒ›› ከባድ ቢሆንም ከትምህርት አላገደውም:: በጥንካሬ ተጉዞ ዘጠነኛ ክፍል ደርሷል::

አለኸኝ አንድ እግሩ ላይ የተገኘውን የእጢ ካንሰር ለመታከም ከሚኖርበት ወረዳ ወደ ደብረማርቆስ፤ ከዛም ባህር ዳርና አዲስ አበባ ተመላልሷል:: ሕክምናው በቋሚነት ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በሆነ ጊዜም በዘመድ ቤት እያረፈ፣ ጤናውን ሲከታተል ቆይቷል::

የማቲዎስ ወንዱ ሶሳይቲ ቤተሰብ እስኪሆን ድረስ እንግልቱ ቀላል አልነበረም:: አንዳንዴ ቤተሰቦቹ ታክሞ ይድን አይመስላቸውም:: ሁሌም ለትራንስፖርት ሊሰጡት አይፈልጉም:: ለእነሱ የእሱ ከገጠር አዲስ አበባ መመላለስ ዋጋ ቢስ ነው:: ሁሌም በንግግራቸው ከቤቱ አርፎ እንዲቀመጥ ይመክሩታል።

የማቲዎስ ወንዱ ካንሰር ሶሳይቲ አለኸኝን የመሰሉ ታካሚዎች መኖራቸውን ባወቀ ጊዜ ሙሉ የትራንስፖርት ፍጆታቸውን ይሸፍናል:: አስፈላጊ የሚባሉ መድኃኒቶችን በመግዛትም ሸክማቸውን ያቀላል:: የላብራቶሪና፣ የሲቲስካን ወጪዎችን በተጠየቁ ጊዜ ሁሌም ከጎናቸው ነው::

ድርጅቱ ሆስፒታል ተኝተው መታከም ላለባቸው ሕሙማን አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ወደኋላ አይልም:: ከአጋር ድርጅቶች በሚያገኘው እገዛም በትምህርት ዓለም ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ያስተምራል:: አቶ ወንዱ እንደሚሉት ወደፊት ይህ ሶሳይቲ ብዙ ዕቅዶችን ነድፏል፤ ራዕይም ሰንቋል::

‹‹ጤናማ አፍሪካ›› በሚል ስያሜ በሚቋቋመው ደሀ ተኮር ፕሮጀክት በሽታን አስቀድሞ መከላከል የሚቻልበትና ጤናማ ኑሮን መምራት የሚታሰብበትን ጉዳይ ዕውን ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ነው::

ዕለቱን ከሕፃናቱ ጋር ዋዜማውን ለማሳለፍ ከተገኙት እንግዶች መካከል ወጣት አልሻዳይ አንዷ ነች:: አልሻዳይ ኑሮዋ በሀገረ አሜሪካ፣ ሺካጎ ከተማ ነው:: ወደ ኢትዮጵያ ለእረፍት በመጣች ጊዜ በአንዲት ባልንጀራዋ ምሪት ድርጅቱን በአካል ተገኝታ የማየት አጋጣሚውን አግኝታለች::

የኤልሻዳይ ፍላጎት ሰብዓዊነትን መሠረት ያደረገ ነው:: ሁሌም በሰዎች መሀል ተገኝታ ስሜታቸውን መጋራት፣ ችግራቸውን መካፈል ትወዳለች:: በዚህ ሰፍራ ባየችው ነገር ሁሉ ደስተኛ ነች:: ወደፊት በሶሳይቲው ስላገኘቻቸው ልጆች የያዘችውን ህልም በተግባር የመፍታት ዕቅድ አላት::

በስፍራው ተገኝተው ለሕፃናቱ ፍቅር ከለገሱት እንግዶች መካከል ርብቃና ጓደኞቿ ይገኙበታል። እነ ርብቃ የካቶሊክ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ናቸው። በማቲዎስ ወንዱ የካንሰር ሶሳይቲ የበጎ ፈቃድ አገልጋዮች በመሆን ሲሳተፉ ቆይተዋል::

በእነ ርብቃ እሳቤ ሰዎች ከመቀበል ይልቅ በመስጠት የሚያገኙት እርካታ ይበልጣል:: ብዙዎች ይህን ባደረጉ ጊዜ ስለሕይወት ያላቸው ዕይታ ይቀየራል:: እነ ርብቃ በዚህ መንገድ መጓዝ ከጀመሩ ወዲህ ውስጣቸው ያደረው ሰላምና እፎይታ ከሁሉም የላቀ ነው::

እንደ በጎ ፈቃድ አገልጋይነታቸው ሁሌም በስፍራው በደረሱ ጊዜ ውስጣቸው ሰላምና ፍቅር ያገኛል:: ዘወትርም በመስጠት ይጠቀማሉ፣ በመስጠት ይደሰታሉ:: ይህ እውነት ወደ እነሱ ይመላለስ ዘንድም በየጊዜው ከበጎነት አይርቁም::

እንደ አቶ ወንዱ በቀለ ተሞክሮም ሰዎች ከእጃቸው ያለውን በሰጡ፣ ባበረከቱ ቁጥር ጥቅሙን የሚወስዱት ራሳቸው ይሆናሉ:: ለዚህ እውነታም ምስጋናውን ማድረስ የሚኖርባቸው ተቀባዮች ሳይሆኑ ሰጪዎች ሊሆኑ ይገባል:: ምክንያቱም በመስጠት የሚገኘውን ደስታና ርካታ በመውሰድ ቀዳሚዎች ናቸው::

የገና በዓል ዋዜማን ከሕፃናቱ ጋር ለማሳለፍ የተገኙትን እንግዶች ጨምሮ የማቲዎስ ወንዱ ሠራተኞች ዕለቱን አስመልክቶ ለልጆቻቸው ስጦታዎችን አበርክተዋል:: በስጦታው ወቅት ተቀባዮቹ ስማቸው በተጠራ ጊዜ የነበረው አቀባበል ይለያል:: ልጆቹ ከነበረቡት ተነስተው ስጦታቸውን በሚቀበሉበት ወቅት ሲባል የነበረውን የእርካታ ትርጓሜ በእውን ማረጋገጥ ይቻላል::

ልጆቹ ስጦታቸውን ሲወስዱ የታየባቸው ፈገግታ ከተለመደው የልጅነት ስሜት የዘለለ አልነበረም። በስፍራው የነበረው ታዳሚ ግን በርግጠኝነት ደስታ የሚሸመተው ከተቀባዩ ሳይሆን ከሰጪው ልቦና መመንጨቱን በተግባር አይቶ አረጋግጧል::

ይህን እውነት ደግሞ ከልጆቹ ወላጆች ጥልቅ ምርቃትና ደማቅ ፈገግ ላይ ማንበብ ይቻላል:: አዎ! ይህ ሀቅ በመስጠት ለራስ የሚተርፍ እውነተኛ የደስታን ስሜትን መሸመት እንደሚቻልም ያረጋግጣል:: ለመላው የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ምዕመናን በሙሉ መልካም የገና በዓል ይሁን!!!

# ከኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት

## ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# 2ኛው የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን ብሔራዊ ምክር ቤት ጉባዔ

**ኢያሱ መሰለ**

የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን ብሔራዊ ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1273/2014 የተቋቋመ ነው። ምክር ቤቱ ማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድሕንን እንደ ሀገር ተደራሽ ለማድረግ ከወረዳ እስከ ፌደራል ድረስ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር ይመክራል፤ የአተገባበር አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤ አፈጻጸሞችንም ይገመግማል፤ ጠንካራ ጎኖች እንዲቀጥሉ፤ ክፍተቶችም እንዲታረሙ ያደርጋል። በነዚህ ተግባሮቹ ምክንያት በማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድሕን ዘርፍ የተቀመጡ የአጭርና የረዥም ጊዜ እቅዶችና ስትራቴጂዎች ግብ እንዲመቱ ብርታት ሆኗል።

ብሔራዊ ምክር ቤቱ ታኅሣሥ 22 ቀን 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ስካይ ላይት ሆቴል በ2015 በጀት ዓመት አፈጻጸምና በ2016 በጀት ዓመት የትኩረት መስኮች ላይ ያነጣጠረ ውይይት አድርጓል። በውይይት መድረኩም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፣ ሚኒስትሮች፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ተወካዮች፣ የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች፣ የከተማ አስተዳደር ከንቲባዎች፣ የክልል የጤና ቢሮ ኃላፊዎች፣ የብልጽግና ፓርቲ የክልልና የከተማ አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች፣ የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት ኃላፊዎችና ተወካዮች ተገኝተዋል።

በዕለቱ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ፤ ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋንን ለሁሉም ዜጎች በፍትሐዊነት ተደራሽ በማድረግ፤ እንዲሁም ጠንካራ የጤና ሥርዓት በመገንባት የጤና ልማት ግቦችን ለማሳካትና ጤናማ ዜጋን ለመፍጠር እንደ ሀገር በርካታ ሪፎርሞች (ማሻሻያዎች) እየተተገበሩ



እንደሚገኙ ገልጸዋል። በየደረጃው የጤና አገልግሎት ተቋማትን ለማስፋፋት በተደረገው ጥረት እስከ 2015 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ 379 ሆስፒታሎች እና 3ሺ 826 ጤና ጣቢያዎች ተገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ የጤና አገልግሎት ሽፋኑን ከ90 በመቶ በላይ ማድረስ መቻሉን ተናግረዋል።

የጤና ፋይናንስ ሥርዓቱን ለማጎልበትም ሆነ ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋንን ለማረጋገጥ የጤና መድሕን ስትራቴጂን በመቅረጽ ላለፉት ዓመታት የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድን ሥርዓት ሲተገበር እንደቆየ አንስተዋል። ይህንን ትግበራ ይበልጥ ለማጠናከርና ጠንካራ የጤና መድሕን ሥርዓት ለመገንባት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1273/2014 መሠረት በማድረግ የተቋቋመው ብሔራዊ ምክር ቤት ሥራ በጀመረበት ወቅት ያስቀመጣቸውን መሠረታዊ አቅጣጫዎች ተከትሎ በየክልሉ ያለው አመራር ባደረገው ሰፊ ርብርብ ቀደም ሲል ከነበሩት የበጀት ዓመቶች የተሻለ ትልቅ ውጤት እንደተመዘገበም ጠቅሰዋል። ለውጤታማነቱም በየደረጃው ያሉ አመራሮችና ባለሙያዎች አስተዋፅዖ እንደነበራቸው ጠቅሰው በጤና ሚኒስቴር ስም ምስጋና አቅርበዋል።

ይሁንና በማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድሕን በፕሮግራም መታቀፍ ካለባቸውና ከድህነት ወለል በታች ከሚገኙ ዜጎች እስከ አሁን ተደራሽ መሆን የተቻለው 59 በመቶ ለሚሆኑት ብቻ እንደሆነ ጠቅሰው የተቀመጠው ስትራቴጂክ ግብ ላይ ለመድረስ ቁጥሩን ከፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። ፕሮግራሙ ከዘመቻ ሥርዓት ተላቆ በተዘረጋለት የአሠራር ሥርዓት መሠረት እንዲጓዝ ማድረግ፤ የአባልነት ምጣኔን ማሳደግ፤ የተጀመሩ ሪፎርሞችን ማስቀጠል፣ አጠቃላይ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱን ለማሻሻል በተለይም የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድሕን ዓመታዊ የፋይናንስ ኦዲት ሥራን አጠናክሮ ማስቀጠል፤ በኦዲት የሚገኙ የገንዘብ ጉድለቶችን ማስመለስና ተከታትሎ ርምጃ መውሰድ፣ በ2016 በጀት ዓመት ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ስለሆነም የ2016 በጀት ዓመት የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድሕን ፕሮግራም ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆንና ቀጣይነት ባለው መልኩ የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንዲያስችል ትኩረት የተሰጣቸውን ጉዳዮች ከክልላዊ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል። በመሆኑም አመራሩና ባለድርሻ አካላት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው በባለቤትነት የመምራት፣ የመደገፍና ክትትል የማድረግ ሚናቸውን እንዲወጡ ክብርት ሚኒስትሯ ጥሪ አቅርበዋል።

የእለቱ የክብር እንግዳና የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድሕን ብሔራዊ ምክር ቤት ሰብሳቢ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ክቡር አቶ ደመቀ መኮንን ባደረጉት ንግግር፤ ሀገር አቀፍ ምክር ቤቱ ያስቀመጣቸው አቅጣጫዎች በአመዛኙ ተግባራዊ በመሆናቸው በ2015 በጀት ዓመት የወረዳዎች ሽፋን በአጭር ጊዜ እድገት ታይቶበታል ፤ ለዚህም እውቅና መስጠትና ማበረታታት ያስፈልጋል ብለዋል። የጤና መድሕን አገልግሎት የጤና ሥርዓትን አቅም ለማጠናከር በእጅጉ እንደሚረዳ ጠቅሰው ብዙኃኑን የፓኬጁ አካል በማድግ የጤና እክል የሚደርስባቸው ጥቂት ዜጎች በብዙኃኑ ድጋፍ ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል ብለዋል።

የወረዳ ሽፋን እና የአባላትን ቁጥር ማሳደግ እንደ ሀገር ሳይዥጎረጎር ወጥ በሆነ መንገድ ሊከናወን እንደሚገባም አሳስበዋል። የክፍያ ሥርዓቱ መርሕን የተከተለ እና አቅምን መሠረት ያደረገ፤ የመንግሥትን የድጎማ ጫና የማያበዛ መሆን እንዳለበትም ተናግረዋል። የገንዘብ አቅምን ወደ አንድ ቋት ማሰባሰብ አስፈላጊ እንደሆነ ጠቅሰው በዞን፣ በክልልና በፌደራል ደረጃ ቋቶችን መክፈት እንደሚያስፈልግም አስረግጠዋል።

እስከ አሁን ትኩረት ተደርጎበት እየተሠራበት ያለው ማኅበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ላይ እንደሆነ ተናግረው አገልግሎቱ የተሟላ እንዲሆን ፕሮግራሙን ወደ ማኅበራዊ ጤና መድሕን ወይም በመደበኛ ገቢ ወደ የሚተዳደሩት የኅብረተሰብ ክፍሎች ማሻገር እንደሚስፈልግ ገልጸዋል። ለዚህም ስትራቴጂክ ፕላኑ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል ብለዋል።

# ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

## ጋር በመተባበር በየሣምንቱ የሚታተም

# እንኳን ለብርሃነ ልደቱ በሰላም አደረሳችሁ



**የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ መልካም የገና በዓል እንዲሆንላችሁ ይመኛል።**

ተቋማችን የመንግሥት አሠራርና አገልግሎት አሰጣጥ በሕግና በሥርዓት እንዲመራ፤ የዜጎችን መብት በማክበርና ተጠቃሚነታቸውን ባረጋገጠ መልኩ እንዲከወን ከሕዝቡ ጋር በመሆን እየሠራን እንገኛለን።

በመንግሥት ተቋማት ውስጥ የሚፈጠር እንግልት፤ የሕግና የአሠራር ጥሰት፤ ከቢሮም ውጪ በሕዝቡ ላይ የሚደርሱ የአስተዳደር በደሎችን ለመከላከልና ለማረም እንዲሁም በሕግ የተደነገጉ የዜጎችን መብቶች መከበራቸውን ለመከታተል በምናደርገው ጥረት ሁሉ የሚያጋጥሙንን ፈተናዎች ተሻግረን በሕዝብና በሀገር የሚጠበቅብንን ኃላፊነት መወጣት እንድንችል አስፈፃሚ አካላትና ሕዝቡ ከተቋማችን ጎን እንዲሆኑ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ሕግና ሥርዓትን አክብሮ ሕዝብን በማገልገል አስተዳደራዊ በደሎችን መከላከል እንዲሁም ታስቦበትም ይሁን በአጋጣሚ በሕዝብ ላይ የሚፈጠሩ ችግሮች ካሉ ፈጥኖ ማረም ስለሕዝብ ተቋቁመው ሕዝብን የሚያገለግሉ የመንግሥት ተቋማት ቀዳሚ አጀንዳ ሊሆን ይገባል እንላለን።

የመንግሥት አገልግሎትን ለማግኘት በአስፈፃሚ አካላት ለሚያጋጥሟችሁ አስተዳደራዊ ችግሮች ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት ወይም በክልሎች ወደሚገኙ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቻችን በመምጣት አለያም በነፃ ስልክ 7502 ወይም በቢሮ ስልክ 0115580021/26 በመደወል አስተዳደራዊ በደሎችን የተመለከቱ አቤቱታዎች፣ ቅሬታዎችና ጥቆማዎች ማቅረብ የምትችሉ መሆኑን በዚሁ እንገልፃለን።

**መልካም አስተዳደርን በተግባር ማሳየት የሁሉም ተቋማት ቀዳሚ ተግባር ይሁን እንላለን!**

**መልካም የገና በዓል!**

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም**

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ